# የፍጥሞ ራዕይ

... በቀደም ወንድም ሙር በተናገረው ጉዳይ ላይ... ወንድም ኔቪል ማስታወቂያውን እየተናገረ ነበር፡ ወደ ህንጻው... እየገባ፡ ስለ ጌታ መንፈስ ተናገረ። እንዲህ አለ፡ “ዙርያዬን አይቼ እስክረጋጋ ድረስ ንጥቀት የሆነ መስሎኝ እጅግ በመደነቅ ነበርሁ፡ በኋላ ግን ሌሎች ተቀምጠው ሳያቸው፡” እንዲህ አልኩኝ፡ “አይ፡ ንጥቀት ገና አልሆነም፡ ሌሎቻቸው—እዚህ ካሉ እኔም አለሁ” አልኩኝ። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ የጌታ መንፈስ እጅግ መልካም ይሆንልናል።

2 በህንፃው ውስጥ ብዙ ወዳጆች በማየታችን በጣም ደስ ብሎናል። ለመጥቀስ መሞከር ይከብዳል። ወንድም ካርፔንተር፡ እኔ እና ሚስቴ ያጋባ ወንድም፡ በሩ ላይ ሲደርስ፡ አስተዋልሁ። ወንድም ካርፔንተር፡ በዚህ ቤተ ክርስትያን ውስጥ እጅግ በረከት የሆነን ሰው ነው፡ በአገልግሎት ህይወት ረገድ በረከት ሆኖልናል፡ ሲሰብክ፡ በሁሉም ሰፍራ ነው። እሱና፡ ሌሎች ብዙዎች ጭምር፡ እንኳን ደህና መጣችሁ ልንላችሁ እንወዳለን።

3 ትናንት ማታ የተላከልኝ አንድ ጥያቄ ይዣለሁ፡

**ወንድም ብራንሃም፡ የማቴዎስ 25 አምስቱ ሰነፎች ደናግል እንደ አሕዛብ ቅሪቶች ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉን? አምስቱ ሰነፎች ደናግል ድነዋል ነገር ግን በታላቁ የመከራ ዘመን ውስጥ ማለፍ እንዳለባቸው ተረድቻለሁ። ይህ ልክ ነውን? ከሆነስ፡ የመጨረሻው መድረሻቸው ምን ይሆን? በማቴዎስ 25፡33 እና 34 ላይ ከፍየሎች የተከፋፈሉት በጎች ሊሆኑ ይችላሉን?**

4 እንደኔ እይታ በጣም ጥሩ የሰነ መለኮት ምሁር ነው... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... እኔም እንደዚያ አስባለሁ፡ ቅሪቶች እንደሆኑ አስባለሁ፡ እንቅልፋሞቹ ደናግል የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት የሚጠብቁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት ያለባቸው በራእይ ላይ የተጠቀሱት እነርሱ ናቸው። ለምሳሌ አንዲት ሴት አንድን ጥለቷን ቆርጣ—ቀሪውን ታስቀምጣለች፡ እንግዲህ፡ የቆረጠችው ነገር፡ የራሷ ነገር ይሆናል... ወይም በምትፈልገው መንገድ ቆርጣ፡ ጥለትዋን በወደደችው ሰፍራ ታስቀምጣለች። ከዚያም የሚተርፋት ነገር ቅሪት ይባላል፡ በራሷ ነጻ ሐሳብ ከአንድ ቦታ ለመቁረጥ ትመርጣለች። የሚተርፈው ግን ቅሪት ይባላል።

5 አሁን፡ ትዝ ካላችሁ፡ አምስት ሰነፎችና አምስት ጥበበኞች ደናግል ነበሩ፡ ሁሉም ከአንድ ዕቃ የተሠሩ፡ ደናግል ናቸው። በምርጫ፡ ግን፡ እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በፊት በምርጫ ሙሽራይቱን መረጠ፡ ዓለም ሳይፈጠር በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ስማቸውን ተጻፈ፡ እግዚአብሔር ፍጻሜ የሌለው ስለሆነ፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ አሰባቸው።

6 እና አንዳንድ ጊዜ እንደምንጠቀመው ቃል “አስቀድሞ መወሰን፡” እንለዋለን፡ በምንኖርበት በዚህ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ግን በእውነት መያዣ ነው። በዘመነ ስማዕት ይህን መጠቀማቸው እጅግ አስደናቂ ነበር፡ እነርሱም አምነውበት ነበርና። አሁን ግን ከዚያ፡ ወደ ሕጋዊ ጽንስ ሐሳቦች ተወስደዋል፡

ወደ ቸርች ወደ መጣው የሕግ ትምህርት ተለውጧል... በርግጥ መልካም ነገር ነው፡ ምክንያቱም በእንግሊዝ ውስጥ ሪቫይቫል እስኪጠፋ ድረስ ሁሉም በካልቪኒስታዊነት ስለተዋጡ፡ ጆን ዌስሊም ሚዛን የሚያስጠብቀውን የአርሜንያ ትምህርት እየሰበከ መጣ። እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ ሚዛን ያስጠብቃል።

7 ስለዚህ በመቅረዛቸው ውስጥ ዘይት ያልነበራቸው እነዚያ ሰነፎች ደናግል፡ ለቅሶ፡ ዋይታ፡ እና ጥርስ ማፋጨት ወደሚገኝበት ወደ ውጫዊ ጨለማ እንደተጣሉ እምናለሁ። ያንን ከታችኛው ማስታወሻዎቻችሁ ጋር፡ ካስተያያችሁት፡ እንደገና ወደ ታላቁ መከራ ይጠቁማል። ወደ ኋላ የሚቀሩ እና በታላቁ መከራ ውስጥ የሚያልፉትን እነሱ ናቸው ብዬ እስባለሁ። ጊዜ ኖሮን በደንብ ከገባንበት፡ ጠለቅ ያለ ትምህርት አለው። እናንተም...

8 አሁን፡ አስታውሱ፡ በመጀመሪያ እንደተናገርኩት፡ ቴፖቹን ስታዳምጧቸው፡ "እነዚህ ነገሮች እኔ ትክክል ናቸው ብዬ ባመንኩት መንገድ ናቸው።" አያችሁ? እንግዲህ፡ ስሕተት ከሆኑ፡ እኔ ስሕተት—አይመስሉኝም። እኔ... የምናገረው እምነቴን ብቻ ነው። የማንንም ስሜት ለመጉዳትም አይደለም። ገብተን ወደ ጎን እናርጋቸውና፡ የተባለውን ብቻ እንውሰድ፡ ከዚያም መርምረን፡ ቅዱስ ቃል መሆኑን ማረጋገጥ አለብን። ይህን ለማድረግ የተሻለ መንገድ ይህ ነው። እንግዲህ... አሁን በምንኖርበት ዘመን፡ በብዙ አይነት ነገሮች ደጋግማ አሁንም አሁንም ደጋግማ በተደጋጋሚ ስትቃረም በቆየች አገር እየኖርን፡ እንደው፡ በድንግል ግዛት መካከል እንዳሉ ሰዎች፡ በትክክል እንዲገነዘቡት ማድረግ ከባድ ነው። ትነግራቸዋለህ፡ ያምኑታል፡ አካሄዱም እንደዚያው ነው።

9 አሁን፡ ግን፡ አንዱ **በዚህ** ጽንሰ ሃሳብ ይመጣል፡ ሌላኛው **በዚያ** ጽንሰ ሃሳብ ይመጣል፡ እና ዘጠኝ መቶ የሚጠጉ ልዩ ልዩ የሓይማኖት ተቋሞች አሉን፡ እያንዳንዱም (በትምህርታቸው) ከሌላው ጋር ይቃረናሉ፡ ስለዚህ አንደኛው ስሕተት፡ ሌላኛው ትክክል መሆን የማይቀር ነው። ስለዚህ አሁን ብቸኛው ማረጋገጫው፡ አያችሁ፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መለስ በማለት፡ መጽሐፍ ቅዱስን መፈተሽ ነው። እንዲሁም፡ ብዙ ጊዜ፡ ሰዎች የራሳቸውን ትርጓሜ ያስቀምጣሉ። እኛ ግን ምንም አይነት የሰውን ትርጉም ላለማስቀመጥ፡ የምንችለውን ያህል እንሞክራለን። እንዲሁ፡ ባለበት እንብበነው "ባለበት መልኩ፡" እንናገረው።

10 ብዙ ጊዜም አሳስቤአችኋለሁ፡ ያለውን ብቻ ከወሰዳችሁ፡ ከቅዱስ ቃል ጋር በትክክል እጅና ጓንት ይሆንላችኋል። የጂግሳው እንቆቅልሽ እንደመስካካት ነው፡ እንቆቅልሹን በትክክል ከመስካታችሁ በፊት ጥለቱን መፈለግ አለባችሁ። እንዲህ ካልሆነ ግን፡ "የሚገጥማችሁ ሰዕል... ላም በዛፍ ላይ ሣር ጋጠች፡ ይሆንባችኋል፡" ብያችኋለሁ። ስለዚህ—ነገሩ ልክ አይሆንም።

11 ለመንፈስ ቅዱስን ስንፈቅድለት... መጽሐፍ ቅዱሱን የጻፈው ማን ነው? በሰዎች ዘንድ ሆኖ መንፈስ ቅዱስ ጻፈው። ስለዚህ ምንም ያህል የተማርክ ብትሆንም፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ፡ በፍጹም አትረዳውም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ዓይን ሰውሮ፡ መማር ለሚወዱ ለህጻናት ስለገለጠላቸው ኢየሱስ አመሰግኗል። እና ከአንዱ ከጳውሎስ በቀር፡ እያንዳንዱ ደቀ መዛሙርት ይብዛም ይነስ መሃይም እና ያልተማሩ ሰዎች ነበሩ። ጳውሎስም ክርስቶስን ለማወቅ እውቀቱን ሁሉ መጣል እንደነበረበት

ተናግሯል። ስለዚህ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን “በሰዎች ጥበብ እና በታላቅ ንግግር እንዳልመጣ፡” ተናገረ፡ ምክንያቱ ያኔ—እምነታቸው በሰዎች ጥበብ ነበርና፡ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በመገለጥ ወደ እነርሱ መጣ፡ ይህም እምነታቸው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ እንዲያርፍ ነው። እኛም አሁን፡ ሳምንቱ ወይም የሳምንቱ ክፍለ ጊዜ፡ ከማለቁ በፊት፡ ዘመናት እየተሻገረች፡ የመጣችው፡ ቀጭን ፈትል አይታችሁ፡ የተፈጸመው ነገር ይህ እንደነበረ በትክክል እንድታዩ በዚህ ነገር ላይ መንጠላጠል እንፈልጋለን።

12 ስሌዳውን ትንሽ ከፍ ስላደረጋችሁት እናመሰግናለን። የተሻለ ይመስላል።

13 እንግዲህ፡ አቤት፡ እንደው... ክረምትን በሙሉ መጠቀም በቻልን ብዬ እመኛለሁ፡ ምክንያቱ ሙሉውን የራዕይ መጽሐፍ ወስደን አንዴ ማየት እንችል ነበርና። በመልካም ትምህርቶች የተሞላ ነውና። እና አስታውሳለሁ፡ ቤተክርስቲያኑ ገና አዲስ በነበረችበት ጊዜ፡ ከሃያ ዓመት በፊት ወይም ከሃያ-አምስት ዓመታት በፊት የነበረ ይመስለኛል፡ አንዴ ጀምረን... ክረምት እንደገባ፡ እስከ ቀጣይ ክረምት ድረስ፡ የራእይ መጽሐፍን አንዴ ጨረስነው።

14 ያኔ፡ መጽሐፈ ኢዮብን ስንማርም አስታውሳለሁ። ኦህ፡ ወንድም ራይት! በዚያ ላይ ለረጅም ጊዜ ቆየሁና፡ በመጨረሻ አንዲት ሴት ጽፋ ጠየቀችኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ኢዮብን ከአመድ ክምር በጭራሽ አታነሣውምን?” እንደው፡ እኔ'ኮ ነጥብ ለማሳየት እየጣርኩ ነበር፡ ምክንያቱ፡ ነገሩ ሁሉ አራት ነጥብ የሚያገኘው፡ የጌታን መንፈስ ወደ ነብዩ እስከሚመጣባት እስከዚያች ሰዓት ድረስ፡ ከዚያም መብረቁ እስኪታይ ነጎድጓዱም እስኪጮኽ ድረስ፡ ነገሩ ሁሉ የሚተሣሰረው መንፈስ በላዩ ወርዶ የጌታን ምጽአት እስኪያይ ድረስ ነው። በዚያ በአመድ ክምር እርሱን ያቆየሁበት ምክንያትም፡ ያንን ይዤ ቤት ለመግባት ነው፡ ነጥቡን ማሳየት—እንድችል ነው። ትንሽ አድካሚ፡ አሰልቺ እንደሚሆን ይገባኛል። አንድ ሰው በነገር ላይ ጨዋታ ላይ እንደሆነ ሰስማም፡ እኔም፡ ደንገጥ እላለሁ፡ ነገሩ ግብ የሚመታ ይመስላል። ምናልባት እግዚአብሔር ያንን ሰው የሚመራው ለሆነ ዓላማው ይሆናል።

15 ጥያቄውን ከማለፋችን በፊት፡ አሁን ወደዚህ ወደ ቅሪቶች እንመለስ። ግልጽ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። በተረፈ... ቅሪቶቹ በእግዚአብሔር ስለመመረጣቸው በእውነት እምናለሁ። እግዚአብሔር—ዓለም ሳይፈጠር፡ “አስቀድሞ በማወቅ” ችሎታው፡ ቅሪቶችን እንደመረጣቸው እምናለሁ። ቃል ሳይሆን... አሁን **አስቀድሞ መወሰንን** ተመልከቱ፡ ቃሉ በህዝቡ መካከል እንደማይታይ ትንሽ መውጊያ ነውና። አያችሁ? እግዚአብሔር ግን፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ማለቂያ በሌለው በታላቅ አእምሮው፡ ቤተ ክርስትያኒቱን መረጠ፡ ኢየሱስን መረጠ፡ ቤተ ክርስትያንን መርጧታል፡ በዚህም ምክንያት ገና ከመጀመሪያው ስለ መጨረሻው መተንበይ ይችላል። እርሱ... ፍጻሜ የሌለው ከሆነ፡ የማያውቀው ነገር የለም ማለት ነው። በምድር ላይ የሚኖር እያንዳንዱ ቁንጫ፡ አይኑን ስንት ጊዜ እንደሚነካካ ጭምር ያውቀዋል። አሁን፡ ልክ እንደዚህ ነው... በተጨማሪም ምን ያህል ስም እንደሚሰራ፡ አንድ ላይ ምን ያህል እንደሚሰሩ ያውቃቸዋል። ይህ ማለት ፍጻሜ የሌለው ነው፡ ፍጻሜ

አልባ ነው፡ በምንም መንገድ… እሱን—ማብራራት አትችሉም። ስለዚህ እግዚአብሔር፡ ይህ ነው፡ ፍጻሜ የለውም።

16 ስለዚህ፡ ካስተዋላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን ስለሚመጣው ስለ ጸረ ክርስቶስ ይናገራል…

17 አሁን በደንብ ስሙኝ! ብቸኛው ጉድለት… ምናልባት በእኔ ሚልዮኖች ሊያገኙብኝ ይችላል። ነገር ግን ውድ ወንድማችን ቢሊ ግራሃም፡ ባለፈው እሁድ ቀን፡ የሰበከው ድንቅ ሰብከት፡ በእርግጥ ወቅታዊ መልእክት ነው ብዬ እሰባለሁ። ነገር ግን… እርሱ ሲናገር "ሰይጣን የተመረጡትን ሳይቀር ያታልላል" ብሎ ተናግሮ ነበር።

18 አይደለም፡ መጽሐፍ ቅዱስ ያለው፡ "የሚቻል **ቢሆን ኖሮስ** የተመረጡትን እንኳ እስኪያስት ድረስ ነው።" እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በፊት የመረጣቸው ስለሆኑ ግን፡ የማይቻል ነገር ነው። አያችሁ? በጉ… ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የታረደው በግ ነው። እግዚአብሔር በአእምሮው ውስጥ አሰቦ፡ ያንን ቃል አንዴ ከተናገረ፡ በፍጹም አይለወጥም፡ በፍጹምም አይሻርም። አያችሁ፡ ምክንያቱ እርሱ—ወሰን የሌለው—በመሆኑ፡ ቃላቶቹ ይፈጸማሉ።

19 አሰቡት፡ አሁን… ዛሬ ማታ ተቀምጠንባት ያለች ምድርም የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ናት። አለም በአንድነት ተገልጠው ባልታዩ ነገሮች ተመሰረተች። በቃ "ይሁን፡" በማለቱ ብቻ፡ ሆነ። እግዚአብሔር በመናገር ብቻ ፍጥረትን መገንባት ከቻለ፡ የታመመ አካልን ለመፈወስ ለእርሱ እንዴት ቀላል ነው። ቃሉን፡ ተመልከቱ። ቃሉ ምን እንደሆነ የምናይበት እምነት ብቻ በኖረን! አይይ፡ እንጃ ብቻ… በሃሳባችን ከመሬት ጋር እጅግ ታሰረን ተዋህደናል። ችግሩ ብዙ ክትባቶች ወሰደናል፡ ከአንደኛው አንድ መርፌ፡ ከሌላኛው ሌላ መርፌ እየወሰድን፡ ሁሉም ነገር ወደተሳሰረበት ሰፍራ—ደርሰናል። ነገሩን ሁሉ እርግፍ አርጋችሁ አራግፋችሁ፡ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ ማወቅ ብትችሉ ግን፡ እርሱ የማይወድቅ እንደሆነ ሁሉ ቃሉም እንደማይወድቅ ታውቁ ነበር። ቃሉ ከወደቀ ግን፡ እግዚአብሔር ወደቀ፡ እግዚአብሔር ከወደቀ… እንግዲያውስ እግዚአብሔር አይደለም። አያችሁ? ሌላው… ይህ አስታውሱ፡ **እዚህ** አንድ ነገር ተናግሮ **እዚያ** ሌላ ነገር አይናገርም፡ እርሱ እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ከመጀመርያ ውሳኔው ጋር መጽናት አለበት። ስለዚህ፡ ከእኛ-…

20 አንድ ነገር ብቻ ይጠብቅብናል፡ ይህም እርሱ ያለው ሁሉ እውነት እንደሆነ እናምን ዘንድ ነው፡ ከዚያ በኋላ እራሱ ይፈጽመዋል። አቤት፡ እንዴት ውብ ነው! ድንገተኛ ነገር እንዲሆንላችሁ ትጠብቃላችሁ ወይ፡ አንዳንዴ ትንሽ እምነት ይጠይቃል። ተአምር ላይሰራላችሁ ይችላል፡ ይሁን እንጂ ጸንታችሁ ያዙት፡ በደንብ ጠብቁት፡ ይሰራላችኋል። እርሱ እንዳለው፡ "የሰናፍጭ ዘር፡ በዘሮች መካከል ትንሿ ዘር ናት።" አስተውላችሁ ከሆነ ግን፡ መቼም ቢሆን ከማንም ጋር የማትዳቀል ዘር ናት። ሰናፍጭ ከማንኛውም ነገር ጋር ማዳቀል አትችሉም፡ አይዳቀልምና። እናም እምነታችሁ፡ ከማንኛውም አይነት አለማመን ወይም ከማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ወይም ቀኖና ጋር የማይዳቀል ትንሽ እምነት ካላችሁ፡ ከእግዚአብሄር ጋር በትክክል ከጸናችሁ፡ በትክክል አብራችሁ

ከሆናችሁ፡ ከጭጋግ መካከል ያወጣችኋል፡ በደንብ ያሻግራችኋል። አዎን! ከዚያች ከእምነት ጋር ጽኑ።

21 አሁን፡ በመጀመሪያ፡ እግዚአብሔር... መጽሐፍ ቅዱስ፡ በዮሐንስ ራዕይ፡ “በመጨረሻው ዘመን፡ ስለሚመጣው የክርስቶስ ተቃዋሚ ይናገራል... ” አሁንም ወደ አንድነት እየተሰበሰቡ ያሉትን አብያተ ክርስትያናትን ተመልከቷቸው። “በመጨረሻው ዘመን፡ የክርስቶስ ተቃዋሚው፡ ከዓለም ምስረታ ጀምሮ ስሞቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፋትን በምድር ላይ ያሉትን ሁሉ ያታልላል።” ስሞቻችሁ በሕይወት መጽሐፍ ላይ የተጻፈው መቼ ነው? ገና ዓለም ሳይኖር በፊት፡ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል አስቀድማችሁ በዚህ ዘመን ውስጥ ተመርጣችኋል።

22 እኔም ከኤዲ ፔሮኔት ጋር፦

ነፍሴን በእረፍቱ ሰፍራ አኖርኳት፡
ላልሄድ ወደ ጫካው፡ ወደ ጥርጣሬው ባሕር ላልወሰዳት፡
የቁጣው ማዕበል፡ ጥልቁን ሲጠራርግ፡
እኛ ግን በኢየሱስ አገኘን የዘላለም ምሕረት።

23 ሊለየን የሚችል ምንም ነገር የለም (እግዚአብሔር... በቃሉ ላይ አይጸጸትም። ወሰን የሌለው ነው እየተባለ፡ **እዚያ** እንደሚያጣችሁ እያወቀ፡ መንፈስ ቅዱስ **እዚህ** የሚሰጣችሁ ከሆነ፡ የሚሠራው ስራ ምን ዓይነት ሽቀጥ ነው? )፡ መንፈስ ቅዱስንም ተቀብላችሁ፡ በገዛ ልምምዳችሁ ካልተታለላችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ግን ተመልከቱ፡ ኤፌሶን 4፡30፣ “እስከ ቤዛነት ቀን የታተማችሁበትን፡ ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ... ” እስከ ቀጣይ ሪቫይቫል? ትክክል ይመስላልን? “እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ ታተማችሁ!” እስከ መቼ? እስከ ቤዛችሁ ድረስ።

24 የባቡር ፉርጎን ውስዱ፡ ተሽከርካሪውን ላይ በደንብ ጭናችኋል እንበል፡ ልክ እንደተጫነ... ተሽከርካሪውን፡ ወዲያው አትዘጉትም፡ መጀመሪያ ተቆጣጣሪው መምጣት አለበት። የሚንገጫገጭ ዕቃ እንዳይኖር፡ በደንብ ይፈትሻል። ምናልባት ፉርጎው... ፉርጎው’ኮ በደንብ የተጫነ ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን ገና ክፍተት ካለው፡ በደንብ መጫን አለበት። እንግዲህ ብዙዎቻችን ችግሩ እዚህ ጋር ነው፡ መንፈስ ቅዱስ አልተቀበልንም፡ ተቆጣጣሪው ሲመጣ፡ ብዙ ያልተሞሉ ቦታዎችን ያገኛል፡ አያችሁ፡ በዚህ ምክንያትም ገና በማሕተም አይዘጋውም።

25 ታላቅ የነገረ መለኮት ምሁር በቀደም ወደ እኔ መጣ፡ በቀደም አይደለም፡ ከሶስት ወይም ከአራት ዓመታት በፊት ነበር፡ “አንድ ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ፡” አለኝ። “አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ፡ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት፡” አለኝ።

“አዎን፡ እውነት ነው፡” አልኩት።

“ከማመን በቀር ሰውዬው ምን ማድረግ ይችላል፡” አለኝ?

“አዎን ማድረግ የሚችለው ማመን ብቻ ነው፡” አልኩት።

26 ከዚያ እንዲህ አለኝ፡ “ታዲያ መንፈስ ቅዱስ ከምትለው ነገር ጋር የት ትደርሳለህ? ” እንደምታውቁት፡ ባፕቲስት ነው። እርሱም አለ—እንዲህ አለ፡

“ከዚህ መንፈስ ቅዱስ ጋር የት ትደርሳለህ? ” እንዲህ አለ፦ “ሰውየው ካመነ! ባመንክበት ደቂቃ፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለሃል።”

እኔም፡ “አይ፡ አይደለም። አሁን፡ ቅዱስ ቃሉን እያጋጨኸው—ነው፡ ቅዱስ ቃላት እርስ በርስ አይጋጭም። አየህ? ጳውሎስ ጠየቃቸው፡ ‘ካመናችሁ **ወዲህ** መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን አላቸው? ’”

እርሱም “እንዴ... ” አለ፡

27 ከዛ እንዲህ አልኩት፡ “እውነት ነው ይህ የእምነት አባት የሆነው አብራሃም... የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል ተሰጠው እግዚአብሔርንም አመነ፡ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት፡ ነገር ግን እምነቱን የመቀበሉ ምልክት እንዲሆን ግን የመገረዝን ማኅተም ሰጠው።”

28 ስለዚህ፡ ገና በመንፈስ ቅዱስ ማሕተም ካላተማችሁ፡ በእርሱ ዘንድ ያላችሁን እምነት ገና አልተቀበላችውም፡ ገና ያልተሞሉ ባዶ ቦታዎች አሏችሁ ማለት ነው። አያችሁ? አዎን፡ ልታምኑ ትችላላችሁ፡ ይሁን እንጂ ብዙ ክፍተቶች ይኖራችኋል። ክፍተቶቻችሁን በደንብ ከተጫኑ በኋላ ግን፡ እስከ ቤዛነት ቀን ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ያትማችኋል። በእርሱ ማመናችሁ የመሰከራችሁት እምነት እንደተቀበለ የእግዚአብሔር ማረጋገጫ ያ ነው።

29 አብራሃም እምነቱን መሰከረ፡ እግዚአብሔርም “እኔ እንተን እንደተቀበልኩህ... ምልክት የሚሆን ነገር አሁን እሰጥሃለሁ፡” አለው። የመገረዝንም ምልክት ሰጠው።

30 አሁን፡ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ ስትቀበሉ እና በእርሱ ስታምኑ እና ህይወታችሁን እንዲያጸዳ ስትጠይቁት፡ ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ ተመልሶ የመንፈስ ቅዱስን ምልክት ሲሰጣችሁ፡ ከዚያ እስከ ቤዛነት ቀናችሁ ድረስ ታትማችኋል።

31 ይህም ፋርጎው፡ ልል ከሆነ... ነገር ሁሉ ተጭኖ ከተዘጋ በኋላ እስከ መዳረሻው ድረስ ታትሞ በሩንም በማሕተም ከተዘጋ በኋላ፡ እንዲህ—ከተላቀቀ፡ ማሕተሙንም ከሰበራችሁት የባቡር መንገድ ኩባንያው ዕድሜ ልክ ሊያሰቀጣችሁ ይችላል። ሊሰበሩ አይገባቸውም። ማንም ሰው ሰቦ እንዳይከፍተው እና በውሰጡ ያለውንም እንዳይመለከት፡ ከውሰጡ ያለውን መርምሮ፡ ጥቂት ነገሮችን እንዳያሰወግድ፡ ሌሎች ነገሮችንም እንዳይጨምርበት፡ እስከ መዳረሻው ድረስ በማሕተም ይዘጋል። አይቻልም፡ በጭራሽ!

32 **ይህች** ቤተ ክርስትያን፡ ማለት፡ አስተምህሮውን፡ “**ይህ** ጥሩ አይደለም፡ **ያኛው** ጥሩ አይደለም ትላለች።” እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሲሰጣችሁ፡ ነገር ሁሉ ያርፋል! የቆማችሁበትን ታውቁታላችሁ፡ የሆነውን ታውቁታላችሁ፡ እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ፡ እስከ ምድር ጉዞአችሁ ፍጻሜ ድረስ ታትማችኋል። ኦህ፡ ማይ! እምነት እንዲኖረው እና በእግዚአብሔር እንዲታመን፡ በመንፈስ ቅዱስ እና በኃይሉ ችሎት እንዲነሣ ያደርገዋል።

33 አሁን፡ መንፈስ ቅዱስ ያልተቀበሉ እነዚያ ደናግል፡ (ታስታውሳላችሁ? ) የጎደላቸው ብቸኛው ነገር የመቅረዞቻቸው ዘይት ብቻ ነው። ልክ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ **ዘይት** “የመንፈስ ቅዱስ” ምሳሌ እንደሆነ ያስተምራል፡ የመንፈስ ቅዱስ ምልክት ስለሆነም፡ ድውዮችን እና ሌሎችን፡ በዘይት

የምንቀባው ስለዚህ ነው። አሁን፡ ስለዚህ—መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ላይ ካልወረደ፡ ገና አላገኙትም ማለት ነዋ። እርሱ ሲመጣ፡ እንዲህ ይሏቸዋል... ማለት፡ ዘይት ለያዙት ደናግል፡ እንዲህ ይላቸዋል...

34 አያችሁ፡ በቤተ ክርስትያን ዘመን ውስጥ፡ ይኖሩ የነበሩ ናቸው፡ በዚያ ይኖሩ የነበሩ አንዳንዶች መልካም ሰዎች ሲሆኑ ከኮከቡ ብርሃን ዘንድ ግን አልነበሩም፡ ማለቴ፡ ወደ ዘይቱ ውስጥ ከጠለቀው ክር ጋር አልነበሩም። አያችሁ፡ ከውጭ ነበር። ወጥቷል፡ እነርሱ ግን ራሳቸውን ለይተዋል። ጳውሎስ፡ በሱ ዘመን ሲናገር "እምነት ስላልነበራቸው፡ እራሳቸውን ለዩ፡" አለ። አያችሁ፡ ከነሱ ተለዩ፡ "ከእኛ ወገን ስላልነበሩ ከእኛ ወጡ።" አሁን፡ በመጀመሪያ ከኤፌሶን ዘመን የጀመረው እስከ ዛሬ ዘመን ወደዚህ ዘመን ድረስ ደርሷል። ተመሳሳይ ነገር፡ እያንዳንዱ ዘመናት፡ ወደ እነዚህ ዘመናት ሲደረቡ የሚሆነው ነገር ምንድነው። ከትንሽ ጊዜ በኋላ በጥልቀት እንገባበታለን።

35 አሁን አስተውሉ፡ ምንም እንኳን፡ ድንግል ብትሆንም፡ ለቅሶ፡ ዋይታና፡ ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ገብታለች።

36 ውድ ወዳጄ ሆይ፡ ይህን ብቻ ልበል፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ እዚህ ቤተ ክርስቲያን፡ እዚህ ስመጣ፡ ወይም በአገሪቱ ውስጥ በሆነ ሰፍራ ሰሄድ፡ የፈውስ አገልግሎት አደርጋለሁ ለበሽተኞችም እጸልያለሁ። ጊዜው ግን ይህ ነው፡ ህሊናችሁን ኪሳችሁ ውስጥ አርጉ ብዬ እየነገርኳችሁ የነበረው ጊዜ፡ ይህ ነበር። እንደው አሁን—እርስ በርሳችን ሐቀኞች እና እውነተኞች ሆነን መምጣት እንፈልጋለን፡ ምክንያቱ በመጨረሻው ዘመን ነንና። አዎን!

37 እናንተም፡ የተወደዳችሁ ናዝሪኖች እና ፒሊግሪም ሆሊነሶች ቅድስና ብላችሁ የሳታችሁበት ነገር ይህ ነው። አያችሁ? አሁን፡ የአስቆሮቱ ይሁዳ በተመሳሳይ ሁኔታ በዚያ ደረጃ ይኖር እንደነበረ አስተዋላችሁ? ይሁዳ ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝነት አምኖት፡ አዳኝ አድርጎ ተቀብሎታል። እርሱም ተቀድሶ ነበር። ኢየሱስ፡ "አባት ሆይ በእውነት ቀድሳቸው፡ ቃልህ እውነት ነውና፡" ብሎ በጸለየ ጊዜ፡ በዮሐንስ 17፡17፣ ላይ አብሮ ተቀድሷል። እርሱም ቃል ነበር። በጣም ጥሩ!

38 በማቴዎስ ወንጌል 10 ድውያንን የመፈወስ፡ ሙታንን የማስነሳት፡ አጋንንትን የማስወጣት ስልጣን ተሰጣቸው። ወደ አገሪቱ ዳርቻዎች ሁሉ ወጥተው—አጋንንት ገሰጸዋል፡ በእልልታም እየጮሁ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ተመለሱ። ኢየሱስም አላቸው፡ "አጋንንት ስለ ተገዙላችሁ ደስ አይበላችሁ፡ ነገር ግን ስማችሁ በሕይወት መጽሐፍ ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።" ልክ ነው? ይሁዳም ከእነርሱ ጋር ነበረ፡ ይሁዳ ከእነርሱ ጋር ነበረ፡ ይህ የሆነው ግን ኢየሱስ ከመሰቀሉ ከአንድ አመት ከሰድስት ወር በፊት ነው።

39 አሁን ግን ይሁዳ፡ መንፈስ ቅዱስ እና ልዩ ልዩ ነገሮች ወደሚቀበልበት፡ የበዓለ እምሣ ቀን በደረሰ ጊዜ ግን፡ ከለሩን ማሳየት ጀመረ። ኢየሱስን—ካደ፡ ከሃዲ ሆነበት። ስለዚህ ያ መንፈስም፡ በሉተር፡ በዌስሊ በኩል አልፎ ወደዚህ በመድረስ፡ ያቺን ቤተ ክርስትያንን ድንግል ወደ ሆነ ህይወት (እይታችሁ የማታውቁት ንጹህ፡ የጸዳ፡ ቅዱስ፡ መልካም፡ ምርጥ ህዝብ) በማምጣት እስከ ቅድስና ድረስ አደረሳት፡ በልሳን ወደ መናገር እና መንፈስ ቅዱስ ወደ መቀበል... ሲደርሱ ግን፡ ናዝሪኖች፡ ፒልግሪም ሆሊነሶች፡ ፍሪ ሜቶዲስቶች

ሁሉ፡ “ያ’ማ ሰይጣን ነው፡” ይሉታል። ያኔ መንፈስ ቅዱስን በሰደባችሁ ጊዜ ወዲያው እራሳችሁን ለዘለአለም ታስኮንናላችሁ፡ “ምክንያቱ በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፡ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገር ሁሉ ግን ለዘላለም አይሰረይለትም።”

40 አስታውሱ፡ ደቀ መዝሙር ሁሉ በልሳን ተናገሩ። ኢየሱስ ክርስቶስም በመስቀል ላይ፡ ልሳን እየተናገረ ሞተ። ኧህ-ሃም። ስለዚህ እዚህ ከእነርሱ ጋር አብራችሁ መሆን ካልቻላችሁ፡ እዚህ ከእነሱ ጋር ወዳጅ መሆን ካልቻላችሁ፡ በእዚያስ ታዲያ? ለእነርሱ’ኮ… ዲያብሎስ አለ ካሉ፡ እነሱ ናቸው። ስለዚህ እሱም ከለሩን ያሳየበት ሰፍራ በዚያ እንደነበረ ታያላችሁን? ያቺ ድንግል፡ እንደሌሎቹ የጸዳች ሕይወት፡ እነሆ በንጽሕና መጣች። እነሆ በቅድስና የሚያምኑትን የጥንቱ-አይነት ናዝሪን፡ ፒሊግሪም ሆሊነስ አብያተ ክርስትያኖችን፡ ለምሳሌ ብወሰድ፡ ጣታችሁን በእነሱ መቀሰር እስከማትችሉ ድረስ፡ የጸዱ ናቸው። ሁላችንም እንደዛ ብንኖር ጥሩ ነገር ነው። ልክ ነው፡ መኖር አለባችሁ።

41 አሁን፡ ስለ ጴንጤቆስጤዎች አብዝተን እንደ አስመሳይ እንቆጥራቸዋለን። እውነት ነው። ነገር ግን የውሸት ዶላር ስታዩ፡ ከትክክለኛው፡ ከእውነተኛው እንደተሰራ ትረዳላችሁ። ትክክል ነው። እና እውነተኛ መንፈስ ቅዱስም—አለ፡ በልሳኖች የሚናገር እና ምልክትና ድንቅ የሚያደርግ ነው፡ ይህም ከበዓለ ሃምሳ ቀን ጀምሮ የነበረ ነው። ስለዚህ አስመሳዮች መኖራቸው ግዴታ ነው። ትክክለኛዋ ሴት ደምቃ ለመታየት፡ ክፉ እና ከንቱ የሆነች ሴት ልትኖር ይገባል። የፀሐይ ብርሃን የከበረ መሆኑን ለማሳየት፡ ሌሊት፡ ጥቁር ጨለማ ሊኖረን ይገባል። ትክክል ነው። መልካም ጤንነት ለማጣጣም፡ መታመም አለባችሁ። የአንበሰ እና የጎፈር ሕግ ነው፡ ጊዜ እስካለ ድረስም፡ ይህ—ሁልጊዜ አለ፡ ወደፊትም ይኖራል።

አሁን፡ ስለዚህ፡ ቤተ ክርስቲያን እራሷን ከፍ ያደረገችበት ሰፍራ አለ።

42 ኢየሱስ፡ “በመጨረሻው ዘመን፡” በማቴዎስ 24 እንዲህ ይሆናል አላለምን፡- “የሚቻላቸው ቢሆንስ ኖሮ የተመረጡትን እስኪያስቱ ድረስ ሁለቱ መንፈሶች እጅግ ይመሳሰላሉ አላለምን”? ኧሃ-ሃህ። ምድር ከተፈጠረ ጀምሮ የተመረጠው ሁሉ ግን የዘላለም ሕይወት አለው። የዘላለም ሕይወት፡ እሱን ማስወገድ አትችሉም። እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው፡ እግዚአብሔር አለመኖር እንደማይቻለው ሁሉ እናንተም አለመኖር አትችሉም። ትክክል ነው። የእግዚአብሔር አካል ስለሆናችሁ፡ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጅ ናችሁ፡ ሕይወታችሁ ተቀይሯል የእግዚአብሔር አካል ናችሁ፡ የዘላለም ሕይወት አላችሁ። ኦህ፡ እኔ እወደዋለሁ። እናንተስ?

43 አሁን፡ አንድ ሰው እዚህ አንድ ማስታወሻ አቀብሎኛል፡ ትንሽ ጥያቄ ናት። መልስ ለመስጠት አሁን ብዙ ጊዜ አንወሰድም። አስታውሱ፡ ዘወትር ጥያቄ ስታስቀምጡልኝ፡ በቻልኩት መጠን ለመመለስ እሞክራለሁ። ይሄኛው ግን ወሳኝ ጥያቄ ነው፡

> **አንድ ሰው ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መመስከራቸው፡ ወይም መዘመራቸው፡ ወይም መልእክትን በልሳን መስጠታቸው፡ መልእክቶች፡ ወይም ትንቢት መተርጎም፡ የሚችሉ መሆናቸው ወይስ አለመሆናቸው ማወቅ ፈልጓል።**

44 አይ፡ የስርዓቱን አካሄዱን ጠብቆ፡ በስፍራው የተገለጠ እስከሆነ ድረስ… ስህተት አይደለም። አያችሁ? ቤተ ክርስትያን በአካሄድ የታነጸች ናት፡ ይህን የምንጠቀምበት… እውነተኛ፡ እና ትክክለኛ መንገድ ልሳን በሚናገሩ ሰዎች፡ መልእክታቸው ከፑልፒት ከሚመጣው መልእክት በፊት መሰጠት አለበት፡ በሰብከት ጊዜ መሆን የለበትም፡ ምክንያቱ ጳውሎስ እንደተናገረ፡ መንፈስ ቅዱስ በአንድ ጊዜ ከአንድ ቦታ ብቻ ይንቀሳቀሳልና። ሴቶች ግን ሰባኪ ከመሆን በቀር፡ የትንቢት እና የልሳን እና ልሳን የመተርጎም ስጦታ፡ ልዩ ልዩ ነገር ተሰጥቷቸዋል። ሰባኪዎች መሆን የለባቸውም። በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንዳይሰብኩ ተከልክለዋል፡ ልክ ነው፡ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ስፍራ መያዝ፡ ወይም መሰበክ አይችሉም። ስጦታዎች በተመለከተ ግን፡ ስጦታዎች ሁሉ አሏቸው፡ መልእክቷ በስፍራው እንዳይሰማ የሚከለክላት ሕግ የለም እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ 12 መሠረት፡ አንድ ወይም ዘጠኝ መንፈሳዊ ጸጋዎች ሊኖራት ይችላልና። አያችሁ፡ እያንዳንዱ መልእክት ጊዜውን መጠበቅ አለበት።

45 "በልሳን የሚናገር ቢኖር፡ ተርጓሚ ግን ከሌለ፡ ተርጓሚ እስኪመጣ ድረስ ዝም ይበል።" አያችሁ? እነዚያን መልእክቶች፡ ብዙ ጊዜ፡ ከጉባኤው በፊት መሰጠት ያለባቸው ናቸው፡ ከዚያም ነብዩ፡ ወይም፡ ሰባኪው፡ እርሱም የአዲስ ኪዳን ነቢይ፡ ማለት ሰባኪው፡ በወጣ ጊዜ እግዚአብሔር በእሱ ውስጥ መንቀሳቀስ ይጀምራል፡ አያችሁ፡ እሱ ሲጨርስ መልእክቶች ይጀምራሉ፡ ሌላም፡ ከዚያ በፊት፡ ሁልጊዜም አካሄድ መኖር አለበት፡ ሁልጊዜ፡ ይሁን እንጂ ሴትም መብት አላት።

46 ቀጣዩ፡ ለዚህ መልስ ለመስጠት፡ ትንሽ ጊዜ መውሰድ እፈልጋለሁ፡ ርእሱን አነባለሁ፡

> **ከአንድ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎሙ ሦስት እምነቶች ጀመሩ**። ጥቅምት 15፡ ዋሺንግተን። በቡድን ሆነው የሚሰሩ የካቶሊክ፡ የፕሮቴስታንት እና የአይሁድ ምሁራን አዲስ የጋራ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ጀምረዋል ለረጅም-ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው ቀኖና መጽሐፍ ቅዱስ ሊሆን ይችላል።

47 እዚህ ውስጥ አሳቤን ከመስጠቴ በፊት አንዳንድ ተጨማሪ ነገሮችን ማጥናት እፈልጋለሁ። በሌላ አባባል፡ የምንናገረው ነገር በትክክል ማየት ትችላላችሁ፡ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ዘመን ይሆናሉ ያላቸውን ነገሮች፡ ይህም እነዚህ አካሎች አንድ ላይ ሆነው ለአውሬው ምስል እንደሚሠሩ ነው። በትክክል። ሞክረውታል፡ ሠርተውበታልም፡ በተለይ ያንን ማቅረብ የሚችሉበትን ምርጥ እድል አግኝተዋል፡ ምክንያቱ ሁሉ በእጃቸው ላይ ነው። እነዚህን ትንቢታዊ መልእክቶች ያመጣሁበት ምክንያት ይህ ነው፡ ምክንያቱም ወቅታዊ መሆናቸውን አስቤአለሁና።

48 የምሽቱ ተመልሶ የሚመጣ ሰው የሚኖር ከሆነም፡ ቀደም ብለን ጀምረን ቀደም ብለን ለመጨረስ እንሞክራለን። ርዕስ ጉዳዩን ካልጨረስኩት፡ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት እናገራለሁ። ዛሬ ማታ ከ9ኛው ቁጥር፡ እስከ 19ኛውን እስከ 20ኛው ቁጥር ካላለፍን፡ ጠዋት በአስር ሰዓት እንጀምራለን። እንዴት እንደምንስማማ፡ በአገልግሎቱ መዝጊያ ላይ እናሳውቃችኋለን።

49 ነገ ማታ፡ ኤፌሶን ቤተ ክርስትያን እንጀምራለን፡ ይህም የሰባቱ ምሽቶች ጅማሬ ይሆናል፡ ኤፌሶን፡ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ሰምርኔስም፡ እና ጴርጋሞስ፡ ትያጥሮንም፡ እና ሰርዴስ፡ እና ፊላዴልፊያ፡ እና ሎዶቅያ፡ በሚቀጥለው እሁድ።

50 እና እነዚህን ድንቅ ጌጦች በየ መንገዱ መነሰነሳቸው እያወቅኩ፡ ጊዜው እስኪደርስ ድረስ እጆቼን አጣምሬ መቀመጥ ይከብዳል። መንፈሱ በህዝቡ ዘንድ እየተሞሉ መሆናቸውን እየተሰማኝ፡ እኔም በአይኔ እያየሁት፡ በቃ በኃይል እየዘለልኩ—ስለነዚህ አንድ ነገር እንድናገር ውሰጤ ይገፋፋኛል፡ ነገር ግን ረጋ ብዬ በየዘመናቸው እና በየወቅታቸው ላይ ማስቀመጥ ይገባኛል። ስለዚህ ማታ መምጣት ካልቻላችሁ፡ ካሴቱን አግኙት ወይም በሌላ መንገድ መስማታችሁን አረጋግጡ፡ ምክንያቱም በሁሉም ቦታ እንዲሰማ እፈልጋለሁ። ይህንንም ያደረኩት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ስለተሰማኝ ነው፡ ይህን እያደረግኩት ያለሁበት ብቸኛው ምክንያት ያ ነው። እና እኔም፡ ቤተክርስቲያንን እንደሚረዳ ባላሰብ ኖሮ... ያውም በዚህ ቀን፡ እንደዚህ አይነት ጉባኤዎች የማናደርግበት ዘመን እንደሚመጣ፡ አትርሱ፡ ስለዚህ መስራት የምትችሉበት ጊዜ እያለላችሁ አሁን አድርጉት። አያችሁ፡ ይህን በምን ሰዓት መከልከል እንደሚጀምሩ፡ አሁን አናውቀውም።

51 እንዲህም ይሆናል በአብያተ ክርስቲያናት ኮንፌደሬሽን መካከል ከላይ ጀምሮ፡ በአብያተ ክርስትያናት ሁሉ ኅብረት ይፈጠርና አንድ ላይ ይሆናሉ፡ አሁንም እንኳ በ U.N. ህንጻው ውስጥ እያንዳንዳቸው የሐይማኖት ተቋም ገብተውበታል። ያኔ እናንተም የአንዳቸው አባል ትሆናላችሁ ወይም ያባርሯችኋል። ከለሮቻችን የምናሳይበት ማወቃችንንም እርግጠኛ የምንሆንበት፡ ግምት ሳይሆን፡ የቆምንበት ሰፍራ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** መሆኑን የምናረጋግጥበት ጊዜ ያኔ ነው። ትንሿ ቤተክርስትያን ሁል ጊዜም ቢሆን በተናቁት መካከል ዘንድ ናት፡ በጣም አነስተኛ መንጋ... ልክ፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መክፈያ—ትንሿ ክር ናቸው፡ ሁልጊዜ ግን ቤተ ክርስትያን ናቸው። እኛም ይህን መርሳት የለብንም።

52 አሁን እንደገና ከማንበባችን በፊት ትንሽ አስተያየት ልስጥ። ዛሬ ጠዋት የኢየሱስ ክርስቶስን ልዑል አምላክነት መገለጥ ተቀብለናል፡ ዛሬ ጠዋት እንደ ልዑል አምላክነቱ፡ እንደ ታላቁ **እኔ ነኝ** (**ነበርኩ** ሳይሆን ወይም ወደፊት **እኖራለሁ** ሳይሆን)፡ ሁልጊዜ፡ እኔ ነኝ መሆኑ እግዚአብሔር ለእኛ ገለጠው። እናም በዚህ በራእይ ምዕራፍ 1 መገለጥ ላይ፡ አንድ ነገር እናስተውላለን... መገለጡ ምንድን ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እዚህ ውስጥ ራሱን የገለጠው የመጀመሪያው ነገር ምንድን ነው? የሰማይ አምላክ መሆኑን። አንድ አምላክ እንጂ፡ ሦስትነት አምላክ አለመሆኑ። አንድ አምላክ፡ በራእይ መጀመሪያው ላይ እራሱን የገለጠበት መንገድ ያ ነው። ስህተትም እንዳይሆን በ1ኛው ምዕራፍ አራት ጊዜ ተናግሯል። መጀመሪያ ማወቅ ያለባችሁ ነገር፡ አምላክ እንጂ፡ እርሱ ነቢይ፡ ወይም—ትንሹ እግዚአብሔር አይደለም፡ ሁለተኛው እግዚአብሔር አይደለም፡ እግዚአብሔር ነው! እግዚአብሔር ነው። ስለዚም አሁን መገለጡ ተሰጥቶናልና፡ አሁን ዛሬ ምሽትም የሰባት መአዝናዊ ሰብእናው እስክንደርስበት ድረስ በዚያው እንቀጥልበታለን።

53 ኦህ፡ እንደው እነዚህን ቃላት ስናስተምር እግዚአብሔር ይርዳን። ከታሪካዊ ዳራ እይታ አንፃር—አ—አጥንቻለሁ፡ የመንፈስ ምሪት እስክቀበል ድረስ ግን እዚህ ፑልቢት ላይ እጠብቀዋለሁ። ምክንያቱም በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ሰፍራ እንደተሰበሰብን ይሰማኛልና፡ መንፈሳችሁም፡ ማለት በእናንተ ዘንድ ያለውን ክፋያችሁ፡ የእሳት ፍንጣቂያችሁ (መንፈስ ቅዱስ) በሌላው ላይ ይመጣል፡ ከሌሎች ወደ ሌሎች እያለፈም፡ ታላቁን የእግዚአብሔር አካል በማቀጣጠል ነበልባል ያደርገዋል፡ መገለጦችም በዚያ ውስጥ ናቸው...

54 አሁን፡ እየተነጋገርን ባለነው፡ ይህ ጥያቄ ቀረበልኝ፡ "ስለ ሴቶች... እና የመሳሰሉት?" በመጀመሪያም ቤተ ክርስትያኒቱን ሁከት ውስጥ የከተታት ነገር ይህ ነው፡ ክብርን ሁሉ ከጉባኤው ወስደው ፑልፒት ላይ አደረጉት። እግዚአብሔር ግን የጉባኤው አምላክ ነው። በሰው ሁሉ ውስጥ ይሰራል፡ ሊገባበት በሚችለው በእያንዳንዱ ልብ ውስጥ ይኖራል። ሰጦታ ያላቸውን ሰዎች ፈልጎ በእነሱ በኩል ይሰራል። ይህም፡ ዲያብሎስ በአንድ ነገር ካልነደፋቸው ነው፡ እርሱ ግዙፍ የሆነ ተራ ሰብሰባ በማድረግ ሰዎች እንዲጠፉ ያደርጋልና። ጳውሎስ እንደተናገረው፡ "በጉባኤው ጊዜ፡ ሁላችሁ በልሳኖች ብትናገሩ፡ ያልተማረ ሰው ገብቶ፡ እናንተ፡ 'ሞኞች! አብዳችኋል!' አይላችሁምን? በልሳኖች የሚናገር ሰው፡ **ይህም** ያም፡ **ሌላውም** በሙሉ፡ ከአካሄድ ውጪ ቢሆን አይሰራም። ግን፡" እንዲህ አላቸው፡ "አንድ ግን በትንቢት ቢናገር፡ የተሰወረ የልብ ምስጢር ቢገልጥ፡ 'በእውነት እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነው' አይሉምን።" እንዲሁም አንዱ ቤተ ክርስትያኒቱንም ለማነጽ፡ በመገለጥ ልሳን ቢናገር ትርጓሜውንም ቢሰጥ፡ ቤተ ክርስትያን በዚህ ትታነጻለች። መነገር ያለበት ነገር እግዚአብሔር እኛ በማንረዳው ቋንቋ ይቃትታል ለሌላኛው ሰው ይሰጠዋል በሌላም እንዲተረጎም ያደርገዋል፡ ከዚያ ልክ እንደተነገረ ነገሮች በትክክል ይፈጸማሉ፡ ያ ማለት የጌታ መንፈስ በመካከላችሁ አለ ማለት ነው። እና፡ ኦህ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ለዚያ እንትጋ፡ እሳት—መንደዱ እንዲቀጥል እናድርግ።

55 አሁን፡ ታላቁን የመጽሐፍ ቅዱስ... ቀኖና ከመክፈታችን በፊት፡ እየጸለይን ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ተነስተን አቅጣጫ ብንቀይር አይሻልም ወይ ብዬ አስባለሁ።

56 ጌታ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የማይሳሳት የሰማይ አምላክ ሆኖ ዳግመኛም (ከሺ ዘጠኝ መቶ ዓመታት በኋላ) ለእኛ ያቀረብከው ኃያል አምላክ፡ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ከኛ ጋር ስለመገኘቱ እና ስለ መሆኑ እናመሰግናለን። አለም ምን ማድረግ እንዳለበት በማያውቅበት በዚህ ግራ መጋባት ጊዜ ውስጥ መኖራችን ሰናውቅ ደስ ይለናል፡ ምሽጎቻቸውን እያጠናከሩ፡ መሬት ውስጥ ጉድጓዶችን ቢቆፍሩም፡ ጌታ ሆይ፡ ከእግዚአብሔር ቁጣ ግን፡ መደበቅ አይችሉም። ጌታ ሆይ፡ የዚህን ሁሉ መድኃኒት ግን—አንድ መድኃኒት ናት፡ እኛም በመቀበላችን ደስተኞች ነን፡ "ደሙን ባየሁ ጊዜ አልፋችኋለሁ።" አቤቱ፡ ዛሬ ምሽት ከእግዚአብሔር በግ ደም ከሊቀ ካህናቱ ሁሉን-ከሚችለው ጥበቃው ስለ ኃጢአታችን ንሰሃ፡ ይማልድልን ዘንድ፡ ዛሬ ማታ በአርያም ሰለመሆኑ እጅግ ደስ ይለናል። ዛሬ ማታ እንደበተ ርቱዕ የሆነውን፡ ታላቁ መንፈስ ቅዱስ ጋር፡ ታላቁ ቅባት-ቀቢው፡ እና ታላቁ የህይወት-ሰጪ፡ ከእኛ ጋር በመገኘቱ እጅግ ያኮራናል።

57 አሁንም፡ ጌታ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ማታ በዚህ ጣሪያ ሥር እነዚህን ሰዎች በአንድነት እንደጠራኋቸው፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን ወይም እንደ ተወሰነ ክፍል ሆነን እዚህ ተሰብሰበናል፡ መሰብሰባችን ግን በዚህ ቤተ ክርስትያን ስም ወይም በአንድ ግለሰብ ስም ሳይሆን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። ስለዚህም አካሉን እና አሳቡን ሁሉ አልፎ የሚቆጣጠረው፡ ያ መንፈስ ዛሬ ማታ ወደ እኛ ይምጣ፡ መጥቶም ቃሉ ይሰበከን ቃሉንም ይተርጉምልን፡ እርሱንም ስንጠብቅ ለተራበው ልባችን ሰጠን። በሰሙ እና ለክብሩ እንለምናለንና። አሜን። (አረፍ አረፍ በሉ።)

58 አሁን መጽሐፍ ቅዱሶቻችሁን ለያዛችሁ፡ ራዕይ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 9 ትከፍታላችሁ፡ እስክርቢቶ እና ወረቀት ያዙና፡ በሂደት ጥቂት ቀኖች እና ሌሎች ነገሮች አጽፋችኋለሁ።

59 አሁን፡ የጠዋቱ በአብዛኛው... እግዚአብሔር በክርስቶስ ላይ እንደተገለጠ፡ የሚያሳይ መገለጥ፡ በአምላክነቱ ላይ፡ መሰረት የሚጥል ስብከት አይነት ነበር። ሰንቶቻችሁ አመናችሁ? እግዚአብሔር በክርስቶስ ተገለጠ፡ ጆሆቫ በክርስቶስ ተገለጠ። አሁንስ እግዚአብሔር በማን ይገለጣል? በቤተ ክርስትያኑ፡ በእኛ፡ በህዝቡ ውስጥ ይገለጣል። ያው መንፈስ፡ ያው ሰራ፡ ያው ትረካ፡ ያው ፍቅር፡ ያው ምሕረት፡ ያው ትዕግሥት፡ የውሃት፡ ትዕግሥት፡ ሰላም፡ ምሕረት፡ በክርስቶስ ዘንድ የነበረ ሁሉ አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። አሁንም፡ ይህንን አስታውሱ፡ የእግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ አፈሰሰው (የመለኮቱ ሙላት በሰጋው እርሱ ነበርና)፡ የክርስቶስ ሙላት ሁሉ በቤተ ክርስትያን ውስጥ አፈሰሰው። እግዚአብሔር ከእኛ በላይ፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር፡ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ነው። የእግዚአብሔር ሦስታዊ ህብረት፡ እግዚአብሔር በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ በሦስት የተለያዩ ምግባሮች መተረኩ ነው።

60 የዚህ መገለጥም ሦስት አማልክት አለመሆኑን፡ እና በሦስት እንዳልተቆራረጠ የሚያስረዳ ነው። በአባትነት ዘመኑ አምላክ በነበረ ጊዜ ግን፡ አንዱ አምላክ፡ በልጅነት ዘመኑም አምላክ ነው፡ በመንፈስ ቅዱስ ዘመኑም አምላክ ሲሆን፡ አንዱ አምላክ ነው። ሦስት የተለያዩ አይደለም፡ ሦስት አካላት አይደለም፡ ባለ ሦስት ሰብእና አይደለም። ባለ አንድ ሰብእና፡ አንድ አካል ነው። አካል ሳትሆኑ ሰብዕና ሊኖራችሁ አይችልም። አንዳንድ ሰዎች "እሱ ሶስት አካላት አይደለም፡ ነገር ግን ባለ ሶስት ሰብእና ነው፡" ይላሉ። ያንን መስነጣጠቅ አይቻልም፡ ሰብእና ካለው፡ አካል ነው፡ ምክንያቱ ሰብእና ለመኖር አካል መኖሩ ግድ ነው። ስለዚህ እርሱ ባለ አንድ ሰብእና፡ አንድ አካል ነው፡ ትላንትም፡ ዛሬም፡ ለዘላለም ያው የሆነ፡ አልፋ፡ ኦሜጋ፡ የነበረ፡ ያለው፡ የሚመጣው እርሱ ነው። አቤት፡ እርሱ **ሁሉ** በሁሉ ነው። ይህን ወደድኩት።

61 ተፈጥሮውን፡ ሕይወቱን፡ ሥራውን ተመልከቱት። ያኔ በዘመኑ እንደነበረው፡ አሁንም በዚህ ቤተ ክርስትያን ውስጥ መተረክ አለበት። (ይህን የምናገረው በጥላቻ አይደለም፡ እግዚአብሔር ያውቃል።) እዚህ ብቻ ሳይሆን ግን፡ በመላው ዓለም። እንዲህ መሆኑም ያሰደስተኛል። ያ መንፈስ ከእኛ ጋር እየሰራ እርሱ እዚህ መሆኑ እያሳየን በውስጣችን ሰላለ፡ የቆምንበት ሰፍራ በደንብ እናውቃለን። እኛ አይደለንም፡ እሱ ነው፡ እነዚህን ነገሮች ማድረግ አንችልም፡

እግዚአብሔር ነው። ከዚህ በተጨማሪ፡ በሳይንሱ አለም፡ ምስሉ እንዲነሳ ፈቅዷል። ከእኛ ጋር፡ በእኛ፡ በዙርያችን፡ ከእኛ በላይ፡ በእኛ በኩል፡ በውስጣችን እና በውጫችን ይሰራል። አቤት፡ እንዴት ድንቅ ነው!

62 እንዲት ዝማሬ ይዘመሩ ነበር፡

> በእሳት ቊጥቋጦ ውስጥ ሙሴን የተናጋርኩ **እኔ ነኝ**፡
> የአብርሃም አምላክ፡ ብሩህ የንጋት ኮከብ **እኔ ነኝ**።
> የሳሮን ጽጌሬዳ፡ ኦህ፡ **እኔ ነኝ** ከወዴት መጣ ትሉኛላችሁ?
> አባቴንስ ታውቃላችሁን፡ ወይስ ሰሙ ማን ነው?
>
> ኧረ፡ ማን እንደ ሆንሁ፡ ከወዴትስ እንደመጣሁ ትላላችሁ፡
> አባቴንስ ታውቃላችሁን፡ ወይስ ሰሙ ማን ነው?
> አልፋ፡ ኦሜጋ፡ ከመጨረሻው መጀመሪያ **እኔ ነኝ**፡
> ፍጥረት በሙሉ **እኔ ነኝ**፡ ስሜም ኢየሱስ ነው።

63 አቤት፡ መገለጡ፡ እንዴት ድንቅ ነው! አሁን፡ አስታውሱ፡ በስነ መለኮት ሊቃውንት ልታገኙት አትችሉም፡ በዚህ መንገድ አይመጣም። የሚመጣው በመገለጥ ብቻ ነው። የውሃን ጥምቀት፡ በኢየሱስ ክርስቶስን ስም መሆኑ የምትረዱት፡ በመገለጥ ብቻ ነው። ኢየሱስ እና እግዚአብሔር አንድ አካል መሆኑ የምትረዱት በመገለጥ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ በመገለጥ ላይ የተገነባ ነው። መላ ቤተ ክርስቲያን በመገለጥ ላይ የተገነባች ናት። ማቴዎስ 17 እንዲህ ይላል፡ "እላችኋለሁና፡ 'በዚህ ዓለት ላይ (በመንፈሳዊው መገለጥ ላይ) ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።'" በየትኛውም ቦታ ቢሆን፡ ከታሪክም ይሁን፡ ወይም ከቅዱሳት መጻሕፍትን፡ እስከ ማርቲን ሉተር ዘመን ድረስ ከካቶሊክ ቤተክርስትያን በቀር "በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ" ስም የተጠመቀ ሰው መኖሩን የሚያውቅ አንድ ሰው ካለ እንዲያሳየን ይቅረብ። በመቀጠል የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያንም፡ እንዲሁ...

64 በደንብ አዳምጡ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ዘመናት በምንገባበት ጊዜ፡ ክፋት ሁሉ፡ በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ክፋት ሁሉ፡ ቀጥላ ወዳለች ገባ። በመጨረሻው ዘመን በፍፁም ክህደት እስከሚያበቃ ድረስ እንዲሁ እየተሸጋገረ መጣ። የተጀመሩት እያንዳንዳቸው ኢዝሞች፡ ክፋቶች ሁሉ በእያንዳንድ ቤተ ክርስቲያን እየተወራረሱ ወደፊት ይቀጥላሉ። ልክ እንደ ኦሪት ዘፍጥረት፡ ግንዱ፡ ማደግ እንደ ጀመረ፡ በቤተ ክርስቲያን በኩል መንገዱን ሸምኖ በመጨረሻው ዘመን ተገለጠ። መጽሐፍ ቅዱስ "ከዚያች ቀን ያመለጡ ብፁዓን ናቸው፡" ማለቱ አይደንቅም። አዎን፡ ወዳጄ፡ ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ያመለጠ።

65 እናንተም እግዚአብሔርን ለምኑት... ስለ መገለጦቹ እየተናገርን ባለነው ጊዜ፡ መገለጥ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት። ሊታወቅ የሚችለው በመገለጥ ብቻ ነውና፡ እናንተም መዳን የምትችሉት በመገለጥ ብቻ ነው። አእምሮአዊ በሆነ ብቃት፡ እውቀቱ ሊኖራችሁ ይችላል፡ ለእናንተ እስኪገለጥ ድረስ ግን አትድኑም። "በመንፈስ ካልሆነ በቀር፡ ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ሊለው ማንም አይችልም።" ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። መንፈስ ቅዱስን እስካልተቀበለ ድረስ ማንም ሰው ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ሊለው አይችልም። ምናልባት "ፓስተር እንዳለው፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፡" ሊል ይችላል። እነዚያም እውነቶች ናቸው።

“ቤተ ክርስትያን እንዳለችው።” እውነት ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ **ለአንተ** እስኪገለጥልህ፡ እና በአንተ ውስጥ እስኪሆን ድረስ **አንተም** አታውቀውም። “በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ከሆነ በቀር፡ ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ማንም አይልም።” በእውቀት አይቻልም፡ በአእምሮም አይቻልም።

66 ቀን ከማታ እንደሚለይ ልዩነታቸው ሰፊ ሆኖ ሳለ... ለአይሁዶች፡ ለካቶሊኮች፡ ለፕሮቴስታንቶች፡ የሚመች መጽሐፍ ቅዱስ፡ ጨምቀው ለመስራት እንዴት ይጥራሉ። አይሁዳውያን ከዚያ የተሻለ ያውቃሉ ብዬ አስብ ነበር፡ ምናልባት ሰዓቱ የደረሰና፡ ሁሉም ወደ ታላቅ ስህተት የመሄጃው ሰዓት የመጣ ይመስለኛል። ስለዚህ፡ ሌላውም ሁሉም ነገር አስታውሱ፡ እኛ ይህን ማስቆም አንችልም፡ ማድረግ የምንችለው ብቸኛው ነገር ብርሃኑን ማዳረስ፡ ምናልባት እንደ ሰማዕት እራሳችንን ሰጥተን መቀጠል ነው፡ ማድረግ የምንችለው መንገድ ይህ ብቻ ነው። ብዙዎች ግን ያንን ማድረጋቸው አይቀርም። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የተቀናበረበት መንገድ እና እኛም የምንገባባቸው ነገሮች እነዚህ ናቸው። ካልነቃሁበት፡ እኔም እገባበታለሁ።

67 አሁን፡ ከሁሉ በፊት የራዕይ መጽሐፍ የሚጀምረው፡ እርሱ ማን እንደሆነ በሚገልጥ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ይጀምራል። አሁን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ሁላችንም ይህን እናውቃለን። ሰንቶች ታምናላችሁ? “አሜን፡” ትላላችሁ። [ጉባኤው፡ “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ሁሉን ቻይ አምላክ ነው፡ ሰሙም አንድ ነው። ያ ሰም እንድትድኑበት ከሰማይ በታች የተሰጠ ብቸኛው ሰም ነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይባላል። “በገንዳው ውስጥ ለምን ይፈሩታል? ” እኔ ልገረም የማልችለው ነገር ይህ ነው። ኧሃ-ሃህ። አያችሁ? ያ መንፈስ ያኔ በሰምርኔስ ሰርጎ ሰለገባ፡ ከዚያም አልፎ እስከ ጨለማው ዘመን ድረስ እራሱን እየሸመነ ደረሰ፡ በዚያም ዶክትሪን አደረጋት፡ በዚህ እስከ መጨረሻ ዘመን ድረስ መጣ። አሁን፡ በዚህ ሳምንት ውስጥ፡ እነዚያን ነገሮች እንዴት አድርጎ እንደሚያጎላቸው—ታሪክን እና መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ተከታተሉ።

68 ከዚያ በመቀጠል። በመልአኩ በኩል፡ በክርስቶስ ለዮሃንስ ተሰጠው፡ ለማን እንዲሰጥለት (ለማን?) ለቤተክርስትያኑ፡ ለአብያተ ክርስትያናት ይገልጥ ዘንድ ነው። በእጁም ያሉት ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ሰባት መልእክተኞች ናቸው። ስለዚህ መልእክት ሊቀበል የተመደበ ሰው ሁሉ፡ ያ በመጀመሪያ የተጀመረ እውነተኛው መልእክት፡ ይቀበላል።

69 በተጨማሪ፡ ወደ እነዚያ ጥልቅ ቦታዎች ወርደን፡ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንዴት እንደሰራባቸው ሰናየው፡ አስደናቂ ነው። እልል ያሰብላችኋል። እኔ ራሴ፡ ጥቂት ካነበብኩ በኋላ፡ ዞር ዞር ብዬ አለቅስና፡ ተመልሼ መጥቼ ቁጭ እላለሁ፡ እንደገናም እንቀሳቀሳለሁ። ይህን በማወቄ በጣም ደስተኛ ነኝ፡ እኛ በምንኖርበት በዚህ ዘመን ያንን ነገር እንድናይ እግዚአብሔር እንዴት ምህረትን አገነነልን? በቃ፡ ኢየሱስ “አንድ ሰው አልማዝ ለመግዛት ያለውን ሁሉ ሸጠ፡” እንዳለው ነው። እናንተም ይህን ለማግኘት፡ የዓለም ነገሮችን፡ እና የሌላ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ፡ ፈጽማችሁ ሸጣችኋል። እውነት ነው፡ መልሕቃችሁ ሁሉ በዚያ አድርጋችኋል። የቃሉን መገለጥ ለማየት የነፍስ መልህቅ ነው።

70 አሁን፡ የሚያነበው ሁሉ የተባረከ ነው ይላል። ልክ ነው? እና ዛሬ ጠዋትም እንዲህ እንላለን፡ ማንበብ ካልቻላችሁ፡ የሚሰማም የሚያነብም ሁሉ፡ የተባረከ ነው። አሁን፡ ሲነበብ ቁጭ ብለው ለሚያዳምጡት በመባረክ ይጀምራል፡ ከዚያም በእርሱ ላይ ማንኛውንም ነገር ለሚጨምር ወይም ከርሱ ላይ ማንኛውም ነገር ለሚያጎድል ሰው እርግማን ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ኢየሱስ ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኑን ከገለጸ፡ እርሱን ከዚያ ለሚያነሳው ወዮለት። አዎን። መገለጥ ነው። የመገለጥ—ሙሉ ቀኖና ነውና… ለሚጨምር፡ የእግዚአብሔር የመጨረሻ መጽሐፍ፡ የመጨረሻ ቃሉ ነው፡ የመጨረሻው-… ከዚ በተቃራኒ የሆነ መገለጥ ሁሉ፡ የውሸት ትንቢት ነው፡ እግዚአብሔር አይደለም፡ ምክንያቱም ይህ እውነት ነው።

71 እናም፡ አስታውሱ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ መጽህፍቶች፡ በክርስቶስ በእራሱ የተጻፈው መጽሐፍ ይህ ብቻ ነው። አስቡት! የብቻው መገለጥ፡ የሆነ መጽሐፍ ነው። በረከቱን እና እርግማኑን በማኖር፡ ማሕተሙን ያደረገበት ብቸኛው መጽሐፍ ነው። ለተቀበሉት በረከት ነው፡ ለማይቀበሉት እርግማን ነው።

72 አሁን—አሁን ለመጀመር ወደ ፍጥሞ ደሴት ደርሰናል፡ 9ኛው ቁጥር። በመጀመሪያ ደረጃ፡ ማለት የምፈልገው… የዚህ ርዕሰም፡ **የፍጥሞ ራዕይ** ነው። ይህ የተፈጸመበት ጊዜ ከ95 **ዓ/ም**፡ እስከ 96 **ዓ/ም** ነው። ቦታው በፍጥሞ ደሴት ነበር። መገኛ ቦታው ከትንሿ እስያ የባሕር ዳርቻ፡ በስተምዕራብ፡ ከኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በተቃራኒ ሰላሳ ማይል ርቀት ላይ፡ በሜዲተራንያን አዋሳኝ በኤጂያን ባሕር ዳርቻ ላይ ነው። መገኛው ቦታ ያ ነው።

73 አስቡት! በትንሿ እስያ የባሕር ዳርቻ፡ በኤጂያን ባሕር ሰላሳ ማይል ርቃ የምትገኝ፡ አንዲት ትንሽ ደሴት ናት። ከፊላዴል-… ወይም መጀመሪያው መልእክት ከተነገረባት፡ ዮሐንስም በዚያ ጊዜ ፓስተር የነበረባት፡ ከኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በተቃራኒ ነው። በሌላ አነጋገር፡ እሱ ከነበረበት ወደ ምሥራቅ ሲያይ፡ ወደ ቤተክርስቲያኑ በቀጥታ ይመለከት ነበር። የመጀመርያው መልእክት ደግሞ፡ የቤተ ክርስቲያንን ዘመን ለምትወክል ለቤተ ክርስቲያኑ ነበረ። እሺ፡ ራእዩ በጊዜው የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ለነበረው፡ ለቅዱስ ዮሐንስ መለኮት ተሰጠው።

74 ታዲያ የደሴቷ ሁኔታ ምን ዓይነት ነበረች? የት ነበር፡ በምን አይነት ሁኔታስ ነበረች? እሺ፡ በታሪክ ውስጥ በእባቦች፡ በጊንጦች፡ በእንሽላሊቶች፡ ወዘተ የተሞላች ድንጋያማ ደሴት እንደሆነች ይታወቃል። በድንጋይ የተሞላች፡ ሰላሳ ማይልስ ሰፋት ነበረች። በዮሐንስ ዘመን፡ እንደ አልካትራዝ እስር ቤት፡ ይጠቀሙባት ነበር። የሮማው ንጉሠ ነገሥት ግዛት ወንጀለኞችን የሚላኩባት፡ በእስር ቤት ሊያቆዩዋቸው የማይችሉ፡ እውነተኛ መጥፎ ወንጀለኞችን፡ በዚያች ደሴት ላይ እንዲሞቱ፡ እስኪሞቱ ድረስ በዚያ ያቆዩአቸዋል።

75 ጥያቄ፦ ዮሐንስ ወደዚያ ለምን ገባ? ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው፡ ጻድቅ ሰው፡ መልካም ሰም ያለው፡ ጥሩ ባህሪ ያለው፡ በችግር ውስጥ ያልነበረ፡ ይህ ሰው ለምን እዚያ ገባ? መጽሐፍ ቅዱስ "ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት፡" በማለት ያስቀምጠዋል።

76 አሁን አቀማመጡን አይተናል። የፍጥሞ ደሴት፡ በኤጂያን ባህር፡ ከባህር ዳርቻ ሰላሳ ማይል ርቀት ላይ፡ በግምት ወደ ሰላሳ ማይል አካባቢ፡ ድንጋያማ፡ በእንሽላሊቶች እና ጊንጦች የተሞላ፡ (እንደ አልካትራዝ) ለእስር ቤት የሚያገለግል ነበር። እዚህ እስር ቤት ማቆየት የማይችሉትን እስረኛ በዚያ ይጥላል፡ በአልካትራዝ ላይ እንደሚያስቀምጡት፡ እንደ... አደገኛ ወንጀለኞች ናቸው።

77 አሁንም ይህን ከደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻ የነበረው... እና በተፈጥሮ ሞት የሞተው ብቸኛው፡ ቅዱስ ዮሐንስን መለኮት ወደዚያ ወሰዱት። ዮሐንስ፡ ወደ ደሴቱ ከመወሰዱ በፊት "አስማተኛ ነህ፡" ተብሎ ተከሶ ነበር፡ ስለዚህም ለሃያ-አራት ሰአታት የፈላ ቅባት በሞላ በትልቅ በርሜል ውስጥ፡ ቀቀሉት አልተቃጠለም። መንፈስ ቅዱስን ከሰው ውስጥ መቀቀል አይቻልም... ? ... ምንም ጉዳት ሳይደርስበት፡ ለሃያ-አራት ሰአታት ቅባት በሞላ በርሜል ውስጥ ተቀቀለ። ሮማውያን––ምክንያት ሲሰጡ፡ እንዲህ አሉ፡ "ጠንቋይ ስለሆነ፡ ቅባቱ ላይ ጠንቁሎበታል፡" አሉት። ሥጋዊ አእምሮ ማሰብ የሚቻለው! አሁንስ፡ አያችሁ፡ እኛንም "አእምሮ አንባቢዎች፡ ጠንቋዮች፡ እና ብዔል ዜቡል" ይሉናል፡ አሮጌው መንፈስ ከየት እንደመጣ አያችሁ? እውነተኛው መንፈስ ከየት እንደመጣ ግን አይታችኋል? የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ነው። አያችሁ? ሃያ-አራት ሰአታት፡ ፈልቶ በሚፍለቀለቅ፡ ትኩስ ቅባት ውስጥ የተቀቀለ፡ አንዳች ግን ያልተነካ ሰው። አቤት፡ እግዚአብሔር መንፈሱ በእርሱ ዘንድ አለበሰው። ስራው ገና አላለቀምና።

78 በደሴቲቱ ላይ ለሁለት ዓመታት አስቀመጡት። እግዚአብሔርም ብቻውን ለራሱ ባገኘው ጊዜ፡ የእግዚአብሔር መልአክ እንደገለጸለት የራዕይ መጽሐፍን ጻፈ። ያ እንዳበቃ፡ ወደ ሀገሩ ተመልሶ የኤፌሶን ቤተክርስቲያንን እረኛ ሆነ። ዮሐንስ መለኮት፡ በኤፌሶን ሞተ ተቀበረም።

79 አቤት፡ እንዴት ያለ አቀማመጥ ነው! እሺ፡ ቤተ ክርስቲያን በዮሐንስ ሥር፡ ወይም በታላቅ ሰደት ስር ሆና፡ ዮሐንስ 9ኛውን ቁጥር እንዲህ ሲል ጽፏል፡

> **እኔ ወንድማችሁ የሆንሁ... ከእናንተም ጋር አብሬ-... መከራውንና፡ መንግሥቱን የኢየሱስ ክርስቶስንም ትዕግሥት የምካፈል ዮሐንስ፡ ስለ እግዚአብሔር ቃልና፡ ስለ ኢየሱስ ምስክር፡ ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ።**

80 በሌላ አነጋገር፡ ወደ እርሱ የመጣው የእግዚአብሔርን ቃል፡ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እያረጋገጠ፡ ክርስቶስም በእርሱ በኩል እንደገና መምጣቱን እና እርሱም እውነት እንደሆነ እየመሰከረ ነው። እውነቱ ይህ ነው። የእግዚአብሔር ባርያ መሆኑን የሚያረጋግጥ፡ የእግዚአብሔር ቃል በእሱ ዘንድ ተተረከ። ያንን መካድ አልቻሉም፡ ስለዚህ "አስማተኛ" ነህ አሉት። "ቅባቱ እንዳይጎዳው አስማት አርጎበታል፡ ሰዎቹ እንዳይድኑ አስማት አስርቶባቸዋል፡ ምንም ነገር የማይጎዳው... ሟርተኛ-... ክፉ መንፈስ የሰፈረበት፡ መጥፎ ሰው አይነት ነው።" በማለት በማሕበረሰቡ ዘንድ መኖር የማይገባው አደገኛ ሰው መሰላቸውና፡ በዚያም ምክንያት ወደዚያ ወረወሩት። እርሱ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ አደራ ተሸካሚ ሰው ነበር፡ እግዚአብሔርም በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ዓላማ ነበረው።

81 በሰደት እና ነገሮች ሁሉ ብዛት፡ ሊጠቀምበት ስላልቻለ፡ ቅዱሳንም እየመጡ፡ “ወንድም ዮሐንስ ሆይ፡ **አሁንስ፡** ምን ማደርግ ይገባናል? ምን እናደርጋለን?”

82 ዮሐንስ ነቢይ ነበር፡ እናውቀዋለን። እናም እነዚህን ጥያቄዎች እየጠየቁ ስለነበር፡ እግዚአብሔር ሮማውያን መንግስትን በመጠቀም ወደ ደሴቲቱ ወስዶ አቆየው። እንዲህም አለው፡- “አሁን፡ ዮሐንስ ሆይ፡ ና ቅረብ፡ የሚሆነውም ነገር አሳይሃለሁና።” የኋለኛው ሐዋርያት፡ ከዮሐንስ በቀር ሌላ የሚጽፈው አልነበረም። ስለዚህ በፍጥሞ ደሴት ከ95 ዓ/ም እስከ 96 ዓ/ም ድረስ አቆዩት። እርሱም ጽፎ፡ እንዲህ አለ፡-

> **እኔ... ወንድማችሁ የሆንሁ፡ ከእናንተም ጋር አብሬ መከራውንና፡...**

83 አሁን፡ ስለ ታላቁ መከራ አላለም። ታላቁ መከራ ያ አይደለም፡ ያም ወደ ቤተክርስቲያን አይመጣምና። ታላቁ መከራ የሚመጣው ወደ አይሁድ እንጂ፡ ወደ ቤተክርስቲያን አይደለም። ስለዚህ መከራው፡ ስለ ታላቁ መከራ አልነበረም።

84 አሁን 10ኛው ቁጥር፡-

> **በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ፡ በኋላዬም... የመለከትን ድምፅ፡... የሚመስል፡**
>
> **ታላቅ ድምፅ ሰማሁ፡...**

85 አሁን፡ በመንፈስ እስክትሆኑ ድረስ ለምንም አትጠቅሙም፡ እግዚአብሔር ሊጠቀምባችሁ አይችልም። በመጀመሪያ ነገራችሁን በመንፈስ እስክታደርጉት ድረስ—ጥረታችሁ ሁሉ... ሁሉ—ሁሉ—ሁሉ—ከንቱ ነው። “መዝሙር፡ በመንፈስ እዘምራለሁ። እጸልያለሁ፡” “በመንፈስ እጸልያለሁ፡” አለ ጳውሎስ። ከዚያም ወደ እኔ የሚመጣ መልካም ነገር ቢኖር፡ ለእኔ በመንፈስ ለእኔ ተገልጦ በቃል የተረጋገጠ መሆን አለበት (በሚያፈራው ፍሬ መተረክ አለበት)።

86 አሁን፡ በሌላ አነጋገር፡ እንዲህ ካልኩ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ ንስሐ ከገባሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ከተጠመቅኩ፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንደምቀበል ቃል ገብቶልኛል ካልኩኝ። መጀመሪያ ማድረግ ያለብኝ ነገር ንስሐ መግባት ነው። ይህ እውነት እንደሆነ ተገልጦልኛል። ከዚያም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጠመቃለሁ፡ ከዚያስ ፍሬው፡ መንፈስ ቅዱስን መቀበሌ ነው።

87 ከታመምኩ፡ እርሱም ካመንክና የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች ዘይት ቀብተው ከጸለዩልህ፡ የእምነት ጸሎት የታመሙትን ታድናለች ብሎ፡ ቃል ከገባልኝ። “ጌታ ሆይ፡ አምኛለሁ። መመሪያህን ተከትያለሁ፡ ሽማግሌ ይጸልይልኝ፡ በዘይት ይቀባኝ።” አበቃ፡ ቀጥል፡ ያ ነው—ያ ብቻ ነው።

88 “አይ፡” አንተ፡ “በርግጥ፡ ምንም ልዩነት አልተሰማኝም” ብለሃል። ኢየሱስም ገና ሳይወለድ፡ እግዚአብሔር እርሱን ዓለም ሳይፈጠር በፊት አርዶታል፡ እርሱ ያኔ ገና—ዓለም ሳይፈጠር በፊት የታረደ፡ የእግዚአብሔር በግ ነበረ። በእግዚአብሔር ዘንድ በአሳቡ፡ አስቀድሞ ያለቀ ነበረ። እኔም ብሆን፡ እናንተም በዚያ አልነበርንም፡ ይሁን እንጂ በእግዚአብሄር መጽሐፍ ውስጥ፡ ስሞቻችን አስቀድመው ከነበሩ፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ተጽፎ ነበር።

89 እግዚአብሔር አንድ ነገር ከተናገረ፡ መፈጸም አለበት። ስለዚህ አስታውሱ፡ የእግዚአብሔርን ቅድመ ሁኔታዎች ስታሟሉ፡ እግዚአብሔር ራሱን ይገለጣል እና የቀረውን ሐላፊነት ይወስዳል፡ እናንተ ግን ቀጥሉ፡ ተሰርቶ ያለቀ ጉዳይ ነውና። አቤት፡ አይደንቅም ወይ? ኦህ፡ ማይ፡ አስቡት! በእግዚአብሔር ፊት ብቻ አቅርበው... እግዚአብሔርም "አንተ **ይህን** አድርግ፡ እኔ **ይህን** አደርጋለሁ፡" ብሏል። በቃ፡ እኔ **ይህን** ካደረግኩ፡ እሱ **ያንን** ያደርጋል።

90 ከዚያ በኋላ፡ ዲያብሎስ "አየህ፡ ዘገየብህ፡" ይላል።

ያ ምንም ለውጥ አያመጣም። ዳንኤል አንድ ጊዜ ጸለየ መልአኩም ወደ እርሱ ከመድረሱ በፊት ሃያ-አንድ ቀን ቆየ፡ ነገር ግን ተስፋ አልቆረጠም፡ እንደሚመጣ ያውቅ ነበር፡ ስለዚህ እስኪደርስ ድረስ ጠበቀው። ሃሳቡ ያ ነው። አቤት፡ እምነታችሁ የሚያድገው ያኔ ነው። አሁን ከዚያ መውጣት አለብን፡ እንዲህ ቢሆን በፍጥነት የፈውስ አገልግሎት ይኖረን ነበር፡ አይደል? ትክክል። አዎን፡ የእምነት። ውስጠኛውን ለመፈወስ ግን፡ የነፍስ-ፈውስ አገልግሎት እንፈልጋለን፡ ዘለአለማዊ ህይወት የምታገኙበት፡ እና ጸንቶ የሚቆይ ያ ነውና። የዘላለም ሕይወት አይጠፋም ወይም አያረጅም፡ ያው ሆኖ፡ ይኖራል።

91 አሁን፡ ምንም ነገር ከመፈጠሩ በፊት በመንፈስ ነበረ። (እነዚያን ነገሮች ሲያደርግ)፡ በመጀመሪያ ደረጃ በፍጥሞ ደሴት ውስጥ ነበር፡ እና እንዲህ አለ፦ "የሚናገረኝ ድምጽ ሰማሁ፡" እና ሌላ ሌላ ነገር ተናገረ። አንዳች ነገር ከመፈጸሙ በፊት ግን፡ በመንፈስ ነበረ። ይህን በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ዘንድ ካስተዋላችሁት፡ ትልቁ ፊደል መንፈስ፡ መንፈስ ቅዱስን ነው። አሜን! በመንፈስ ነበረ። አቤት፡ ሳሰበው እንዴት ይደንቃል፡

**በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርኩ**፡...

92 በየትኛው ቀን? በጌታ ቀን። አሁን፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ትልቅ ክርክር አለ። ለአንድ ደቂቃ ብቻ፡ ጸጥ እናስብለው።

93 እንግዲህ፡ ዛሬ ጠዋት እንደተናገርነው፡ አንዳንዶች፡ የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል 17 መገለጥ፡ "ጴጥሮስ" ነበር ይላሉ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን "በጴጥሮስ ላይ ቤተክርስቲያኑን ሠራ፡ እሱ የመጀመሪያው ጳጳስ ነበር፡" ትላለች። ያገባ ሰው ሆኖ እንዴት ጳጳስ ሆነ? አያችሁ? "ጴጥሮስ ሮም ሄደ፡ በዚያም ተቀበረ፡" ይላሉ። እስኪ ከታሪክም፡ ይሁን ከሌላ፡ ጴጥሮስ ሮም መሄዱን የሚገልጽ አቅርቡ። አያችሁ? ጳውሎስ አዎን ሄዷል፡ ጴጥሮስ ግን አልሄደም። እሺ።

94 ስለዚህ እነዚህ ሁሉ ኢዝሞች፡ እና ነገሮች ሾልከው እንደመጡ ለማወቅ ችለናል። ሰዎች ግን፡ አያችሁ? ዛሬ... በሄዳችሁበት ሁሉ፡ እንደው... አንዳንድ ታላላቅ አብያተ ክርስትያን በእጁ የነበረ ሚስማር ይዘውታል። በዚያም ከነበሩት፡ ትክክለኛ ሚስማሮች፡ ዛሬ ስንት ሚስማር እንዳገኙ... ታውቃላችሁ? አስራ ዘጠኝ። አጥንት፡ ከልብሱም—ቁራጭ አሏቸው፡ ይነኩታል ይዳብሱታል። እኛ ግን—እነዚያ ነገሮች የሉንም፡ አያስፈልጉንምና። ክርስቶስ ሕያው ነው! እሱ በእኛ ውስጥ ነው፡ ሚስማር፡ ወይም ግማደ መስቀል፡ ወይም የአጥንት ቁራጭ፡ ወይም የሆነ ነገር አያስፈልገንም። እርሱ ሕያው አምላክ ነው፡ ራሱን እየተረከ፡ አሁን በእኛ የሚኖር ነው። እኛ አንድ የመታሰቢያ ህግ አለን፡ ያም የጌታ እራት ነው፡ የሞቱን መታሰቢያ ነው። ክርስቶስ ግን፡ ከእኛ ጋር እና በእኛ ውስጥ ነው።

እኛ ደግሞ ወደ ዓለም ልናውለበልበው የምንፈልገው ነገር ያ ነው (የመንፈስ ቅዱስን ክብር ነው)። መብራት እስኪጠፋ ድረስ እናውለበልበዋለን። እሺ።

95 ስለዚህ፡ አሁን... እንደምታዩት፡ የመንገዱ ሌላኛውን ዳር፡ መርጠናል። ታውቃላችሁ እኔ ሁልጊዜ ይህን ለመሆን በጣርኩ ቁጥር፡ ጌታችን ሁልጊዜ ለእኔ ይገልጽልኛል፡ አንድ ጽንፍ፡ እና ሌላ ጽንፍ አለ፡ በመንገዱ መሃል ግን እውነትን ያስቀምጣል። ኢሳያስ 35 ላይ፡ ወደፊት አንድ አውራ ጎዳና ይኖራል፡ ብሎ የተናገረበትን አስተውላችኋልን? እናም ውድ የናዝሪን ወንድሞቻችን፡ ያንን መዝሙር እንዴት እንደሚዘምሩት ታስታውሳላችሁ፡ "**የቅድስና አውራ ጎዳና። የቅድስና አውራ ጎዳና**።" አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱሶቻችሁን በትክክል ካነበባችሁ፡ "የቅድስና አውራ ጎዳና" አይልም። የሚለው ግን፦ "አውራ ጐዳና እና **መንገድ** ይኖራል፡ ሰሙ እንዲህ ይባላል፡" የቅድስና አውራ ጎዳና ሳይሆን፡ "የቅድስና **ጎዳና**" ይባላል። **እና** ማለት ዓረፍተ ነገርዎን የሚያጠናቅቅ መስተጻምር ነው። አያችሁ? የቅድስና አውራ ጎዳና አይደለም፡ "አውራ ጐዳና **እና** ጎዳና ይኖራል፡ ሰሙም **የቅድስና ጎዳና** ይባላል።"

96 አያችሁ፡ መንገድ ሲሰራ፡ **ጎዳና ሲዘጋጅ**... ቆንጆ መንገድ ከተሰራ፡ ውበቱ መኃሉ ላይ ነው፡ ምክንያቱ ቆሻሻዎችን ሁሉ ወደ ሁለቱ ጎኖች ያስወግዳቸዋልና። በቃ። አንድ ሰው በእውነት ወደ ክርስቶስ የመጣ ከሆነ፡ ዓይኖቹ በክርስቶስ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ትንሽ ስሜታዊነት ካለበት፡ አክራሪ ይሆናል። ትንሽ ቀዝቃዛ ከሆነም፡ በብስለቱ ምክንያት ወደ ጎን፡ ወደዚያ ተሸቀንጥሮ፡ አያችሁ፡ ተራ ኩኩምበር ይሆናል። ዋናው ቁም ነገር ግን የሚሰራ እና የሞቀ፡ በቂ መንፈስ የተሞላ ሲሆን፡ በመንገዱ መሃል ላይ ነው። አሜን! ከመንፈስ መታዘዝ ስር ራስህን ለመጠበቅ መንፈስ ሲንቀሳቀስ ለመንቀሳቀስ፡ እስኪንቀሳቀስ ወይም ከተንቀሳቀሰ በኋላ ሳይሆን፡ መንፈሱ ሲንቀሳቀስ ወዲያው ለመንቀሳቀስ፡ በበቂ ሁኔታ ያወቀ ነው።

97 የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን "መገለጡ ጴጥሮስ ነው፡" አለች።

የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን "ክርስቶስ ነው፡" አለች።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ግን፡ "ከእርሱ ዘንድ (ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ) የክርስቶስ መገለጥ ነው።"

"አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ።"

"የዮና ልጅ፡ ስምዖን ሆይ፡ ብጹዕ ነህ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም፡ ከማንም ሰው፡ ሴሚናሪ፡ ወይም ገዳም፡ ከማንኛውም ነገር አልተማርከውም። ነገር ግን በሰማያት ያለው አባቴ ይህን ገልጦልሃል። አንተ ጴጥሮስ ነህ፡ በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆች ሊያሸንፏት አይችሉም።"

98 አሁን ሁለት የተለያዩ ሀሳቦችን ወደሚገናኙበት ሌላ ቦታ መጥተናል። አሁን እኔ፡ ልሳሳት እችላለሁ፡ ከሆነም፡ እግዚአብሄር ይቅር ይበለኝ። ነገር ግን ሰባተኛው-ቀን አድቬንቲስቶች ከሚሉት ጋርም አልስማማም፡ "በጌታ ቀን፡ እርሱ በገባባት በሰባተኛዋ ቀን ነው ይላሉ።" የሰባተኛው-ቀን አድቬንቲስት ወንድሞች፡ እና ብዙዎቹ፡ የጌታ ቀን ብሎ የጠራው የሰንበትን ቀን እንደሆነ ይናገራሉ። የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንም፡ "የ—እሑድ ቀንን፡ የመጀመሪያው

ቀን፡" የጌታ ቀን ብላ ትጠራዋለች። እና ብዙ ጊዜ እናስተውላለን—የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንም፡ የፕሮቴስታንት ሰዎችም ሁሉ፡ እስከ ዛሬ ድረስ፡ "እሑድን፡ የጌታ ቀን" በማለት ይጠሩታል። ያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ እሑድ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንጂ የጌታ ቀን አልነበረም። ሰባተኛው ቀንም፡ ሰንበት አልነበረም። ዮሐንስ ራዕይን ለመጻፍ ሁለት ዓመት ስለፈጀበት ከእነዚያ ቀናት አንዱ ሊሆን አይችልም። ብዙ ሰባተኛ ቀናት እንዲሁም ብዙ የመጀመሪያ ቀን ፋሲካዎች አልፏልና። የትኛዋ ቀን ናት?

99 መጽሐፍ ቅዱስ፡ ራዕይ የተጻፈው ከ 95 እስከ 96፡ **ዓ/ም፡** ሁለት ዓመታት። የጌታ ቀን ነበር። የጌታ ቀን ያለው በትክክል የተናገረውን ነው፡ ያም እንዲሁ ነበርና። ዮሐንስ በመንፈስ ወደ ጌታ ቀን ተወሰደ። ይህ የሰው ቀን ነው፡ የጌታ ቀን ግን ወደፊት ይመጣልና። በጌታ ቀን እንደነበረ በቅዱሳት መጻህፍት እናያለን፡ በመንፈስ ተይዞ ወደ ጌታ ቀን ተወሰደ። አሜን! ትክክል። አያችሁ፡ እነሆ እርሱ በጌታ ቀን ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጌታ ቀን ይናገራል። እንደ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት መሰረት፡ በጥቂቱ ወደ እሱ ደርሰናል።

100 የመጀመሪያው ነገር፡ ስለ ሰንበት ቀን፡ ስንነጋገር፡ የሰንበት ቀን የተወሰነ ቀን ማክበር አይደለም። ቅዳሜን የሰንበት ቀን አድርገን እንድናከብራት የተሰጠን ትእዛዝ የለም። በአዲስ ኪዳን፡ የመጀምሪያዋ ቀን የሰንበት ቀን አድርገን እንድናከብራት የተሰጠን ትእዛዝም የለም። መጽሐፍ ቅዱስ፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 4 ላይ እንዲህ ይላል፡ "ኢያሱ አሳርፏቸው ቢሆን ኖሮ፡ ከዚህ በኋላ ስለ ሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር ይላል።" ትክክል። ለእግዚአብሔር ሕዝብ ግን፡ ዕረፍት ወይም ሰንበትን-ማክበር፡ ቀርቶላቸዋል። ወደ እረፍቱ እንደገባን፡ የምናምን እኛም፡ እግዚአብሔር ከሰራው እንዳረፈ፡ እኛም ከሰራችን አርፈናል።

101 ተከታተሉ! አቤት! ጌታ ይባረክ። በጣም ደስ የሚል ስሜት ይሰማኛል፡ የለሁም ከራሴ ወጥቻለሁ።

102 አስተውሉ፡ በሰንበት ቀን። እግዚአብሔር ምድርን በስድስት ቀን ሰራ፡ በሰባተኛው ቀን ግን ወደ እረፍቱ ገባ ከዚያ በኋላ ዓለማትን ለመስራት ወደ ኋላ አልተመለሰም። ከዚያም ለሰዎች ልጆች እንደ መታሰቢያ አድርጎ ሰጣቸው። ምክንያቱ አሁን እዚህ ሆናችሁ ልታከብሩት አትችሉም፡ ምክንያቱ እናንተ ሰንበትን እዚህ ስታከብሩ፡ የዓለም ሌላኛው ክፍል እንደገና እሑድ ቀን ይሆንበታል። አያችሁ? ስለዚህ በቦታና በጊዜ ለተወሰነ ለእስራኤል ሕዝብ፡ የተመደበ መሆኑን ያሳያል። በዚያ ግን ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሰንበት-ማክበርን ቀርቶላቸዋል።

> **ወደ እረፍቱ መግባታችን**… **ለምናምን** ለእኛ፡… **ከሰራዎች ሁሉ**… (ዕብራውያን ምዕራፍ 4፡ እየጠቀሰኩ ነው)… **ምንም እንኳን ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ** የተከናወነ **ቢሆንም።**
>
> **ስለ ሰባተኛው ቀን ግን**… **በአንድ ስፍራ**-… **እንዲህ በማለት** ተናግሯል…
>
> **እንደ ገናም፡** እንዲህ ሲል፡ **ስለተወሰነ ቀን በዳዊት ይቀጥራል**፡… (ማስታወሻ ለምትይዙ፡ ዕብራውያን 4)

**ይህን ከሚያህል ዘመን በኋላ፡ በዳዊት ሲናገር፡ ዛሬ ብሎ፡ አንድ ቀን፡ እንደ ገና** ይቀጥራል፡ **ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት**... **ወይም፡ በፊት እንደ ተባለ፡** ልባችሁን **እልከኛ አታድርጉ**።

**ኢያሱ እረፍት የሰጣቸው ኖሮ** ቢሆንስ፡ (ቀን)... **ከዚያ በኋላ ስለ ሌላ ቀን** ባልተናገረ **ነበር።**

**በዚያ** ግን **ዕረፍት ቀርቶላቸዋል**... (ሰንበትን-መጠበቅ)...

103 "ዕረፍት" የሚል ቃል። **ሰንበት** ለእኛ እንግዳ ቃል ነው፡ ትርጉሙም "ዕረፍት" ማለት ነው። የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "የዕረፍት" ቀን፡ የሰንበት ቀን፡ እረፍት ያድርጉ፡ ሥራ አትሰሩ።

**ኢያሱ እረፍት የሰጣቸው** ኖሮ ቢሆንስ፡... **ከዚያ በኋላ**... **ስለ ሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር።**

በዚያ ግን... **ለእግዚአብሔር ሕዝብ ዕረፍት** (ሰንበትን-መጠበቅ) **ቀርቶላቸዋል።**

**ወደ ዕረፍቱ የገባን**፡... **እግዚአብሔር ከሰራው እንዳረፈ፡ እኛም** ከሰራችን... አርፈናልና፡

104 ወደ እረፍት ጨርሰን ገብተናልና፡ በሳምንቱ ቀጣይ ቀን እንደገና ለመጀመር ወደሱ አንመለሰም። ኢየሱስ ለብጹአን ሲናገር፡ እንዲህ አለ፡ "ለቀደሙት፡ 'አትግደል' እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፡ ያለ ምክንያት፡ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ፡ ገድሏል። ለቀደሙት፡ 'አታመንዝር፡' እንደተባለ ሰምታችኋል። ትእዛዙ ያ ነው። እኔ ግን እላችኋለሁ፡ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሰዋ ጋር አመንዝሮአል።" ልክ ነው?

105 ስለዚህ እነዚህ ሁሉ ነገሮች እውነተኛውን ጊዜ እስኪመጣ ድረስ፡ የነበሩ መታሰቢያዎች፡ ምልክቶች፡ ድንቆች ናቸው። አሁን፡ ኢየሱስ በማቴዎስ 11 ላይ፡ (ብፁዓን ማዘዝ)፡ ከጨረሰ በኋላ፡ እንዲህ አለ፡

**እናንተ ደካሞች፡** የደከማችሁ፡ **ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፡** ወደ እኔ ኑ፡ እኔም ለነፍሳችሁ **እረፍትን እሰጣችኋለሁ**።

**ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፡ ከእኔም ተማሩ፡ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና**... (ልክ ነው? )

**እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፡ ወደ እኔ ኑ... እኔም አሳርፋችኋለሁ፡ ለነፍሳችሁ** እረፍት ታገኛላችሁ። ("አንድ ቀን፡ አሥር ቀን፡ አምስት ዓመት፡ ሠላሳ-አምስት ዓመት፡ ሃምሳ ዓመት፡ ዘጠና ዓመት የደከማችሁ ሁሉ፡ ከዛልክ እና ከደከመህ፡ ወደ እኔ ና፡ እኔም አሳርፍሃለሁ። ያን ሁሉ የኃጢአት ሸክም ከአንተ አራግፌ፡ ወደ አንተ እገባለሁ፡ ፍጹም ዕረፍት እና እርካታን እሰጥሃለሁ።")

106 አሁን ያ እረፍት ምንድን ነው? እስኪ—ለጥቂት ጊዜ በዚህ ላይ እንቆያለን፡ ምን እንደሆነ እናየዋለን። አንዳንዶቹ እንዲህ ይላሉ፡ "ሂድና፡ የቤተ ክርስቲያን አባል ሁን።" አይደለም! "ስምህን በመጽሐፉ ላይ አስመዝግብ።" አይደለም! "እሺ፡ የተለየ አይነት አጠማመቅ።" አይደለም! እስኪ ተረጋግተን

እንየው። ይህን ለማየት ስትጠባበቁ ለመረጋጋት ፈቃደኞች ናችሁ? ዮሐንስ የት እንደሄደ እናያለን። ወደ ምን ዓይነት ቀን ሄዶ ነበር እናየዋለን?

107 ኢየሱስ በምድር ላይ ሲሞት፡ እና ሰራው ሲጠናቀቅ፡ ወደ አንድ ሰፍራ ገባ።

108 አሁን ወደ ኢሳይያስ ምዕራፍ 28፣ ከቁጥር 8 እንከፍታለን። አሁን፡ ኢሳይያስ 28፡8 እንደሆነ፡ እምናለሁ። ኢሳይያስ 28ን፡ እናንብብ፡ ነብዩ ከሰባት መቶ አሥራ ሁለት ዓመታት በፊት የተናገረው ነው። አሁን፡ እውነተኛው **ሰንበት** ምን እንደሆነ፡ እውነተኛው ዕረፍት ምን እንደሆነ ማወቅ የምትፈልጉ ሰንቶች ናችሁ? እነሆ። አሁን፡ ነቢዩ የተናገረው ይህ ነው፡ የት እንደተፈጸመ አሳያችኋለሁ። ኢሳይያስ 28:8ን፡ ተከታተሉ፡

**ማዕዱ ሁሉ**... (ነቢዩ ስለ እነዚህ ቀናት ትንቢት ተናገረ)

**ማዕዱ ሁሉ ትፋትንና ርኩሰትን ተሞልቶአታል፡** (የሚያጨሱ የሚጠጡ የሚዋሹና የሚሰርቁ ሰዎች ሁሉ፡ የጌታን እራት ይካፈላሉና)... ንጹሕ ሰፍራ **እንኳ የለም።**

**እውቀትን** ለማን **ያስተምረዋል**?...

ዛሬ እውቀትን ለማን ማስተማር ትችላላችሁ?

109 ቢሊ ግራሃምን ዛሬ የሰማችሁ ሰንቶች ናችሁ? የሰበከው ድንቅ ሰብከት ነበር፡ ሰዎች ውሸትን አምነው በዛ ውሸት እንዴት እንደሚቀጥሉ እና—እና እራሳቸውን ትክክል የሆነውን እንዳደረጉ አድርገው ይመጻደቃሉ። የአሜሪካ ህዝብ ሲያታልል፡ እንዲህም አለ፡ "የጠቢብ ሰው ማጣሪያ፡ እና የሚያጨሰው ሰው ሲጋራ፡" እሱን እንደ ምናምንቴ ከመቁጠር ይልቅ፡ በአንዲት የዲያብሎስ ውሸት ተታለሉ፡ ምንም ይሁን ምን፡ እንዲህ ያለውን በማጨሱ ጠቢብ ሰው ለማስመሰል ነው። ያ ሁሉ... ሞት እና ካንሰር ያዘለ መሆኑን እያወቀ፡ በሳምባው በኩል ምጎ ካቦነነ፡ እንደውም ሞኝ የሚያደርገው ማጨሱ ነው። ሞኝ እሱ ነው። ይህ የጠቢብ ሰው ማጣሪያ፡ አይደለም—አይደለም—እንዲህ ብሎ ነገር የለም። ጠቢብ ሰው እንዲህ አይነቱን ነገር አይጠቀምም።

110 "ያለ ኦሬንተል 92 ህይወት የለም፡" እና የመሳሰሉ ነገሮች። ያለ ክርስቶስ ህይወት የለም፡ እውነተኛው ህይወት ያ ነው። ወንዶች እና ሴቶች ያንን ነገር እንዲጠጡ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው? ምክንያቱም እግዚአብሔር እርሱን እንዲጠሙት ወደ በውስጣቸው ያስቀመጠውን ጥማት ለማርካት ይጥራሉ፡ ስለዚ ያንን በዓለም ነገሮች ለማርካት እየጣሩ ነው። እና እነዚያ የምንከተልበት ምክንያት ይህ ነው። ለዚያም ነው ሰዎች እንዲህ የሚሆኑት፡ ስለ እግዚአብሔር ያለውን የውስጥ ጥማታቸው ለማርካት ይጥራሉ፡ ዲያብሎስም በህይወት ፈንታ ሞትን እየሰጣቸው ነው።

... **ማዕዱ ሁሉ ትፋትን ተሞልቶአል**...

111 ቀሳውስቱ፡ ሌላውም ሁሉ፡ እንዲህ ይላሉ፡ "ረጋ ያለ መዝናናት ችግር የለውም።" እንደዚህ ብሎ ነገር የለም!

**እውቀትን** ለማን **ያስተምራል**? ወይስ **ወሬ ማስተዋልን**... **ለማን ይሰጣል? ወተትን ለተዉ ወይስ ጡትን ለጣሉ ነው።** (ከእንግዲህ እኛ ሕፃናት አይደለንም።)

**ትእዛዝ በትእዛዝ፡ ትእዛዝ በትእዛዝ፡ ሥርዓት በሥርዓት፡ ሥርዓት በሥርዓት፡ ጥቂት በዚህ፡ ጥቂት በዚያ ነው፡**

**በባዕድ አፍ** በልዩም ልሳን **ለዚህ ሕዝብ ይናገራል።**

**እርሱም፡ ዕረፍት ይህች ናት**... (ምን? ሰንበትን-መጠበቅ!)... **የደከመውን አሳርፉ** ይህችም **ማረፊያ ናት**... ("እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ።") ... **የደከመውን አሳርፉ፡ ይህችም** ማረፊያ **ናት አላቸው፡ እነርሱ ግን መስማትን እንቢ አሉ።**

112 ያ የተፈጸመው መቼ ነው? ከሰባት መቶ አሥራ ሁለት ዓመታት በኋላ በጴንጤቆስጤ ቀን የማይታወቅ ልሳን በሕዝቡ ላይ ወረደ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው በሌላ ልሳኖችም መናገር ጀመሩ፡ መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸውን ወሰደ፡ ዓለማዊ ነገሮቻቸው አስተዋቸው። ከዚያም ከክርስቶስ ጋር ወደ ዕረፍት ገቡ። ጳውሎስ ሲናገር፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 4 ላይ፡ "ወደ ዕረፍቱ የገባን እኛ ነን እግዚአብሔር በፍጥረት ቀን እንዳደረገው ከዓለማዊ ሥራዎች ሁሉ አርፈናል፡ እርሱ ወደ ዕረፍቱ እንደ ገባ፡ እኛም አለማዊ ስራዎቻችን ከተውን በኋላ ከእርሱ ጋር እንገባለን።" ትክክለኛ፡ እና እውነተኛው ሰንበታችሁ ይህ ነው።

113 ጳውሎስም ተይዞ ወደ ሰንበት መንፈስ ተወሰደ፡ በመንፈስ ቅዱስም እስከ ጌታ ቀን ድረስ ተሻገረ።

114 ጦርነቶች ለምን ሆነብን? ለምን ተቸገርን? ለምንድነው ህዝብ በህዝብ ላይ የሚነሳው? የሕይወትን ልዑል፡ ኢየሱስ መጣ፡ እርሱንም ገደሉት።

115 ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፡ ወይም ከአሁን ጀምሮ፡ ሳንታ ክላውስ እና ሬንዲር እና—ጂንግል ቤል እና የጣኦት አምልኮ ስርዓቶች አሸንክታቦች ሁሉ፡ ይንጠለጠላል። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አዋጅ ነው። ሰዎች ስጦታዎችን ለመለዋወጥ እና እንዲያ የመሳሰሉ ነገሮችን ለማድረግ በውድ ዋጋ ይገዛሉ፡ ጣኦት ነው! ክሪስማስ የአምልኮ ቀን ነው።

116 በነገራችን ላይ፡ ክርስቶስ በታኅሣሥ ሃያ-አምስተኛው ቀን አልተወለደም። ሊሆንም አይችልምና። ይሁዳ ብታዩት ኖሮ፡ ኮረብታዎቹ በበረዶ የተሞሉ ናቸው፡ እዚህ ካለው የባሰ ነው። የተወለደው ተፈጥሮ ሁሉ በሚፈካበት በሚያዝያ ወር ነው።

117 ግን፡ አሁን ባህላቸው ነው። እኛ ለምን—ለምን እነዚህን ነገሮች እናደርጋለን? ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ይልቅ የሰዎችን ወጎች ስለምንከተል ነው። ከዚያም... ያ ብቻ ቢሆን በተሻለ፡ ነገር ግን በዛ ምክንያት ነገሩን ንግድ ያደርጉታል። እንዲህ ያሉ ድርጊቶችን መፈጸማቸው ለእነሱ ውርደት ነው፡ አሳፋሪ ነው። የጣኦት በዓል ነው! ሳንታ ክላውስ ከኢየሱስ ጋር ግንኙነት የፈጠረው መቼ ነበር? እነዚህ ሁሉ የፋሲካ ጥንቸል ወይም ዶሮ... በሆነ ቀለም መቀባት ወይም የሆነ ነገሮች፡ የሆነ ነጭ ጥንቸል ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ጋር በምን ይገናኛል? የንግዱ ዓለም እንዴት እንደሆነ አይታያችሁም... ?

118 ለዚህም ነው እነዚህን የሮክ-እና-ሮል ያረጁ እና የቆሸሹ፡ የብልግና ምስሎችን፡ መጽሃፎችን፡ እና እንደነዚህ አይነት ነገሮች የሚሸጡላቸው፡ የሰዎች ተፈጥሮ እንደዚህ አይነቱ ከንቱ ነገር ስለሚመኝ ነው። ልብ ውስጥ የሆነ ችግር

ስላለ ነው፡ ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ዕረፍት ከቶ አልገቡም ከእነዚህ ነገሮችም አልተላቀቁም። ወደ ዕረፍት መጥተው መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ፡ ከዚያ ከዓለም እና ከዓለም ነገሮች ጋር ይቆራረጣሉ።

119 እርሱንም እግዚአብሔር አሻገረው። ኦህ፡ እንደ ጳውሎስ ወደ ሦስተኛው ሰማይ ተወሰዶ፡ አሁን፡ ነገሮችን አይቷል ብዬ አላምንም። እሺ፡ ከጥቂት ሳምንታት በፊት መንፈስ ቅዱስ፡ እዚህ እንዲህ አደረገ፡ እንዴት ልበላችሁ... በሌላ አባባል፡ እኔ ሞትን የሚፈራ ነበርኩ፡ መንፈስ ቅዱስ ግን ወስዶ አሻገረኝ እና ምን እንደሆነ አሳየኝ። ምስክርነቱን ሰምታችሁታል። ከዚያ ከተመለስኩ በኋላ፡ "ሞት ሆይ፡ መውጊያህ፡ የት አለ? " ከመጋረጃው ጀርባ ያለውን ለማየት ተሻገርኩ። ከዚያ በኋላ ከአድማስ ባሻገር ባለው ህይወታችን መንፈስ እና መናፍስት ሳንሆን፡ ወንዶች እና ሴቶች እንደምንሆን፡ ከመጋረጃው ባሻገር፡ የማይታመሙ፡ የማይሞቱ፡ ወጣቶች መሆናችን እንድነግራችሁ መለሰኝ። ሞት እናንተን ወደዚያ ቦታ ከማድረስ በቀር ምንም አያደርጋችሁም።

120 አሁን፡ ዮሐንስም በመንፈስ፡ ከፍጥሞ ደሴት፡ ወደ ጌታ ቀን ተሻገረ። ይህ የሰዎች ቀን ነው፡ ሰዎችም ይዋጋሉ፡ የጌታ ቀን ግን እነዚህ መንግስታት ሁሉ የጌታችንና የመሲሑ በሚሆኑበት ጊዜ፡ ያኔ ታላቁ የሺህ ዓመት መንግስት ይሆናል። የጌታ ቀን፡ የሚመጣበት ቀን፡ ፍርዱ፡ ያ ቀን የጌታ ቀን ይሆናል።

121 ይህ ግን የሰው ቀን ነው፡ ሰዎች በእናንተ ላይ የፈለጉትን የሚያደርጉበት እና እናንተን የሚመቱበት ምክንያት ለዚህ ነው፡ አሁን ለጊዜው... "ሆሊ-ሮለር እና ወገኛ፡" ይሉአችኋል... ነገር ግን ጊዜ አለ፡ ነገር ግን የሚመጣ ጊዜ አለ፡ አያችሁ፡ ያንን ነገር የማያደርጉበት ጊዜ ይመጣል። በእግራችሁ ስር ወድቀው ያለቅሳሉ ያዝናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ በሚልክያስ ምዕራፍ 4 ላይ፡ ከተቃጠሉ በኋላ በአመዳቸው ላይ ትሄዳላችሁ፡ ሥር ወይም ቅርንጫፍ አይተውላቸውም ይላል። በትክክል መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "ጻድቅ በኃጥኣን አመድ ላይ ይሄዳሉ።" ትክክል። ፈጽመው ላይመለሱ፡ ሥር ወይም ቅርንጫፍ አይተዉላቸውም። ፍጻሜአቸው ያ ነው። አሁን ይህ የሰው ቀን ነው (የሰው ስራ፡ የሰው አሰራር፡ የሰው ቤተክርስቲያን፡ የሰው ሀሳቦች)፡ የጌታ ቀን ግን እየመጣ ነው።

122 አሁን፡ በጌታ ቀን በመንፈስ ነበር። እሺ፡ በጌታ ቀን በመንፈስ በነበረበት ጊዜ የሰማው የመጀመሪያው ነገር... 10ኛ ቁጥር ላይ እንሂድ፡

> **... በጌታም ቀን፡ በመንፈስ**... **የ... መለከትን የሚመስል፡ ድምጽ**... **ሰማ፡**

123 አሁን፡ አንድ ምሳሌ እንዳናልፍ። ነገ መውሰድ ካለብን፡ ልንወስደው እንችላለን፡ አያችሁ። አንድ ሰው ሰዓቱን ይቆጣጠርልኝ፡ እንዳይመሽብኝ።

124 እሺ፡ አሁን፡ "... በጌታ ቀን በመንፈስ ነበረ።" አሁን አስታውሱ፡ መጀመሪያ ማድረግ ያለብህ ነገር ምንድነው? በመንፈስ ሁን። መገለጥ ወደ አንተ የሚመጣበት መንገድ እንዴት ነው? በመንፈስ ሁን። መንፈስ ቅዱስን እንዴት ማግኘት ትችላለህ? በመንፈስ ሁን። በመንፈስ ሁን።

125 ኃጢአተኛ በነበራችሁ ጊዜ፡ ወደ ዳንስ ቤት እንደገባችሁ ወዲያው **በዚያ** መንፈስ ትሆናላችሁ። ኦህ፡ ማይ፡ እጆቻችሁን ማጨብጨብ፡ እግራችሁን

ማጠፍ ትጀምራላችሁ፡ ታብዳላችሁ፡ ኮፍያችሁን ምሬት ላይ ትወረውራላችሁ፡ ከጥግ እስከ ጥግ እየተንቀሳቀሳችሁ፡ ትጃጃላላችሁ። በዛው መንፈስ ውስጥ ስለሆናችሁ ነው። አሰቡት እስኪ፡ አንድ ዳንስ አፍቃሪ ሰው፡ ወደ ዳንስ ቤት ገብቶ፡ "ጥሩ ነው፡ ጥሩ ጊዜ እያሳለፋችሁ እንደሆነ፡ አስባለሁ፡" እስኪ ይበላቸው።

ወዲያው "ኧረ ባክህ!" ይሉታል። "አንተ የአበባ ጌጥ፡ ሂድ ውጣ ከዚህ!" እያችሁ?

126 ቤዝ ኳስ ጨዋታ ውስጥ፡ አንዱ ወገን ከፍተኛ ነጥብ ሲያስቆጥር፡ አንዱ መጥቶ፡ ቁጭ ብሎ እያየ፡ ዘና ብሎ፡ "አሪፍ ይመስለኛል፡ ቢል።" በጭራሽ፡ የቤዝቦል ወዳጅ አያደርግህም፡ በትክክል... የቤዝቦል መንፈስ ውስጥ ነህ አትባልም። አንድ ሰው ነጥብ ሲያስቆጥር፡ ተነስተህ "ኡኡ! ማይ! ድል!" ብለህ ትጮኻለህ፡ ሰው ኮፍያውን **እንዲህ** ብትመታበት፡ ማንም ምንም አይልም።

127 በቤተክርስቲያን በመንፈስ ሆናችሁ፡ ተነስታችሁ "ክብር ይሁን! ሃሌሉያ! ጌታ ይባረክ!" ብላችሁ ስትጮኹ ግን፡

አንድ ሰው ዞር ብሎ፡ "ቅዱስ-ተንከባላዮች፡" ይላችኋል። (ወንድም ዉድ፡ ሆይ... )

128 አንድ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ። እኛ እንዲህ በመሆናችን ቅዱስ-ተንከባላዮች ከተባልን፡ እንግዲያውስ እነርሱም **ያልተቀደሱ**-ተንከባላዮች ናቸው። ያልተቀደሰ-ተንከባላይ ከመሆን ቅዱስ-ተንከባላይ ብሆን እመርጣለሁ። (እናንተስ አይሻላችሁም? ) ማይ! በትክክል! ያልተቀደሱ-ተንከባላዮች።

129 ስለዚህ፡ ዮሐንስ በመንፈስ ነበረ። በመንፈስ ከሆነ በኋላ፡ ነገሮች መምጣት ጀመሩ። ልክ በመንፈስ እንደሆነ፡ የመለከት ድምጽ ሰማ። አሁን፡ መለከት የአንድ ነገር መምጣቱ የሚያውጅ ነጋሪ ነው። ለምሳሌ ብትሉ... ንጉስ እየቀረበ—ሲመጣ፡ የመለከት ድምጽ ይሰማል። ኢየሱስ ሲመጣም፡ የመለከት ድምጽ ያሰማል። ልክ ነው? ዮሴፍ በወጣ ቁጥር፡ የመለት ድምጽ ያሰሙ ነበር። እናም አሁን ደግሞ አዲስ ነገር እየቀረበ ነው፡ ዮሐንስ በመንፈስ ሆኗል የመለከት ድምጽ ሰምቷል። በመንፈስ ከሆነ በኋላ፡ የመለከት ድምጽ ሰማ፡ መለከቱን በሰማ ጊዜ ምን እንደሆነ ለማየት ወደኋላው ዞር ብሎ አየ።

130 ምናልባት ደሴቲቱ ዙርያ እየዘለለ፡ እየሮጠ፡ እያሸበሸበ የነበረ ይመስለኛል። በመንፈስ ሆኖ፡ ጥሩ ጊዜ በማሳለፍ ላይ ነበረ። እና፡ ይህ ሲሆን... ነገሮችን ማመናፈስ ሊመስልብኝ ይችላል፡ ይሁን እንጂ እንደዚያ ለማለት ፈልጌ አይደለም፡ እያችሁ። ሊያደርግ ይችላል! ማለት... እንደው፡ ያንን እያደረገ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔርን በመንፈስ እያመለከ፡ ጥሩ ጊዜ እንደነበረው አስባለሁ፡ ምክንያቱ ያኔ መንፈስ በላያቸው ላይ በወረደ ጊዜ የሆነባቸው የመጀመሪያ ነገር ይህ ነበርና። መንፈስ ቅዱስ በወረደባቸው ጊዜ፡ እንደ ሰከሩ ወንዶችና ሴቶች ተንገዳገዱ፡ እንደ ጠጣ፡ እና እንደ ሰከረ ሰው ሆኑ። እንዲህ እስኪባሉ-... ሰዎች "እነዚህ ሰዎች በአዲስ ወይን ጠጅ የሰከሩ ናቸው፡" እስኪሏቸው ድረስ ሆኑ። ለመጀመሪያ ጊዜ የሆኑት በዚህ መንገድ ነውና፡ አሁንም መንፈሱ እንደገና ሰለ መጣ፡ ምናልባት ተመሳሳይ ድርጊት

ሳይፈጽም አይቀርም። አያችሁ? በዚህ ጉዳይ ላይ አዲስ ነገር የለም—ይህ ነገር፡ **የጥንቱ-እምነት** ነው። አዎና።

131 "በጌታ ቀን በመንፈስ።" አሁን፡ ሰምተነዋል። አሁን ምን? አሁን፡ ምን እያደረገ ነበር? አሁን ከደሴቱ፡ በመንፈስ፡ ወደ ጌታ ቀን ተሻገረ። ወደ ጌታ ቀንም እንደገባ፡ መለከት ሰማ። ምንድነው ይሄ? እየቀረበው ያለ ሰው ነው። ታላቅ ሰው እየቀረበው ነው። መለከት ይሰማል፡ አንድ ሰው እየመጣ ነው! እርሱም አየ! ሃሌ ሉያ! መለከቱም፡

> **አልፋና ኦሜጋ፡ ፊተኛውና ኋለኛው እኔ ነኝ፡ አለ**፡... (የሁለተኛው አካል ወይም የሶስተኛ ወገን አዋጅ ሳይሆን፡ አንድ ወገን)... **አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ**፡... ("አንተን አንዳች ነገር ከማሳየቴ በፊት፡ ማን እንደሆንኩ እንድታውቅ እፈልጋለሁ!")

132 ከመገለጦች ሁሉ የሚበልጠው መገለጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት፡ አምላክ መሆኑ ነው። ይህ ካላመናችሁ ወደ መጀመሪያው መሠረት መድረስ አትችሉም፡ ጴጥሮስ... ወጥቶ የተናገረው ይህ ነውና፡ "ንስሓ ግቡ፡ አምላክነቱን ተመልከቱ። ለኃጢአቶቻችሁም ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ ከዚያ በመንፈስ ለመሆን ዝግጁ ትሆናላችሁ።" ከሁሉ በፊት ማወቅ ያለባችሁ የክርስቶስን አምላክነት ነው። "እኔ አልፋ እና ኦሜጋ ነኝ! እኔ ከሀ እስከ ፐ እኔ ነኝ፡ ከኔ በቀር ሌላ የለም። ፊተኛም እኔ ነበርኩ፡ በኋለኛም እኔ እኖራለሁ። የነበረውም፡ ያለውም፡ የሚመጣውም፡ ሁሉን ቻይ እኔ ነኝ።" አሰቡት! መለከቱ የተናገረው ይህ ነው።

133 ተጠንቀቅ ዮሐንስ! ወደ መንፈስ ገብተሃል፡ የሆነ ነገር ሊገለጥልህ ነው። ምንድነው? የመጀመሪያው ነገር፡ የመለከት ድምፅ፡ "አልፋ እና ኦሜጋ እኔ ነኝ።" የሁሉም መገለጦች የመጀመሪያ እኔ ነኝ። (ኦህ፡ ኃጢአተኛ ሆይ፡ ጊዜው ሳይረፍድ አሁን ንስሐ ግባ፡ ተንበርከክ።) "አልፋ እና ኦሜጋ እኔ ነኝ።" ያሳወቀው የመጀመሪያው ነገር፡ እርሱ ማን እንደነበረ ነው። (እየቀረበው ያለው ሰው ማን ነው? ይህ ንጉሥ ኢየሱስ ነውን? ንጉሥ እግዚአብሔር? ንጉሥ መንፈስ ቅዱስ? ) እንዲህ አለ፡ "ሁሉ በሁሉ እኔ ነኝ! ከሀ እስከ ፐ እኔ ነኝ። መጀመሪያም መጨረሻም እኔ ነኝ። የማይሞተው፡ ዘላለማዊው እኔ ነኝ!"

134 ያኔ ምን እንደነበረ እዩት፡ ትንሽ ቆይተን እርሱን በሰባት ሰብዕናው እናየዋለን። "መጀመሪያም መጨረሻም እኔ ነኝ። አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ፡ ፊተኛውና ኋለኛው እኔ ነኝ። ከመጀመሪያው በፊት እኔ አለሁ፡ ከኋለኛው በፊትም እኔ ነኝ፡ አሁንም አለሁ፡" በሌላ ቃል። "የመጀመሪያው እና የመጨረሻው!"

> ... **የምታየውን፡ በመጽሐፍ ጽፈህ**... በእስያ **ላሉት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፡ ላከው፡ ወደ ኤፌሶን፡... ሰምርኔስ፡... ጴርጋሞስ፡... ትያጥሮን፡... ሰርዴስ፡... ፊላዴልፊያ፡ እና ወደ ሎዶቅያ፡፡**

135 እሺ፡ ከመገለጦች ሁሉ የመጀመሪያው መገለጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ልዑል አምላክ ስለ መሆኑ ነው። ድምፁን ስትሰሙ ማንነቱን ማወቅ አለባችሁ። እሺ፡ በሲና ተራራ ላይ የተሰማው ራሱ ድምፅ፡ በታቦር ተራራ ላይ የተሰማው ያንን ድምፅ፡ እሱ ራሱ፡ "የሰው ልጅ የሚመስለውን።"

136 አሁን በሚቀጥለው ጥቅስ ተመልከቱ። እሺ፡

**ዞርም አልኩ**... (አሁን ምዕራፍ 12።)

137 እስኪ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ለአንድ ደቂቃ ብቻ ለቀቅ እናድርጋቸው፡ ምክንያቱም ቀጣይ ሳምንት ሙሉ በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ላይ እንቆያለንና። አያችሁ፡ ስለዚህ አለፍ እንለዋለን።

138 እርሱ ግን እንዲህ አለው፡ "ይህ... እኔ የማሳይህ መልእክት እንድትልክ አሁን እመራሃለሁ።" ማን ነው? "የመጀመሪያው እና የመጨረሻው እኔ ነኝ። የበላይ እኔ ነኝ። ሁሉን ቻይ እኔ ነኝ። አሁንም የሰባቱ አብያተ ክርስቲያና መልእክት እንድሰጥህ እንደመጣሁ ልነግርህ መጥቻለሁ። እንድትጽፈው፡ እንድታዘጋጀውም እፈልጋለሁ።" አያችሁ? "በእስያም ያሉት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት።" እንግዲህ፡ በዚያን ጊዜ ወደፊት የሚመጡትን ቤተ ክርስቲያን ዘመናትን የሚወክሉ ገጸ ባህሪያት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ።

139 አሁን፡

የሚናገረኝንም **ድምፅ ለማየት ዘወር አልኩ። ዘወርም ብዬ፡ ሰባት የወርቅ ሻማዎች አየሁ፡**

140 "ሰባት የወርቅ ሻማዎች።" ይህ፡ አሁን... ኪንግ ጀምስ ቨርዥን ነው፡ ምናልባት የእስኮፊልድ—ወይ ደግሞ የቶምሰን ቼይን ከያዛችሁ፡ ወይም ሌሎቹ፡ እነሱ ጋር ልክ አይደለም። ሻማዎች አይልም፡ ኩራዝ መሰቀያ ይላል እንጂ፡ በዋናው ትርጉም ውስጥ ግን፡ ትክክለኛ፡ እውነተኛ ትርጉም፡ መቅረዞች እንደሚል አምናለሁ። አያችሁ፡ በሌላ አባባል፡ እነዚህ ሰባት የወርቅ ሻማዎች ሰባት አብያተ ክርስትያናት ነበሩ። ትንሽ ቆይቶ፡... በቁጥር 20 ላይ፡ እዚህ ጋር እንዲህ ይላል፡ "ያየሃቸው ሰባት ሻማዎች ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።" እንግዲህ፡ እዩት፡ ሻማ ቢሆን ኖሮ፡ ብዙም ሳይቆይ፡ ይቀልጣል ነዶም ይጠፋል። ሻማ ግን አይደለም፡ መቅረዝ—ነው። እንደ መቅረዝ ያስቀምጠዋልና። "ዘወር ብዬ የሰውን ልጅ የሚመስለውን... በሰባቱ መቅረዞች መካከል ቆሞ አየሁ።"

141 አሁን—አሁን ተከታተሉ። ሻማው ብዙም ሳይቆይ ይቃጠላል፡ ይጠፋል፡ ከዚያ በኋላ አይገኝም፡ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ቀልጦ ይጠፋል። መቅረዝ ግን፡ መቅረዝ እንደዚህ ነው፡...

142 እዚህ ጋ፡ አንድ ቃል—እንመልከት፡ ወደ—ወደ ዘካርያስ 4:1 እንይ፡ ከዚያም ከዘካርያስ የምንፈልገውን ልናገኝ እንችላለን። ዘካርያስ 4:1፣ ምናልባት በዚህ—የምንፈልገውን አንድ ላይ ለመሰብሰብ እንችል ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ዘካርያስ በሶፎንያስ ማግኘት አልቻልኩም፡ እችላለሁን? እሺ፡ እሺ፡ መጽሐፍ ቅዱሴ እያረጀ ነው። ዘካርያስ 4:1፡ አሁን በደንብ ተከታተሉ፡ ድንቅ ምስል ታገኛላችሁ፡

**መልአኩም...**

143 አሁን፡ ይህ ነቢዩ፡ ገና ከክርስቶስ ልደት አምስት መቶ አሥራ ዘጠኝ ዓመታት በፊት ነው፡

**ከእኔም ጋር ይነጋገር** የነበረው **መልአክ፡ ተመልሶ፡ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ** ሰው **አነቃኝ፡** (አሁን ነቢዩ ራእይ እያየ ነው።)

እርሱም፡ **የምታየው ምንድር ነው አለኝ? እኔም፡ እነሆ፡ ሻማዎችን አየሁ** (ይህ ቃል "መቅረዝ" በሚል ትርጓሜ ተተርጉሟል።) **ሁለንተናው ወርቅ ነበረ፡ የዘይትም ማሰሮ**... **በራሱ ላይ ነበረ፡** (መብራት ነው።) **ሰባትም መብራቶች ነበሩበት፡ በራሱም ላይ ለነበሩት መብራቶች፡ ሰባት ቧንቧዎች ነበሩአቸው፡** (አያችሁ፡ እነዚያ የሚመጡ የቤተ ክርስትያን ዘመናት ነበሩ። አያችሁ? )

**በአጠገቡም ሁለት የወይራ ዛፎች ነበሩ፡**... (አሁን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን... በእነዚያ መብራቶች ውስጥ ምን ያነዱ ነበር? የሚያው ሰው አለ? ዘይት። ምን አይነት ዘይት? የወይራ ዘይት።) ... **ሁለት የወይራ ዛፎች**... (ምንድን ናቸው? አዲስና ብሉይ ኪዳን፡ በአጠገቡ የቆሙት ሁለቱ ናቸው።) **... አንዱ በማሰሮው በሰተ** ቀኝ፡ **አንዱም በሰተ ግራው ሆነው በአጠገቡ ነበሩ አልሁ።**

ከእኔ **ጋር ይነጋገር ለነበረውም መልአክ መልሼ፡ ጌታዬ ሆይ፡ እነዚህ ምንድር ናቸው፡ አልሁት**?

ከእኔ **ጋር ይነጋገር የነበረውም መልአክ መልሶ፡ እነዚህ ምን እንደ ሆኑ—አታውቅምን አለኝ? እኔም ጌታዬ ሆይ፡ አላውቅም፡ አልሁ።**

መልሶም፡ **ለዘሩባቤል የተባለው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ ይህ ነው፡ በመንፈሴ እንጂ፡** በኃይልና፡ በብርታት **አይደለም፡ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።** (እርሱ ኢየሩሳሌምን ያቃናል።)

144 አሁን፡ ሻማው ምንድን ነው? መቅረዝ ነው። እና ምን ያህል እንደሚደንቅ አስተውሉ። እነሆም፡ ዘወር ብሎ፡ ይህን የሰው ልጅ የሚመስለውን በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል ቆሞ አየ፡ ትርጉሙም ወደፊት የሚመጡ ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመን ማለት ነው። እያንዳንዱ ቧንቧ፡ ወይም—ወይም መቅረዝ፡ ከዋናው ትልቅ የዘይት ማሰሮ ጋር ተጣብቋል። እናም በዚህ ዘይት ውስጥ ትንሽ ልዩ-ቅርጽ ወዳለው ኩራዝ ይወጣል በውስጡም ወደ ዘይቱ ወደ ውስጥ የተንጠለጠለ ክር አለበት። እንግዲህ... ዋናውን የሚሞላው ትልቅ ግንድ፡ በቆመናው አናት ላይ ዘይት ያፈሱበታል፡ እና ትልቁን ቅርንጫፍም፡ እንደዚህ ባለው፡ ወደ ግንዶቹ ይፈሳል። እና ይህ ክር የተንጠለጠሉበት—ስር የገባ ቱቦ... ቀን ከሌሊት፡ ይበራል። በዋናው ቱቦ ውስጥ ዘይት ብቻ ይጨምሩበታል እንጂ፡ በፍጹም ስለማይጠፋ፡ መለኮስ አይጠበቅባችሁም። እነዚህም እንዲሁ የሚወጡት መቅረዞች፡ በላያቸው ላይ ኩራዞች ተቀምጠው ነበር። ከኩራዙ ወደታች ወደዚህ ውስጥ የተንጠለጠለው ክር፡ ከዚህኛው ህይወት ያገኛል። ኦህ፡ ከሻማው እጅግ ይለያል። እንዴት ልዩ ነው! መቅረዝ ነው፡ ዘይቱንም ይስበዋል።

145 እንግዲህ፡ እነዚህ መቅረዞች፡ በብሉይ ኪዳን በእነዚህ መቅረዞች ላይ የነበረው እሳት። አንደኛውን ኩራዝ ሲለኩሱት፡ በእጃቸው በያዙት እሳት ቀጣዩን ኩራዝ መለኮስ አይችሉም። አንዱን ኩራዝ ይለኩሳሉ፡ የተለኮሰውን አንስተው ሌላውን ኩራዝ ይለኩሳሉ፡ ቁጭ ያደርጉታል። ይሄን ኩራዝ ይለኩሳሉ፡ በመጀምሪያው እሳት ወሰደው ይሄኛው ኩራዝ ይለኩሳሉ። ኦህ፡ ከአቅማችሁ

በላይ እንዳልሆነ ተሰፋ አደርጋለሁ። “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡” ተመሳሳይ እሳት (መንፈስ ቅዱስ) እነዚያን አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ለዘመናት የለኮሳቸው እርሱ ነው።

146 በቅዱስ ዮሐንስ 15 ላይ ኢየሱስ፡ “እኔ የወይኑ ግንድ ነኝ፡ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ” አላለምን? እርሱ፡ ዋና ግንድ፡ እኛ ቅርንጫፎች ነን። አሁን፡ ግንድ ፍሬ አያፈራም...

147 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።]... እንደ ብርቱካን ያለ፡ የሆምጣጤ ዛፍ ውሰዱና፡ ከዚያ በኋላ—ቅርንጫፍ ከዚህም—ከዚያም ወሰዳችሁ፡ ማለት፡ ለምሳሌ ብንወሰድ፡ የወይን ዛፍ ወሰደን፡ የብርቱካኑን ዛፍ ትንሽ ሰንጠቅ አርገን፡ ወይኑን በዚያ ብናዳቅለው፡ ያድጋል። ከዚያም ሄዳችሁ የሎሚ ቅርንጫፍ ሰብሩና ወደ ብርቱካኑ ዛፍ አዳቅሉት፡ እርሱም ያድጋል፡ ወይም ሮማን ውሰዱ፡ ወይም፡ ማንኛውም የሆምጣጤ ፍሬ፡ ውሰዱ፡ መንደሪን ወይም ታንጀሎ፡ የመሳሰሉ የሆምጣጤ ፍሬዎች ውሰዳችሁ፡ ወደዚህ ዛፍ አዳቅሉት፡ እና የብርቱካን ዛፍ ህይወት ይጠቀማል፡ ብርቱካን ግን አያፈራም። ወይን ፍሬ ያፈራል፡ የታንጀሎ ፍሬ ያፈራል፡ የሎሚ ፍሬ ያፈራል፡ የሚበቅለው ግን ከዋናው የግንዱ ሕይወት ነው፡ ያ ግንድ ሌላ የራሱ ቅርንጫፍ... ካበቀለ ግን፡ በውስጡ ካለው ህይወት ጋር ተመሳሳይ ፍሬ ያፈራል፡ ብርቱካን ያፈራል። ምክንያቱም፡ በመጀመሪያ፡ በሥሩ ውስጥ የብርቱካን ዛፍ ሕይወት አለ፡ ሌሎች ግን የሆምጣጤ ዛፍ ተፈጥሮ እስከሆነ ድረስ በላዩ ካለው ህይወት መኖር ይችላሉ። የዋናው ፍሬ ማፍራት ግን አይቻለውም፡ ምክንያቱም ኦሪጅናል አይደለምና።

148 ቤተ ክርስቲያንም እንደዚህ ነች። ግንዱን ሰንጥቀው ፕሬስባይቴሪያን፡ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ እና የመሳሰሉትን አዳቅለውበታል። የባፕቲስት ፍሬ፡ የፕሪስባይቴሪያን ፍሬ፡ የሜቶዲስት ፍሬ ያፈራል፡ ያ ዛፍ ሌላ ግንድ ያበቀለ... ጊዜ ግን፡ በበዓለ ኃምሣ ቀን ያወጣው ግንድ አንድ ዓይነት ይሆናል፡ የመጀመሪያው ግንድ! በልሳኖች ይናገራል በውስጡም ከሞት የተነሳው የክርስቶስ ኃይል እና ምልክቶች ይኖሩታል። ለምን? ምክንያቱም በተተከለው የተፈጥሮ ህይወት እየተመገበ ነው። በርግጥ፡ የተተከለ አይደለም፡ በዚያ የተወለደ እንጂ። ጌታ ይባረክ! ኦህ፡ ማይ! በፊት አንዴም አሰቤው አላውቅም።

149 ተመልከቱ፡ እነዚህ ሌሎች ተዳቅለው፡ በዛፉ ውስጥ የገቡ ናቸው፡ ስለዚህ የራሳቸውን ዓይነት ፍሬ ያፈራሉ። **ይሄኛውን** ማፍራት አይችሉም። **ያን** እያምኑበትም፡ ምክንያቱ ስለዚህኛው ምንም ነገር አያቁም። ከዛ ዛፍ በሚወጣው ህይወት ውስጥ ቢወለዱ ግን፡ ሊሸከሙት የሚችሉት ብቸኛው ነገር፡ የዋናው ግንድ ሕይወት ነው።

150 እነዚህ ኲራዝ ግንዶች በሙሉ በአንድ ትልቅ ማሰሮ ውስጥ ይጠልቃሉ፡ በአንድ ትልቅ መያዣ ውስጥ፡ ዘጠኙ... ወይም ሰባቱ ኲራዞች ለየብቻቸው ከሱ ይወጣሉ። እንዲህ ሲበሩም፡ እያንዳንዳቸው መብራቶች ከዋናው የህይወት ምንጭ ይመጣሉ። የብርሃናቸው ምንጭም ከዚህኛው በርሜል ውስጥ ከመጥለቃቸው የተነሣ ነው። አቤት፡ ከሰባቱ የአንዱ ኮዋክብት የሚደንቅ ምሳሌ ነው (የሚወክለው ያንን ነው) እዚህ ካለው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሕይወቱ በእሳት ተቀጣጥሏል። ይህም... በእምነት በመንፈስ ቅዱስ እየነደደ ነው፡ እና

ህይወቱ ሻማ ነው፡ ወይም ሻማ ሳይሆን፡ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ (ወደ ክርስቶስ) የተጠለቀ ክር ነው፡ በዚያ ክር አማካኝነት ለቤተክርስቲያኑ ብርሃን እንዲሰጥ የእግዚአብሔርን ሕይወት እየሳበ ነው። አቤት፡ ይህ የእውነተኛ አማኝ ልዩ ጥላ ነው! ምን ዓይነት ብርሃን እየሰጠ ነው? የመጀመሪያው ክር ሲበራ የነበረው ተመሳሳይ ብርሃን ነው።

151 የመጀመርያው የቤተክርስቲያን ዘመን፡ ኤፌሶን ነበረች። ከዋክብት አንዱ፡ የዚያች ቤተ ክርስቲያን መልእክም፡ ጳውሎስ ነው። ሰባት ከዋክብት እሉ ትርጉሙም ሰባት መላእክት፡ ሰባት "መልእክተኞች" ማለት ነው። በዚህ ሳምንት ቅዱሳት መጻሕፍትንና ታሪኩን ወስጄ በእያንዳንዱ መልእክ ውስጥ እያንዳንዳቸው እውነት መሆናቸውን ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ፡ ለእያንዳቸው መላእክትም ብርሃናቸው አንድ ነበረች። ትክክል። እናም በነዚህ ዘመናት መካከል፡ ያ ታላቅ የሆነው ይመጣል።

152 አስተውሉ፡ ብርሃኑን... የሚሰቡት ዋናው ዘይት ካለበት ከማሰሮው ነው፡ ህይወታቸው በክርስቶስ የጠለቀ ነው። ሞታችኋል፡ ህይወታችሁም በክርስቶስ ተሰውሮአል... ወይም በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰውሮ፡ በመንፈስ ቅዱስ ታትሟል። ከዚያ ሊነቅላችሁ የሚችል ማንም የለም። እንዴት ትችላላችሁ? ማንም አይነቀንቃችሁም። የሕይወታችሁ ፍጻሜ በመንፈስ ቅዱስ ይቀጣጠላል፡ ኦህ፡ ይቀጣጠላል፡ ማለት ብርሃን ይሰጣል። አንደኛው የህይወታችሁ ጫፍ ምን ውስጥ የጠለቀ ነው? በክርስቶስ ውስጥ። በክርስቶስ ሞታችኋል እና ተሰውራችኋል፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ከልሏችኋል... ዲያብሎስ ሊነካችሁ አይችልም። አሜን! ማንቋረር እና ድምጽ ማሰማት ይችላል። ሞት እንኳን ሊነካችሁ አይችልም፡ "ሞት ሆይ፡ መውጊያህ የት አለ? ድል መንሣትህስ የት አለ? በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድልን ለሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።"

153 የዚህ ጥቅስ መጨረሻ፡ እናንብበው፡-

**ዘወርም ብዬ፡ ሰባት የወርቅ መቅረዞችን አየሁ፡**

በመቅረዞቹም **መካከል... የሰው ልጅ የሚመስለውን አየሁ፡...**

154 አቤት! አስተውላችኋል? ከዋክብት፡ ሻማዎች፣ እና ኩራዞች። ምን ማለት ነው? ምን ማለት ነው? እየኖርንበት ያለው ዘመን ማታ ነው፡ ሻማዎች እና ኩራዞች እና ኮከቦች ማለቱ ሌሊት እንደሆነ ነው። የኮከብ ሥራስ ምንድነው? ፀሐይ እስክትመለስ ድረስ የፀሐይ ብርሃንን ያንጸባርቃል። የጌታ ስም የተባረከ ይሁን! እውነተኛ የሆነ የእግዚአብሔር አገልጋይም የባትሪ ብርሃን፡ የክብሪት ግንድ፡ አንዳንድ የልጥ እሳት አያንጸባርቅም፡ የክርስቶስን ወርቃማ ጨረሮች ግን ለቤተክርስቲያኑ ያንጸባርቃል፡ ምስክረንቱም "እሱ አንድ ነው፡ ሕያውም ነው፡ እሱም በእኔ ላይ ያበራል።" አሜን! እሱ የሚያንፀባርቀው ብርሃን ይህ ነው። ከዋክብት የጸሃይን ብርሃን እንደሚያንጸባርቁ፡ እያችሁ፡ እኛም የእግዚአብሔር ልጅ ብርሃን እናንጸባርቃለን። ብርሃንን እየሰጠ፡ የሰራውን ያንኑ ስራ እንሰራለን። ምን አይነት ብርሃን? ለሚፈልጉ የወንጌል ብርሃን።

155 እስኪ አሁንም 13ኛው ቁጥር እንየውና፡ ትንሽ ጠለቅ ብለን ደግሞ እንመልከተው።

**በወርቅ መቅረዞቹም መካከል** (መኃል ማለት ነው) **የሰው ልጅ... የሚመስለውን እየሁ፡ እርሱም እስከ እግሩ ድረስ ልብስ የለበሰው፡ በጡቶቹም ዙርያ በወርቅ መታጠቂያ** የታጠቀ **ነበር።**

156 አሁን ይህ ትምህርት የጌታ ቀን ስለመሆኑ ትክክለኛ ስለመሆኑ ተጨማሪ ማረጋገጫ ይህ ነው። እሱን አስተውላችሁታል? በዚህ ጊዜ ካህን፡ ወይም ንጉስ አልነበረም፡ ዳኛ ነበረ እንጂ። አስተውሉ፡ ካህን፡ ወይም ሊቀካህን፡ ወደ መቅደስ ሲገባ፡ ወይም አገልግሎት ሲያገለግል፡ በወገቡ ዙርያ ላይ ይታጠቃል። በትከሻው ላይ በጭራሽ አያስረውም፡ መታጠቂያውን በወገቡ ላይ ማሰሩ፡ እያገለገለ ነው ማለት ነው። ይሄኛው ሲወጣ ግን፡ ከላይ በኩል መታጠቂያውን አስሮ፡ በትከሻው ላይ መታጠቂያውን አድርጎ፡ በደረቱ፡ በጡቶቹ ዙርያ፡ ወርቃማ መታጠቂያ ታጥቋል፡ ከፍ አርጎ ታጥቆታል። ምንድነው? ጠበቃ፡ ዳኛ ነው። ዳኛው መታጠቂያውን እዚህ ትከሻው ላይ፡ ከፍ አርጎ ታጥቆ እንጂ፡ እንደ ካህን ወደ ታች አላወረደውም። እያችሁ፡ ይህ የሚያሳየው በክህነት ሰራው ላይ አለመሆኑን ነው፡ ዮሐንስ እስከ ጌታ ቀን ድረስ ተጉዞ ፈራጅ ሆኖ ሲመጣ አይቶታል።

157 ዳኛ እንደሆነ ታምናላችሁ? ቅዱስ ዮሐንስ 5፡22፣ ፈጥነን እናንብብ፡ ዳኛ መሆኑን ወይም አለመሆኑን እናያለን። ቅዱስ ዮሐንስ 5፡22:

**ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ** አይፈርድም፡

158 ልክ ነው? እርሱ ዳኛ፡ የበላይ ዳኛ ነው። ዮሐንስም እንደ ነቢይነቱ፡ በትንቢት ቀኑ እንዳላየው ያሳያል፡ በጌታ ቀን እንደ ፈራጅ እንጂ፡ ስለ ንግሥናው ዘመንም እንኳን አልፎ አላየውም። አሁን፡ ካህን መታጠቂያውን ወገቡ ላይ ማድረጉ፡ በአገልግሎት ላይ መሆኑን ሰንቶች ታውቃላችሁ? ኪዳኑን ያነበበ፡ ብሉይ ኪዳንን የሚያውቅ ሁሉ፡ ይህን ያውቃል። ካህን እዚህ ዙርያ ሲታጠቅ፡ አገልግሎት ላይ ነው፡ አገልጋይ ነው ማለት ነው። እሱ ግን እዚህ ጋ ከፍ አርጎ ታጠቀ፡ ዳኛ ነው።

159 ትንሽ ጠለቅ ብለን እናንብብ፦

... **የወርቅ መታጠቂያ...** ነበር... **በጡቶቹ ዙርያ...**

160 ልክ ነው፡ **እዚህ** አካባቢ ነው፡ ዳኛ ነበርና።

ቀጥለን የእርሱን ሰባት መአዝናዊ የሰብእናው ክብር መገለጫዎች እናነባለን። ኦህ፡ ማይ! ገና ሳልገባበት ይህ ጩክ ጩክ ይለኛል። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] አስተውሉ! ኦህ፡ ይህ በጣም አስደናቂ ነገር ነው። አዳምጡ፡

እና **ራሱንም**...

161 አሁን ተከታተሉ፡ ሰባት ነገሮቹ፡ እዚህ ተጠቅሰዋል፡ ራሱ፣ ጸጉሩ፣ አይኑ፣ እግሩ፣ ድምፁ፣ የጠቀሳቸው ሰባት ነገሮች አሉ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰባት መአዝናዊ ክብር። እናንብበው፦

ራሱና የራሱ **ጠጕርም እንደ ነጭ የበግ ጠጕር፡ እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፡... ዓይኖቹም...** እንደ **እሳት** ነበልባል **ነበሩ፡**

… **እግሮቹም**… በእቶን **የነጠረ፡ የጋለ** ናስ ይመስሉ **ነበር፡ ድምፁም… እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ ነበረ።**

**በቀኝ** እጁም… **ሰባት ከዋክብት ነበሩት፡ ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ** ወጣ፡ **ፊቱም በኃይል** እንደሚበራ እንደ **ፀሐይ ነበረ።**

162 እንዴት ያለ ራዕይ ነው! እዚህ ምን አየ? በምሳሌነት፡ የከበረ የእግዚአብሄር ልጅን አየ። አሁን፡ እን—እንዘጋጅ አሁን።

163 ኦህ፡ ማይ፡ ገና ስምንት ሰዓት ነው፡ ዘጠኝ የሆነ ምስሎኝ ነበር። ገና መች ጀመርኩ። እሺ። ጥሩ ነው። እንደው፡ ይቅርታ አርጉልኝ፡ እነዚህ ወንድሞች ቆመው ሳያቸው አዝናለሁ፡ እያችሁ፡ ምክንያቱም እግሮቻቸው እንደሚያማቸው አውቃለሁ። ወንድሞቼ ለማንኛውም፡ ማድረግ የምችለውን ነገር ቢኖረኝ፡ በእውነት አደርግላችሁ ነበር። አሁን፡ ይህ እንዲገባችሁ በጣም እፈልጋለሁ። ትንሽ ቆማችሁ ታገሱ እግዚአብሔር አብዝቶ እንዲባርካችሁ፡ ጸሎቴ ነው።

164 አሁን—አሁን አስተውሉ፡ የመጀመሪያው ነገር፡ አሁን ያስተዋልነው፡ ራሱና የራስ ጸጉሩ እንደ በግ ጠጉር ነጭ ነበር። ራሱና የራስ ጸጉሩ እንደ በግ ጠጉር ነጭ ነበር። አሁን፡ ይህ ማለት፡ አርጅቷል ማለት አይደለም። ምክንያቱ ያ አልነበረም። ይህን ለመሰራት ገና አላረጀም። ይህ ግን… ከክህሎቱ ብዛት ከብቃቱ እና ከጥበቡ ብዛት የተነሣ ነው። ምክንያቱም እሱ ዘላለማዊ ነው፡ ዘላለማዊው የሆነ ነገር አያረጅምና። ገብቷችኋል?

165 አሁን ወደ ዳንኤል እንሂድና፡ እዚህ ጋ—እንደዚሁ እንሰልዋለን፡ ምን እንደሆነም ይገባናል። አሁን፡ ለአንድ ደቂቃ ዳንኤል 7፡9 ላይ፡ እንክፈት፡ በዳንኤል ላይ እሱ በሚመጣበት… በዘመናት ወደ ሽመገለው ሲመጣ ተመሳሳይ ሥዕል ታያላችሁ። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር፡ የሆነ ሰው ሁሉ፡ አሁን ወዴት እንደምንሄድ በትክክል ያውቃል። ዳንኤል 7፣ እና 9 ኛ ቁጥር፡ በ8ኛው እጀምራለሁ፦

ቀንዶችንም **ተመለከትሁ፡** እነሆም፡ **በመካከላቸው… ሌላ ትንሽ ቀንድ ወጣ፡ በፊቱም—በፊቱም ከቀደሙት ቀንዶች ሦስት ተነቃቀሉ፡ እነሆም፡** በዚያ **ቀንድ**… **እንደ ሰው፡ ዓይኖች የነበሩ ዓይኖች፡ በትዕቢትም የሚናገር አፍ ነበሩበት።**

**ዙፋኖችም እስኪዘረጉ** ድረስ **አየሁ**…

166 አሁን አዳምጡ። አሁን፡ በደንብ ተከታተሉ። ከኋላ ያላችሁ ብደንብ ትሰሙኛላችሁ? እስኪ እየተሰማችሁ ከሆነ "አሜን፡" በሉ። ባለቤቴን ጠየቅኳት። ይመስለኛል ይሄኛው ማይክ… የተሻለ ይመስለኛል፡ አይደለም'ዴ? እዚህኛው ላይ፡ በጣም የጮህኩ፡ ይመስለኛል፡ አሁን።

167 እሺ፡ አሁን ወደ ዳንኤል 7፡9፦

**ዙፋኖችም እስኪዘረጉ** ድረስ **አየሁ፡ በዘመናት የሸመገለውም ተቀመጠ፡** ልብሱም **እንደ በረዶ ነጭ፡ የራሱም ጠጉር** እንደ… **ጥሩ ጥጥ ነበረ፡** (በዘመናት የጥንት።) **ዙፋኑም የእሳት ነበልባል ነበረ፡ መንኰራኵሮቹም የሚነድድ እሳት** ነበሩ።

**የእሳትም—**ፈሳሽ **ከፊቱ ይፈልቅና ይወጣ ነበር፡** ሺህ ጊዜ **ሺህ ያገለግሉት ነበር፡ እልፍ... እእላፋትም በፊቱ ቆመው ነበር፡ ፍርድም ሆነ፡ መጻሕፍትም ተገለጡ።**

168 "ነጭ ፀጉር!" በጥንት ዘመን... የነበሩት ዳኞች እንዲህ መሆናቸውን ሰው ሁሉ ያውቀዋል። ለምሳሌ የእንግሊዝ ዳኞች እንደ በረዶ-የነጣ ነጭ ዊግ ይለብሱ ነበር። ሰንቶች ታስታውሳላችሁ? የድሮ ጥንታዊ ዳኞች ነጭ ዊግ ይለብሳሉ... ምክንያቱም፡ አሁንም ዮሐንስ ወደ ጌታ ቀን መሄዱ በማሳየት፡ እንደ ዳኛ ሆኖ አይቶታል። አሜን! እንደ ካህን፡ እንደ ንጉሥ፡ እንደ ነቢይ ሳይሆን፡ እንደ ዳኛ። አብ (ቅዱስ ዮሐንስ 5፡22 ነው) ፍርድን ሁሉ ለእርሱ ሰጠ። አሁን በህዝቦች ሁሉ ላይ ለመፍረድ የመጣ፡ ዳኛ ነው። አቤት በዚያ ቀን እንዲህ ሆኖ ስታዩት! ዳንኤልም በዘመናት ወደ ሸመገለው ሲመጣ አየው፡ ፀጉሩ እንደ በረዶ ነጭ ነበር። እነዚያ ሁለቱ አንድ ሲሆኑ አይቷል። እሺ፡

... **ፍርድም ሆነ፡ መጻሕፍትም ተገለጡ።**

**የዚያን** ጊዜም... **የዚያን** ጊዜም **ቀንዱ ይናገረው ከነበረው ከታላቁ—ከታላቁ ቃል ድምፅ የተነሣ አየሁ...** (አይ፡ ተሳሰቻለሁ መሰለኝ፡ አይደል? )

169 ዳንኤል 7:9፣ አዎን፡ ይኸው፡

... **መንኰራኵሮቹም**...

**የእሳትም ፈሳሽ** ከፊቱ... **ይፈልቅና ይወጣ**... **ነበር፡** እልፍ **እእላፋትም** መጡ **በፊቱም ያገለግሉት ነበር...**

**የዚያን ጊዜም ቀንዱ ይናገረው ከነበረው ከታላቁ ቃል ድምፅ የተነሣ አየሁ፡ አውሬይቱም እስክትገደል፡ አካልዋም እስኪጠፋ ድረስ፡** በእሳትም—**ለመቃጠል** እስክትሰጥ ድረስ **አየሁ።** (እህም!)

**ከቀሩትም አራዊት፡ ግዛታቸው ተወሰደ፡** (ይህ ሁሉ የአሕዛብ ኃይላትና መንግሥታት ይወድቃሉ) **የሕይወታቸው ዕድሜ ግን እስከ ዘመንና እስከ ጊዜ ድረስ ረዘመ።**

**በሌሊት** ራእይ **አየሁ፡ እነሆም፡ የሰው ልጅ የሚመስል፡ ከሰማይ ደመናት ጋር...** መጣ፡ (በጧት ክፍለ ጊዜ፡ በ3ኛው ቁጥር ሲመጣ ያየነው እንዴት ነበር? የሰው ልጅ፡ በሰማይ ደመና ሲመጣ።) ... **የሰው ልጅ** የሚመስል **ከሰማይ ደመናት** ጋር መጣ፡ **በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፡** ወደ **ፊቱም አቀረቡት።**

**ወገኖችና፡ አሕዛብ፡... በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ፡ ይገዙለት ዘንድ፡** ግዛትና **ክብር፡ መንግሥትም፡ ተሰጠው፡ ግዛቱም የማያልፍ፡ የዘላለም ግዛት ነው፡ መንግሥቱም... መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።**

170 ጸጉሩም እንደ በግ ጠጉር ነጭ ወደ ነበረው በዘመናት ወደ ሸመገለው መጣ። ዮሐንስም ዘወር ብሎ የሰውን ልጅ የሚመስል በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል ቆሞ አየ፡ እንደ በረዶ-የነጣ ነጭ ፀጉር፡ ዳኛው! የታጠቀው ወገቡ ላይ ሳይሆን፡ ከፍ አርጎ፡ በጡቶቹ ዙርያ የታጠቀ፡ ዳኛ ነው! የዳኛውን መታጠቂያ

በትከሻው ላይ አድርጎ፡ ጵድቁ ያለበት፡ ንጹህ፡ ቅዱስ፡ የተጣራ፡ ከወርቃማ መታጠቂያው ቆሞ ነበረ። ልብሱ! እስከ እግሩ ድረስ የለበሰ ነበር። ስባቱ የሰብእናው ክብር መገለጫ መአዝኖቹን ተመልከቱ።

171 አሁን፡ 14ኛው ቁጥር፡ ይመስለኛል፦

> **የራሱ** ጠጉርሞ... **ራሱና የራሱ** ጠጉርም እንደ **ነጭ የበግ ጠጉር፡ እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፡ ዓይኖቹም... እንደ እሳት** ነበልባል **ነበሩ፡**

172 ራስ፡ ጸጉር፡ "አይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ።" አስቡት! እነዚያ ድሮ በሰው እንባ ደብዝዘው የነበሩት አይኖች፡ አሁን የእሳት ነበልባል ሆነዋል። በንዴት እንደ ተቆጣ ዳኛ ቆሟል። ለምን ናቅከው? ኦህ፡ ኃጢአተኛ ሆይ፡ ይህን አሰብበት! ለብ ያልከው፡ የቤተ ክርስትያን አባል የሆንከው ሆይ አሰብበት! ካቶሊክ፣ ባፕቲሰት፣ ፕሪሰባይቴሪያን፣ ጴንጤቆሰጤ ሆይ፡ አሰቡበት! ካቶሊኮች ሆይ፡ አሰቡበት! ማርያማችሁ'ኮ መንፈስ ቅዱስ ለመቀበል እስከ በዓለ ኃምሣ ድረስ ተጉዛለች፡ እንደሰከረች ሴት ተንገዳግዳለች። የክርስቶስ እናት ራሷ ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባቷ በፊት ያንን ማግኘት ነበረባት። እናንተ ሴቶች ሆይ ከዚያ ውጪ በምን ትገባላችሁ? ወንዶች ሆይ፡ ሁላችሁ፡ ይህን አሰቡበት!

173 ጸጉሩ፡ እና ዓይኖቹ በአንድ ወቅት የሰው እንባ አቅርረዋል፡ ሆኖም ስለ ዓይኖች አንድ ነገር እንድታሰተውሉ እፈልጋለሁ። ገና በምድር ሳለ፡ በአልዓዛር መቃብር ላይ እያለቀሰ፡ እንደ ሰው በእንባ አቅረዋል። ትክክል! በአዘኔታ የተሞላ፡ ሰውነቱ። ኃጢአትን ያሰወግድ ዘንድ፡ የለበሰው፡ እግዚአብሔር ሰውነት ተላብሶ ነበር። ከዚያ ሰውነት በሰተጀርባ ግን፡ የሰውን ልብ አይቶ ስለ ሰዎች የሚያውቅበት ከበሰተጀርባ ሌላ ነገር ነበረው። ለምን? ሟች ሥጋ ቢለብሰም፡ ከበሰተጀርባው የሆነ ነገር ነበረው።

174 ማን እንደሆነ ግን አላወቁም። እንዲህ አላቸው፡ "እኔ እርሱ እንደ ሆንሁ፡" "ባታምኑ፡ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ።" ትክክል። "እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ፡ አትመኑኝ፡ የአባቴን ሥራ የማደርግ ከሆንኩ ግን፡ እኔን ባታምኑ ሥራውን እመኑ።" አቤት፡ መልእክቱን፡ መገለጡን ለእነርሱ ለማሰረዳት በጣም ሞከረ! ወደ ሰው ልብ አይቶ፡ ሰውየውን ሙሉ ለሙሉ ያውቀዋል። ስለዚያ ናፍቆቴ እጅግ ብዙ ነው! በዚያ በተራራው ላይ የተወጉት፡ የሰቃይን ፊት የተመለከቱ አይኖች፡ እና እንደ ሰው ያለቀሱ አይኖች፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ግን ከሰው እይታ በሰተጀርባ ሁሉንም ማየት ይችላሉ፡ የነበሩ ነገሮች፡ ያሉትን ነገሮች—ያሉ ነገሮች፡ የሚመጡትን ነገሮች። ከመጀመሪያው መጨረሻውን ያውቃል፡ ከእነዚያ የሰው አይኖች ጀርባ እግዚአብሔር ሰለነበረ ነው። እግዚአብሔር ወደ ህይወታችሁ ይምጣ እና ይቆጣጠራችሁ፡ ከዚያ የሚመጡትን ነገሮች ያሳያችኋል። ከዚያ በኋላ ነገሮችን ለማንሳት፡ በእነዚያ ሟች አይኖች አልፎ የሚያየው ወደ ህይወታችሁ የመጣው መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ እናንተ አይደላችሁምና።

175 አቤት፡ ክብር ለእግዚአብሔር! "በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሰሳለሁ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፡ ጎበዞቻችሁ ራእይ ያያሉ፡ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ።" ሃሌ ሉያ! አንዳንድ ጊዜ በእናንተ

በኩል ለማየት እንዲችል እንቅልፍ ያስተኛችኋል፡ ብዙ ጊዜ እንደሚያሳያችሁ እርግጠኛ ነው። “ጎበዞቻችሁ ራእይ ያያሉ፡ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፡ በባሪያዎቼና በባሪያዬ ላይ ከመንፈሴ እፈስሳለሁ።” “በ... ዲያቆኖቼ እና በፓስተሮቼ፡” አይደለም፡ “በተጠማ ላይ፡ በሥጋ ለባሸ ሁሉ ላይ፡ መንፈሴን እፈስሳለሁ።” ለምን እንደምጮህ ትገረማላችሁ፡ ወደነዚህ የቤተክርስቲያን ዘመናት እየመጣ ነው።

176 ኦህ፡ እነዚያ አይኖች፡ ያኔም በዚያ ነበረ። እና፡ አስታውሱ፡ አንድ ቀን፡ እነዚያ እንባን ያነቡ አይኖች፡ እነዚያ ዓይኖች በፍርድ ላይ ይቆማሉ። አሁን በምድር ሁሉ ላይ ወዲያና ወዲህ እንደሚሮጥ እሳታማ ነበልባል ሆነዋል፡ እርሱ ሳያውቀው የሚሆን አንዳች ነገር የለም። ኦህ፡ ማይ፡ ተጽፏል። እያንዳንዱን እንቅስቃሴ፡ ሁሉን አሳቦች እያየ የምትሰሩትን ሁሉ ያውቀዋል፡ የልብ አሳብ ሁሉ፡ ምን ለማድረግ እንዳቀዳችሁ ሁሉ እያየ፡ በምድር ይመላለሳል። ሁሉንም ያውቀዋል። ትወዱት እንደሆነም ያውቃል። እርሱን ለማገልገል፡ አሳባችሁ ቅን እንደሆነም ያውቃል። ሁሉንም ያውቀዋል። ኀጢአት ሁሉ በፊቱ ራቁቱን በሆነበት በዚያ ቀን ስትቆሙ፡ እርሱም በነጩ ዙፋን ፍርድ ላይ ሲቆም እንዴት ይሆን ይሆን?

177 አምላክ ሆይ፡ ከዚያ ቦታ አድነኝ! ያንን ማየት አልፈልግም። የእሳት ነበልባል ከሆኑ አይኖቹ ጋር ቁጣን ተሞልቶ አምላክ ሲንጎራደድ፡ ከጽድቅ ጋር፡ ራሱ ላይ ያንን ዊግ አጥልቆ፡ አይኖቹም የእሳት ነበልባል የሆኑትን የልባችሁን ሁሉ አሳብ የሚያውቁ ናቸው፡ ለማድረግ ያሰባችሁትን የሚያውቁ ናቸው። አቤቱ በዘመናት አለት ንቃቃት ውስጥ ሰውረኝ! ሽማግሌው ወዳጄ ሲዘምር፡ “ይህች አለም ሁሉ በእሳት ስትቃጠል፡ ከጎኔ ቁምልኝ። ከጎኔ ቁምልኝ፡ እቅፍህም ትራስ ትሁንልኝ። በዘመናት አለት ውስጥ ሰውረኝ።” እግዚአብሔር ሆይ፡ ፍርድህን አልፈልግም። አልፈልግም... የምፈልገው ጌታ ሆይ፡ ምህረትህን ነው። ፍርድህን ሳይሆን፡ ምሕረትህን ስጠኝ:: ምህረትህን ብቻ ስጠኝ። ህግ አይደለም፡ ሌላም አይሁን... ምህረትን ብቻ ስጠኝ፡ ጌታ ሆይ፡ የምማጸንህ ያ ብቻ ነው። በእጄ የማመጣው አንዳች የለኝ (ጥሩ አይደለሁም፡ ምስክርነት የለኝም)፡ እንዲሁ ብቻ ወደ መስቀልህ ቀረብሁ። ጌታ ሆይ፡ እኔ የማውቀው ይህን ብቻ ነው፡ በኔ ቦታ ሊሆን አንዱ መጣ።

178 አሁን የሰውነቱ ሰባት መአዝናዊ ሰብእናው ተመልከቱ፡ ያደረጋቸውን ነገሮች ታያላችሁ።

> **ራሱ**... **እንደ ነጭ** የበግ ጠጉር፡ **እንደ በረዶም፡** ነጭ ነበሩ፡ **ዓይኖቹም እንደ**... (እንመልከተው)... **ራሱ... እንደ ነጭ...** እንደ **በረዶም፡ አይኖቹም... እሳት** ነበልባል **ነበሩ፡**
>
> **እግሮቹም በእቶን የነጠረ...** የጋለ **ናስ፡** ይመስሉ **ነበር፡**

179 አሁን ተከታተሉ። እንደምታውቁት፡ እንዴት እንደለበሰ አስተውለናል። ተከታተሉኝ። ራሱ፡ ዓይኖቹ፡ አሁን እንደ ናስ ወደ እግሩ ይወርዳል። ዳንኤል ስለ ዓለም መንግስታት ያየው የወርቅ ራስ፡ እና የመሳሰሉት፡ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ያየው ምስል ጋር አነጻጽሩት።

180 ይህ እዚህ የቆመውን፡ ምን እንደሆነ ተመልከቱት፡ ናስ ነው። ናስ ምን ይናገራል? ናስ ስለ ፍርድ፡ ስለ መለኮታዊ ፍርድ ይናገራል። እንደ አምላክ ወደዚህ ምድር ስለመምጣቱ ፍጹም ዓላማው፡ ሥጋ ሊሆን መሆኑን ያሳያል፡

እሱም ስለእኛ ሞቶ የእግዚአብሔርን ፍርድ፡ መለኮታዊ ፍርድን ወሰደ፡ እና ናስ የሆነውን፡ ጠንካራ፡ እና የማይነቃነቅን መንግሥት ተቀበለ። እንደ ናስ ጠንካራ ነገር የለም፡ እስከአሁን ድረስ ናስን ማለሰለስ የሚችል አልተገኘም።

181 ፍርድ! ናስ መለኮታዊ ፍርድ ስለመተላለፉ ይናገራል። በምድረ በዳ የናሱን እባብ ተመልከቱት። የናሱ እባብ ምንን ያመለክታል? እባቡ ኃጢአትን ይወክላል፡ ዳሩ ግን፡ ናስ መሆኑ፡ በኃጢአት ላይ ፍርድ እንደተሰጠ ያስረዳል።

182 አሁንም፡ የጥንቷ የቤተ ክርስትያን ዘመን፡ ያቺ ትንሿ ክር፡ ኤልያስን እንደ ነብይ በናቀች ጊዜ፡ በኤልያስ ዘመን የነበረው አስቡ። በቅርብ ቀናት ደግሞ እስራኤልም፡ የቤተ ክርስትያን ዘመናት እንደነበሯትና፡ በትክክል የእነዚህ ጥላ መሆናቸውን አሳያችኋለሁ። እናም በቤተ ክርስቲያናቸውም ዘመን፡ በኤልያስ ዘመን፡ እርሱን እምቢ ባሉት ጊዜ ለሶስት አመት ተኩል ዝናብ አልነብረም። ያ ነብይም እንዲህ ብሎ ተናገረ "ሰማይ ናስ መስሏል አለ፡" አምላክን በመካዳቸው እና ኤልዛቤልን በመስማታቸው በሕዝብ ላይ መለኮታዊ ፍርድ ሆነ።

183 ናስ ደግሞ መሥዋዕቱ በተገደለበት፡ በናስ የተሠራ መሠዊያ፡ በተገደለበት መሠዊያ ላይ መለኮታዊ ፍርድን ይወክላል። መሠረቶቹም ናስ ነበሩ፡ ፍርድ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ጽኑ የቁጣው ወይን መጥመቂያ ረገጠው እና ፍርዳችንን በእርሱ ላይ ወሰደ። አንድ ደቂቃ ብቻ፡ ራእይ 19፡15 እንክፈትና፡ ያደረገውን እንይ። ራእይ 19፡15 ላገኘው ከቻልኩ፡ ለአፍታ እናንብብ። አዎን፡ እስኪ ከቁጥር… ከቁጥር 12 አካባቢ፡ እንጀምር።

> **ዓይኖቹም… እንደ እሳት** ነበልባል **ናቸው፡ በራሱ ላይም** ዘውድ ነበረ፡ **ብዙ ዘውዶች አሉ፡ ከእርሱም… በቀር፡ አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው።**
>
> **በደምም** የተረጨ **ልብስ ተጐናጽፎአል፡** ስሙም **የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል።** (አሁን፡ አስታውሱ፡ ስሙ የእግዚ አብሔር ቃል አልነበረም፡ ስሙ ግን ያ ተባለ። አያችሁ? )… **ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተባለ።**
>
> **ሰራዊቱ ሁሉ… በሰማይም… ያሉ ሰራዊት ሁሉ ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው፡ በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው፡ ይከተሉት ነበር።**
>
> አሕዛብንም **ይመታበት ዘንድ፡ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፡ እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል፡ እርሱም** ይረግጣል… (ምን ይረግጣል? )… **እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያ** ይረግጣል።

184 ምን አደረገ? ኃጢአተኞች በመሆናችን የእግዚአብሔር ቁጣ በእኛ ላይ ነበረ። ልክ ነው? ማንም ራሱን ማዳን አልቻለም። ማድረግ የምንችለው ምንም ነገር አልነበረንም፡ ሁላችንም "በኃጢአት ተወልደን፡ በአመጽ ተቀርጸን፡ ውሸት እየተናገርን ወደ ዓለም መጥተናል።" እና ምን አደረገ? ሃሌ ሉያ፡ ወደ ምድር መጥቶ፡ የወይን መጥመቂያውን ረገጠው! የልዑል እግዚአብሔር ቁጣ ሁሉ በእርሱ ላይ ፈሰሰ። "የእግዚአብሔር በግ ሆይ፡ ታርደሃልና፡

ይገባሃል።" የዓለምን ኃጢአት በእርሱ ላይ ወሰደ፡ ኃጢአታችንንም ተሸከመ፡ እግዚአብሔርም የቍጣውን መዓት በእርሱ ላይ አፈሰሰ። "እርሱም ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ ስለ በደላችን ደቀቀ፡ የደህንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፡ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።" እንደዚያ ሰው የሞተ አንድም ሰው የለም! በሰውነቱ ውስጥ ደምና ውሃ እስኪለያዩ ድረስ ተሠቃየ። ከመሞቱም በፊት የደም ጠብታዎች ከቅንድቡ ይንጠባጠብ ነበር።

**... ሁሉን የሚችለው አምላክ... የቁጣው... የወይን መጥመቂያው... ጽናት።**

185 (ክብር!) አንድ ቀን እነዚያ የፍርድ የናስ እግሮች፡ ፈራጅ ሆኖ ሲመጣ፡ የክርስቶስ ተቃዋሚውንና፡ ጠላቶቹን ሁሉ ይረግጥበታል። ሃሌ ሉያ! የብረት በትር በእጁ ይዞ በምድር ላይ ይሄዳል። አሜን! ኦህ፡ ኃጢአተኛው ወዳጄ ሆይ፡ ለንስሃ ጊዜ ሳለ፡ ንሰሐ ግባ። ለመርሳት መክር፡ እና ዳግም የማትከሰት ትንሽ ታሪክ መሆኗን ብቻ አሰባት። ዳግም ይከሰታል! "በእኔ ላይ ዳግም አይከሰትም።" በእናንተ ላይ ይከሰታል እንጂ!

186 በናስ እግሮች፡ ጠላቶቹን ይረግጣል። ምክንያቱም ለኃጢአታችን ዋጋ ለመክፈል የእግዚአብሔርን ጽኑ ወይን መጭመቂያ ለመርገጥ መከራ ተቀብሏል። እኛ ግን፡ በደለኞች፡ ምስኪኖች፡ የተራቆትን ትሎች ስንሆን፡ ትንሿን አፍንጫችንን አውጥተን የክህደት መጽሐፍ እናነብ እና "አምላክ የለም" ብለን ለማሰብ እንጣጣራለን፡ "**እንዲህ** ብሎ ነገር የለም ፍርድም ሊመጣ አይችልም፡" እንላለን። እነዚያን የነሐስ እግሮች በመጠቀም ጠላቱን ያደቅበታል። የክርስቶስ ተቃዋሚ ላይ ይዘምትበታል። እነዚያን ከሃዲ አብያተ ክርስቲያናት ወስዶ ወደ ማዶ ወንጭፎ ይጥላቸዋል፡ ጨርሳ ወደምትጠፋበት ወደሚባላ እሳት ይወረውራታል። በምድርም ላይ እርሱ እና ቤተክርስቲያኑ፡ ለዘላለም ይነግሣሉ። ክብር!

187 "ራሱ፡ ነጭ እንደ በግ ጠጉር፡" ጽድቅ፣ ክህሎት፣ እንደበተ ርቱዕነት፣ ብቃት፣ ጥበብ። ዘመናት ያሰቆጠረ፡ ነጭ፡ ስለ ሽምግልናው፡ ስለ ጥበቡ ይናገራል። ስራውን ይመዝናል። የጥበብ ሁሉ—እርሱ የጥበብ ምንጭ ነው። የክህሎት ምንጭ እርሱ ነው። እርሱ የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ነው፡ ስለዚህ የሰው ልጅን በሚመስል በዚህኛው፡ ነጭ ፀጉር ተንጠልጥሎ ለብሶ በነበረው ተመስሏል። ዳንኤልም ብዙ መቶ ዓመታት በፊት፡ ሰባት መቶ ዓመታት በፊት አይቶት፡ እንዲህ አለ፡ "በዘመናት የሸመገለው ብሎታል። የሰውንም ልጅ የሚመስል በኃይል መጥቶ ከዚህ በዘመናት ከሸመገለው ጋር አንድ ሆነ፡ ፍርድም ሆነ።"

188 አሁን አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ለአንቺ ለብ ላልሽው ቤተክርስቲያንን እናገራለሁ። ጌታን ሊቀበሉ አሥር ደናግል ወጡ፡ አምስቱ ልባሞች፡ አምስቱ ሰነፎች ነበሩ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ያንን የተዳቀለ ዛፍ እንዳየነው ነው። አሁን፡ አስታውሱ፡ እግዚአብሔርን ለመገናኘት ሲወጡ... አሁን ተመልከቱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ "መጽሃፎቹ ተከፈቱ፡" ይላል። ዳንኤል 7:9፡ "መጽሃፎቹ ተከፈቱ።" ያ የኃጢአተኛው መጽሐፍ ነው። "ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ።" ከእርሱ ጋር ማን መጣ? ቤተክርስቲያን በንጥቀት መጣች። ኦህ! "እልፍ

አእላፍ ጊዜ እልፍ አእላፍ ከእርሱ ጋር መጥተው አገለግሉት፡” ሚስቱ፡ ሙሽራይቱ። ኦህ፡ ክብር! ሚስቱ፡ ቤተክርስትያን ከእርሱ ጋር መጣች።

189 ፍርድ ሆነ፡ መጻሕፍት ተገለጡ። ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ፡ እርሱም ተኝታ የነበረችው ድንግል ነበረች፡ ለእያንዳንዱም ከመጽሐፋ እንዲህ ተፈረደበት። ይህን ያላደረግክበትን ምክንያት እንድትሰጥ ትጠየቃለህ፡ ከዚያስ ምን ይውጥሃል? አሁን በደንብ ገብቶሃል፡ በደንብ ገብቶሃል። ከዚህ በፊት አታውቁት ይሆናል፡ አሁን ግን አውቃችኋል። አያችሁ? ይህ ጻድቅ በጭንቅ የሚድን ከሆነ፡ ያ ኃጢአተኛውና አመጸኛው ሰው ወዴት ይገኛል? ሲያቃልል የነበረ ሁሉ፡ መልካም ለማድረግ አውቆ ያቃለለ። ወዴት ይገኛሉ? እግሩ እንደ ናስ፡ መለኮታዊ ፍርድ ነው።

190 አሁን፡ እንየው፡ ተቃርበናል… አሁን ወደ ገጹ ፍጻሜ ደርሰናል፡

> … ጠጉርም **እንደ በግ ጠጕር፡… ዓይኖቹም… እንደ እሳት** ነበልባል ነበሩ፡
>
> **እግሮቹም—በእቶን የነጠረ… የጋለ ናስ፡… ይመስሉ ነበር፡ ድምፁም… እንደ ብዙ** ውኃዎች **ድምፅ ነበረ።**

191 “የብዙ ውኃዎች ድምፅ።” **ውኃዎች** ምን ይወክላል? ምልክት ለማድረግ ከፈለጋችሁ፡ ራእይ 17፡15 ክፈቱ፡ እና መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ታገኛላችሁ፡- “ያየሃቸው ውኃዎች ወገኖችና፡ ብዙ ሰዎች፡ አሕዛብም፡ ቋንቋዎችም ናቸው።”

እሺ፡ **ድምጽ**። በህይወት ባህር ላይ ለምትንሳፈፍ ነፍስ ምንኛ የሚያስፈራ ነገር ነው፡ መሪ እና አብራሪ በሌለበት፡ ተለቆ፡ በማዕበል ለሚናወጥ ነፍስ፡ እንዲያ የመሳሰሉ ታላላቅ ነውጦች፡ ፏፏቴዎች ሲሰማ ምንኛ ያስጨንቃል! ለሚንከራተት ነፍስ ምንኛ የሚያስፈራ ነገር ነው! “የብዙ ውኃዎች ድምጽ።” የእሱ **ድምጽ** ምንድን ነው? ፍርዱ ነው፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ለሰዎች ሁሉ በእያንዳንዱ ዘመን፡ ቆሞ የሚጮኽ፡ የአገልጋዮች ሁሉ ድምጽ ነው፡ የሚጮህ የብዙ ውኃዎች ድምጽ፡ የብዙ ህዝብ፡ እና የወገኖች፡ ለእያንዳንዱ ዘመን፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀጥ የሰበኩ፡ በእጁ የነበሩ የሰባቱ ከዋክብት ድምጽ፡ በኢየሱስ ስም መጠመቅ፡ በልሳኖች መናገር፡ የእግዚአብሔር ኃይል፡ የክርስቶስ ትንሣኤ፡ ዳግም ምጽአት፡ መለኮታዊ ፍርድ ድምጽ ነው። የብዙ ውኃዎች ድምፅ ከዚህ የሰው ልጅ ከሚመስለው የሚወጣ ድምጽ ነው፡ ብዙ ውኃዎች።

192 ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ እና መንፈስ ቅዱስንም መቀበል እንዳለብህ በሚነገርህ ሰብሰባ መቀመጥህ ማወቅህ ምን ይጠቅምሃል፡ ወይስ በተሰበሰብክበት ጉባኤ ለምትንከራተት ነፍስ ያ ድምጽ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ፡ ሲሰበክ ሰምታ፡ ለማትቀበል ነፍስ ማወቅ ትርጉም የለውም። ወደ ዘላለማዊ ጥፋት የሚወስድህ ታላቅ ማዕበል፡ ታላቁ ፏፏቴ ከሰርህ ነው።

193 የብዙ ውኃዎች ድምጽ፡ አራተኛው ሰብእና ነው። የብዙ ውኃዎች ድምጽ። የዛሬ ድምጽ እየተቀዳ፡ በአርያም በሚቀዳበት ጊዜ ምን ይውጥሃል? ድምጻችሁ የተመዘገበ ነው። አሳቦቻችሁ የተመዘገበ ነው። “ሰው በልቡ እንዳሰበ፡ እንዲሁ ነው።” አስተውሉ፡ በሰማይ ላይ ድምጻችሁ አብልጦ ይሰማል… ማለቴ፡ በምድር ከሚሰማው ድምጻችሁ ይልቅ በሰማይ ላይ አሳባችሁ አብልጦ

ይሰማል። በእርግጠኝነት፡ እንደዛ ነው። እግዚአብሔር የልብን ስሜት እና አሳብ ያውቃል፡ እርሱ ሁሉንም ያውቃል።

194 ፈሪሳዊውንም፡ "እናንተ ግብዞች፡ ከልብ ሞልቶ የተረፈውን አፍ ይናገራልና፡ መልካምን መናገር እንዴት ትችላላችሁ? 'ቸር፡ መምህር፡' ትሉኛላችሁ፡ እኔ ግን ከልባችሁ እንዳይደለ፡ እናንተን አይቼ አውቃችኋለሁ። ግብዝ መሆናችሁን አውቄአለሁ።"

195 ኦህ፡ ያ ድምጽ ከብዙ የቤተ ክርስትያን ዘመናት የተነሣ ከብዙ ውኆዎች ድምጽ የተነሣ፡ ነጎድጓድ በሚፈጥርበት ጊዜ ምን ይሆን ይሆን?

196 አሁን ሌላ ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ለእናንተ የዳናችሁ ሰዎች አንድ ነገር ልበላችሁ፡ ይህን ልንገራችሁ።

197 አሁን፡ አንተ ተንከራታች ነፍስ ሆይ፡ እናንተ በሚናወጠው ማዕበል የምትወዛወዙ ምስኪን ተንከራታቾች ሆይ፡ ተጠንቀቁ። በዚያን ጊዜ ለእናንተ የቀረ መዳን እንደሌለ ስታውቁ በጣም አስቃቂ ነገር ይሆንባችኋል። ያኔ መዳን አትችልም፡ ጥፋትህ በፊትህ እንደቀረበ ታውቃለህ። አንተ ይህን እንደተረዳህ በደቂቃ ውስጥ ድምጽ እንዲህ ሲናገርህ ትሰማለ፡ "እናንተ አመጸኞች፡ ለዲያብሎስ እና ለመላእክቱ፡ ወደተዘጋጀላቸው ዘለአለማዊ እሳት ሂዱ ከእኔ ራቁ።" ከዚህ በተለያችሁ ጊዜ የእነዚያን ሁሉ ጉባኤዎች ድምጾች እንደ ሚጮኽ ፏፏቴ ሆኖ፡ በሰማችሁ ጊዜ ያኔ ታዉቁታላችሁ። አቤት፡ እንዴት ያለ አስቃቂ ነገር ነው፡ እንዴት ያለ ቅዠት! ሰዎች ሆይ፡ ይህ በእናንተ እንዲፈጸም አትፍቀዱለት። ንስሐ ግቡ፡ አሁን ለመታረቅ ጊዜ ሳላችሁ፡ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ።

198 አሁን ሌላ ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ፡ ተረጋግቶ አርፎ ከለመለመው ዛፍ ስር ተደግፎ የሚፍለቀለቅ ፈፋን እንደመሰማት፡ የበለጠ ጣፋጭ ነገር ለሰው ምንድነው? አቤት፡ አቤት፡ አቤት! ያ ማለት በደስታ እየፈለቀ ከሚያነጋግራቸው ከእግዚአብሔር ድምፅ ጋር በሰማያዊ ሰፍራ አርፋ የተቀመጠች ቤተ ክርስትያን ማለት ናት። ምን እንደሆነ ተመልከቱ? ለኃጢአተኛው ኩነኔ ነው፡ ለዳኑት ግን በረከት ነው። ጀልባውን በክርስቶስ ኢየሱስ፡ በአለቱ ላይ አስደግፎ፡ ተማምኖ እርፎ እንደሚያዳምጥ ሰው፡ እንዴት ማረፍ ይችላል! ወደ እረፍቱ ገብቶ።

199 የውኃ ጅረት የሚወርድበት ቦታ መሄድ በጣም እወዳለሁ። አሣ ማጥመድ ወይም ሌላ ነገር ሰንወጣ፡ አብዛኛውን ጊዜ ውኃዎቹ የሚንቦራጨቅበት ቆንጆ ቦታ ለማግኘት እሞክራለሁ፡ ምክንያቱ እረፍት እንድታርፋ ያደርጋችኋል። ሌሊቱን ሙሉ ሲያወራኝ እሰማዋለሁ። ኦህ፡ ማይ!

200 ነፍሳችሁን በፊቱ በርጋታ የምትሆንበት ሰፍራ ላይ አግኝታችሁ፡ በክርስቶስ መልሕቅ በእውነት ሰትደገፉ አያምርም? በዚያም ሲያናግራችሁ ድምጹን ትሰሙታላችሁ፡ "የምፈውስህ ጌታ እኔ ነኝ። የዘላለም ሕይወትን የምሰጥህ ጌታ እኔ ነኝ። እወድሃለሁ። አንተ የእኔ ነህ፡ ሰምህን በመጽሐፉ ላይ አኖራለሁ። ዓለም ሳይፈጠር በፊት አውቄሃለሁ። አትፍራ፡ እኔ ነኝ። አትፍራ፡ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ።" ከዚያም እዘምራለሁ፡-

ነፍሴን በእረፍት ቦታ አስደግፌአለሁ፡
በዱር ባሕሮች ላይ መንከራተት ትቼአለሁ፡
በጥልቁ፡ በባሕር ላይ ቁጣው ቢያይልም፡
በኢየሱስ ደህና ነኝ እኔ ለዘላለም።

201 ይሄውላችሁ፡ እናንተን በመልካም የሚያናግራችሁ ያ ድምፅ፡ ኃጢአተኛውን ይኮንናል። ኖህን ያዳነው ያንኑ ውኃ፡ ኃጢአተኛውን አጠፋ። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አያችሁ? "የብዙ ውኃዎች ድምፅ።"

202 አሁን ተከታተሉ፡ "ጸጉሩ እንደ በግ ጸጉር፡ ዓይኖችም እንደ እሳት ነበልባል፡ እግሮችም እንደ ናስ፡ ድምጹ እንደ ብዙ ውኃዎች።"

**በቀኝ እጁም ሰባት ከዋክብት ነበሩት፡**...

203 "ሰባት ከዋክብት።" አሁን 20ኛውን ቁጥር እናነባለን፦

**በቀኝ እጄ ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብትና፡ የሰባቱ የወርቅ መቅረዞች** ምሥጢርም **ይህ ነው፡ ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት** ሰባት **መላእክት** (ሰባት መልእክተኞች፡ ሰባት አገልጋዮች) **ናቸው፡** ያየሃቸው **ሰባቱም መቅረዞች ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።**

204 ምንም አይነት ስህተት እንደማይፈጠር እርግጠኛ ለማድረግ ለእሱ ተረጎመለት። ለእያንዳንዱ ዘመን አንድ መልእክ ነው። አቤት፡ በዚህ ሳምንት፡ ወደ ታሪክ እየተመለስን፡ እና እያወጣን መላእክቶቹን እና ያገለገሉትን አገልግሎት ስንመለከት የሚያምር ሳምንት ይሆንልናል። ተመሳሳይ አገልግሎት ነበራቸው። በዚያች ትንሿ ቤተክርስቲያን ውስጥ በዘመናት ሁሉ ተመሳሳይ ነው።

205 ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ አንድ ሰው፡ እንዲህ አለ፡ "ታውቃላችሁ ስለ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ አባባል አለ፡ እንዲህ ይላሉ፡ 'በዘመናት ሁሉ ጸንታ የቆመች ስለሆነች እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ነች።'"

206 እኔም፡ "መንግስት እና ሌላው ሁሉ ከበስተጀርባ ይዛ፡ ይህን ማዕበል ጸንታ ማለፏ፡ ይህ ምንም እንቆቅልሽ አይደለም። ለእኔ እንቆቅልሽ የሚሆንብኝ ያንን ሁሉ ማዕበል ተቋቁማ፡ በሰይፍ እየተሰነጠቀች፡ ለአንበሶች እየተወረወረች፡ በአልጋ ላይ ታሰራ፡ በአንበሶች፡ እየተበላች፡ እየነደደች... እየተገደለች ወዘተ፡ ታናሿ መንጋ፡ እንዴት ተወጣችው ነው።" የእግዚአብሔርም እጅ ከእነርሱ ጋር እንደነበረ ያሳያል። ይኼው ነው። ዛሬም ብርሃኗ እየነደደ ነው። አሜን! አዎን፡ ወዳጄ!

207 አሁን፡ "በቀኝ እጄ ያየሃቸው ሰባቱ ከዋክብት።" በቀኝ እጁ ሰባት ከዋክብት ነበሩት፡ ይህም ማለት የሰባት ዘመናት ሰባቱ አገልጋዮች ማለት ናቸው። አቤት፡ እንዴት—ድንቅ ነው። ወደ ኋላ ተመልሰን—መልእክቱን ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ያመጣው አገልጋይ እንዲሁ እናገኘዋለን። እንዲሁም መልእክቱንም እስከ ሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን፡ እስከ ሞት የጠበቀው አገልጋይም፡ ለጴርጋሞስ ቤተ ክርስቲያን፡ ለትያጥሮን፡ በዘመናት ሁሉ፡ እስከ ዛሬ ድረስ ጭምር። ብርሃኑን ጠብቀው ያመጡት፡ እንደ መጀመሪያው እንደ ዋናው እያያዝ የያዙት አገልጋዮች ሁሉ፡ ብርሃኑ በእርሱ ዘንድ የመጣው ሁሉ።

208 “በቀኝ እጁ ያዛቸው።” አስቡት! ቀኝ እጅ ማለት ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆመ ማለት አይደለም። እግዚአብሔር መንፈስ ነውና፡ ቀኝ እጅ አለው ማለት አይደለም። ክርስቶስ ግን የስልጣኑ ቀኝ እጅ ነበር። ቀኝ እጅህ፡ ባልንጀራህ—ከጎንህ የሚቆም ጓደኛ፡ በጣም የቅርባችሁ የሆነው።

209 እና፡ አስታውሱ፡ ሰባቱ ከዋክብት በቀኝ እጁ ነበሩ። አስቡት፡ ብርሃናቸውን ለማብራት፡ የሃይል ፍሰት ከእርሱ ዘንድ ይወስዳሉ። በቀኝ እጁ ውስጥ፡ ሙሉ በሙሉ በእሱ ቁጥጥር ስር ነበሩ። አቤት! እውነተኛው የእግዚአብሔር አገልጋይ ሁሉ ተመሳሳይ ነው። ይዟቸዋልና... ማን ሊጎዳቸው ይችላል? ማን ሊጎዳቸው ይችላል? በዚያ ውስጥ ከመላእክት አንዱ በመጀመሪያ እንዲህ ጮኸ። አስታውሱ **መልአክ** ማለት “መልእክተኛ” ማለት ነው። በሳምንቱ ውስጥ ወደ እነዚያ ጥልቅ ነገሮች ውስጥ እንገባለን። **መልአክ** ማለት “መልእክተኛ” ነው። እንዲህ አለ፦ “በክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ማን ይለየናል? በሽታ ነውን? ረሃብ ነውን? እራቁትነት ነውን? ሰይፍ ነውን? ሞት ነውን? እኔ ተረድቻለሁ” አለ ጳውሎስ፡ “በክርስቶስ ከሆነ ከእግዚአብሔር ፍቅር ምንም ሊለየን እንዳይችል ተረድቻለሁ፡” ሙሉ በሙሉ ለቀኝ እጁ የተሰጡ ነንና።

210 አንዱ “ሆሊ-ሮለር! ሆሊ-ሮለር!” ቢላቸው፡ ምንም አያሰጨንቃቸውም። “አንተ ኃይማኖተኛ ወግ አጥባቂ!” ፈጽመው አይሰሙትም። ሙሉ በሙሉ የተሰጡ እና ሕይወታቸውን ከኃይሉ ቀኝ ከክንዱ እየሳቡ፡ ብርሃኑን በየዋህነት፡ ደግነት፡ መልካምነት፡ ትዕግስት፡ ምልክቶች፡ ድንቆች፡ ተአምራቶች ሁሉ ያንጸባርቃሉ። ዓለም “እሰማት ነው” ቢለው፡ ማለት የሚፈልጉት ሁሉ ቢሉት፡ ምንም ለውጥ አያመጣብንም፡ ምክንያቱም እንደተሰጠን እና በቀኝ እጁ እንዳለን እናውቃለንና። አይደንቅም ወይ? አቤት!

211 አሁን ልናደክማችሁ አንፈልግም፡ ፈጠን ፈጠን እንበል። “በቀኝ እጁ፡ ሰባት ከዋክብት።”

212 አሁን ሰባተኛው እና የመጨረሻው የስብእናው ውክልና፦

> **... ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ሰለታም ሰይፍ** ወጣ፡...

ስድስተኛው፡ ማለቴ ነው።

> **... ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ሰለታም ሰይፍ** ወጣ፡...

213 አሁን፡ የብዙ ውኃዎች ድምፅ፡ ከአፉም... በቀኝ እጁ ከዋክብት የነበሩት።

> **... ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ሰለታም ሰይፍ** ወጣ፡...

214 አሁን፡ ባለ ሁለት-አፍ ስለታም ሰይፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እንድታውቁት እንዳስሰዋለን። ዕብራውያን 4፡2ን ውሰዱ፡ ልክ አንድ ወይም ሁለት ገጽ ብቻ ተመለሱና ታገኙታላችሁ፡ አያችሁ። ዕብራውያን ከራዕይ ጀርባ፡ ከይሁዳ በኋላ፡ ዕብራውያን ነው። አሁን፡ በደንብ አስጠግታችሁ ያዙ። ወይም... ዕብራውያን፡ 4ኛ የዕብራውያን ምዕራፍ፡ እነሆ። እሺ፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 4 እና 12ኛው ቁጥር፦

> **የእግዚአብሔር ቃል** ሕያው **ነውና፡ የሚሠራም፡ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፡ ነፍስንና መንፈስን**ም **ጅማትንና ቅልጥምንም፡ እስኪለይ ድረስ ይወጋል፡ የልብንም ሰሜትና አሳብ ይመረምራል።**

215 እእነርሱ ግን “እእምሮ እንባቢ” ይሏችኋል። በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ነው! ሁለት-አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ የተሳለ። እንደው፡ በዚያ ላይ የሆነ ነገር ትዝ አለኝ። የጻፍኩት ማስታወሻ ይኖር እንጃ-... ራዕይ 19 ክፈቱልኝ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። ይህንን እንደገና እንየው፡ ትክክል ይመስለኛል። እንጃ ምናልባት... ራእይ 19፡ ወደ 11፡

> ሰማይም **ተከፍቶ አየሁ፡ እነሆም ነጭ ፈረስ**፡... (ይኸው እዚህ ጋርም ነጭ አለ፡ ፍርድን።) ... የተቀመጠበትም **የታመነና እውነተኛ ይባላል**; በጽድቅም **ይፈርዳል... ይዋጋልም።** (ያ ማን እንደነበረ ታውቃላችሁ፡ አይደል? በጣም ጥሩ።)
>
> **ዓይኖቹም**... **የእሳት** ነበልባል፡... (እሱ ማን ነው? )... **እና በራሱ ላይ**... **ዘውዶች** ነበሩ፡... (ኧረ-አቤት። አሁን ወደ መንገሰ እየደረሰ ነው።) ... **እና ከእርሱም በቀር... እና—አንድ እንኳ የማያውቀው፡ የተጻፈ ስም፡ አለው... ነበረው።**
>
> **በደምም የተረጨ ልብሰ ተጐናጽፎአል፡ ሰሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል።**

216 ከአፉ ምን ወጣ? ምን ሄደ? ነጭ ፈረሰ ጋላቢ። እና፡ ራዕይ፡ 7፣... 8 ይመስለኛል። ነጩ ፈረሰ... አይደለም፡ 6 ላይ ነው። ነጩ ፈረሰ ጋላቢ ሲወጣ፡ ቀ—ቀሰት ተሰጠው፡ ድል ለመንሣት እና ድል ለማድረግ ወጣ።

217 ሰይፍም ከአፉ ወጣ። እሱ ምን ነበር? የራዕይ ነጭ ፈረሰ ጋላቢ። ሰይፉን አስተውሉ። “ሁለት-አፍ ያለው ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፡” ቃሉ። እና፡ በመጨረሻም፡ በቃሉ፡ ለሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች ሲገለጥ፡ አሕዛብን ሁሉ በዚህ በተሳለ ሰይፍ፡ በቃሉ ይረግጣል። አሁን ይህን ሰናየው፡ ምን እንደተፈጸመ እዚህ ጋር እንመልከተው፡

> **እና... ቀኝ እጁ... ከአፉም ሁለት አፍ ያለው ስለታም ሰይፍ ወጣ፡** ፊቱም **በብርታትዋ** እንደምትበራ **ጸሐይ ነበረ።**

218 “ስለታም ባለ ሁለት-አፍ ሰይፍ።” ከዚህ ሰው አፍ ምን ይወጣ ነበር? የእግዚአብሔር ቃል። ባለ ሁለት-አፍ ሰይፍ ነው። ምን እየሰራ ነበር? የልብን ሰሜት፡ እና ሀሳቦችን መለየት፡ ሥጋን አልፎ፡ ሰውነትን፡ የደም ሴሎችን አልፎ፡ ወደ አጥንት፡ ወደ መቅኒም ይወርዳል፡ የልብን ሰሜትና አሳብ እስከሚያውቅ ድረስ፡ ከዚያ በላይ ይዘልቃል። የእግዚአብሔር ቃል የሚያደርገው ይህንኑ ነው።

219 “ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።” እና አሁን ቃሉ ስጋ ሆኖ በቤተክርስቲያኑ ሆኖ፡ በእኛም አደረ። የሚያገለግሉት መላእክቱ፡ በእጁ ናቸው። እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኑ ላይ መሰረት ያደረገ ነው። እግዚአብሔር በጣኦት-አሰራት፡ በባህላዊ ዓለም፡ እየሞተ ላለው ዘመን ወንጌልን ለማስተላለፍ በእኛ እየተደገፈ ነው። እግዚአብሔር ሸክሙን በእኔና በእናንተ ላይ እየጫነ ነው። አሕዛብ ሳያውቁ ቢሞቱ ወዮልን። አቤት፡ የሚነበብ፡ ጽሑፍ፡ እና የሂሳብ ቀመሮች፡ እና ጥቂት ሃይማኖታዊ በራሪ ጽሑፎች፡ ይዘው ይወጣሉ ከሃዲዎችን አፍርተው ይመለሳሉ። ያልኩት ወንጌልን ነው! ወንጌል ቃሉ ብቻ አይደለም። ጳውሎስ እንዲህ አለ። ጳውሎስ ሲናገር “ቃሉን እየተረከ መጣ እንጂ፡ ወንጌል ወደ እኛ

የመጣው በቃል ብቻ አይደለም።" ቃሉ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ቃል... መንፈስ ቅዱስ ወዳለው ልብ ውስጥ በሚዘራበት ጊዜ ቃሉ የሚያዘው ፍሬ ያፈራል። ቃልም የልብ አሳብ ደግሞ ይመረምራል! ክብር! ኦህ፡ ማይ! ኦህ! የልብ አሳቦች እና ስሜቶች መርማሪ ነው፡ ቃል እንዲህ ያደርጋል።

220 ባለ ሁለት-አፍ ስለታም ሰይፍ፡ ከአፉ ይወጣል፡ አሕዛብን ያነቃል። ከእነዚህ ቀናት ውስጥ አንድ ነገር መከሰት አለበት። አዎን! የእግዚአብሔር ቃል፡ ሰሙ የእግዚአብሔር ቃል ተባለ፡ ቃልም ተገለጠ። እዩ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡" ማርቆስ 16፡ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ራሱን ለመግለጥ ከመመለሱ በፊት ለቤተክርስቲያን የመጨረሻ ሰላምታው ነበር። "ወደ አለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ፡" በማለት ቤተክርስትያንን አዘዘ። ምንድን? ወንጌልን ሰበኩ። ማርቆስ 16፡ "ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ።" ያ ምንድን ነው? በሌላ ቃል፡ "የመንፈስ ቅዱስን ኃይል አሳዩ፡" መሆን አለበት።

221 አሁን ተመልከቱ፡ "ለሁሉ... " ቃሉን ማስተማር ብቻ አይደለም፡ "ሂድ ቃሉን አስተምር፡" ብሎ አያውቅም። "ሂዱ ወንጌልን ሰበኩ፡" አለ። ቃሉን ሰበክ ሳይሆን፡ ወንጌልን ሰበክ። "ይህንም ወንጌል ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡ በሰሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፡ እባብን ቢይዙ ወይም የሚገድል ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፡ እጃቸውን በድውዮች ላይ ቢጭኑ፡ ይድናሉ።"

222 "እነርሱም ወጡ፡" ይላል መጽሀፍ ቅዱስ፡ "በሁሉም ስፍራ ሰበኩ፡ ጌታም ቃሉን በሚከተሉት ምልክቶች እያጸና፡ ከእነርሱ ጋር እየሠራ ነበር።" ወንጌል ይህ ነው፡ ወንጌል በተግባር ይህ ነው።

223 እነዚህ ምልክቶች እነማንን ይከተላሉ? እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ፡ እያንዳንዱ ዘመን። ያንን ብርሃን ይዘው፡ የሚጓዙ ታናሽ መንጋዎች አሉ። ኢየሱስ "ታናሽ መንጋ፡ አትፍሩ፡ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነው፡" ማለቱ አያሰገርምም። ታናሽ መንጋ፡ ዘወትር አናሳዎችን እንጂ፡ ብዙኃንን አይደለም።

224 እሺ፡ አሁን አንድ ተጨማሪ ጥቅስ። 20ኛው እንውሰድና፡ እዚህ ቁጥር ላይ እንመልከት። አሁን 16ኛውን፡

> **በቀኝ እጁም ሰባት ከዋክብት ነበሩት፡...**

225 አሁንም... ይህን ደግሞ እንየው... ፊቱም፡

> ... **ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ሰለታም ሰይፍ ወጣ፡** ፊቱም **በኃይል** እንደሚበራ እንደ **ፀሐይ ነበረ።**

226 ማቴዎስ 17 ከከፈታችሁ፡ እስኪ... ይህን እንየው። እስኪ እንደከፈትነው በደንብ እንረዳው፡ እንዲሁ እግረ መንገዳችን ነክተነው እናልፋለን፡ ለሚጽፉ ብዙ ሰዎችም፡ እስኪ... ወይም ማስታወሻ ለምትይዙ፡ ሁላችንም እንድናውቀው እንዲያነቡት እናደርጋለን።

227 ማቴዎስ 17፣ እሺ፡

> **... ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን... ከፍ ወዳለ ተራራ ለብቻቸው** አወጣቸው፡

**በፊታቸውም ተለወጠ፡ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፡ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ።**

228 ተለወጠ። ምን አደረገ? ራሱን ወደ መጪው ቀን አልፎ፡ ተለወጠ። አሁን ተከታተሉ፡ ከዚያ ከጥቂት ሰዓታት በፊት፡ ኢየሱስ ከፊተኛው ምዕራፍ ላይ አንድ አንቀጽ ተናግሮ ነበር፡ "እውነት እላችኋለሁ፡ በዚህ ከቆሙት አንዳንዶች... " ልለው የፈለኩት ሰንቶቻችሁ ገብቷችኋል? "የሰው ልጅ በክብር ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ፡ እዚህ ከቆሙ አንዳንዶች አያልፉም፡ አይሞቱምም።" ልክ ነው? ጴጥሮስን፡ ያዕቆብንና፡ ዮሐንስን፡ ሦስቱን ምስክሮች ወሰደ፡ ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ነገር ሁሉ፡ ትንንሿ ቃል ሳይቀር፡ በሶስት ምስክር ትጸናለችና፡ ስለዚህም ይዟቸው ወደ ረጅም ተራራ ወጣ።

229 መጀመሪያ የመጣውን አስተውሉ። ኦህ፡ እዚህ ላይ ደርሼ ማቆም አልችል፡ ይህን መጨረስ አለብኝ። ተመልከቱ! መጀመሪያ ያዩት ነገር ምንድነው? ኢየሱስን ይዘው ወደ ተራራው ወጡ... ወይም ይዟቸው ወጣ፡ በፊታቸውም ተቀየረ፡ ተለወጠ። ፊቱም እንደ ፀሐይ ብርታት በራ፡ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ፡ ሙሴና ኤልያስም ታዩአቸው። አሁንስ የሰው ልጅ በምን መልክ ይመጣል? በመጀመሪያም፡ ሙሴና ኤልያስ፡ ይገለጣሉ።

230 አሁን፡ ኢየሱስ ወደ ምድር ከመመለሱ በፊት፡ አስተውሉ... አሁን፡ ትንሽ ጊዜ አሳልፈናል፡ የኤልያስ መንፈስ ግን ተመልሶ ወደ ምድር ይመለሳል የልጆቹንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ ይመሰክራልና። ኢየሱስን እዚህ አይተውታል፡ የሰው ልጅ ከብሮ የመምጣት ሥርዓት፡ ሐዋርያቱ እዚህ አይተውታል። ይከብራል እና ተመልሶ ይመጣል። የመጀምሪያው ነገር፡ እርሱን ከማየታቸው በፊት፡ ምን ነበረ? ኤልያስ። ከዛስ? ሙሴ፡ የእስራኤል የሕግ-ጠባቂዎች፡ ወደዚያ መመለስ። ከዚያም የከበረ የሰው ልጅ። ሃሌ ሉያ! የመምጣቱን ቅደም ተከተል ታያላችሁን? የኤልያስ መንፈስ፡ ወይም የመጨረሻው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ምስክር። አያችሁ፡ እርሱን ሊገልጥ በኃይል ይመጣል።

231 ከዚያም መቶ አርባ-አራት ሺህ አይሁድ በሲና ተራራ ላይ ይሰበሰባል፡ በዚያም እስራኤል ሀገር ሆነች፡ በዓለም ላይ እጅግ ጥንታዊው ባንዲራ ያላት፡ በዓለም ላይ እጅግ ጥንታዊው ሀገር፣ አሁን የራሳቸው ሀገር፡ የራሳቸው ባንዲራ፡ የራሳቸው ጦር፡ የራሳቸው ገንዘብ፡ እና ሌላም ነገር አላቸው። ሀገር በመሆናቸው ከሊግ ኦፍ ኔሽን አባሎች አንድ ናቸው። ኢየሱስ ሁሉም ነገር እስኪፈጸም ድረስ ፈጽመው እንደማይጣሉ ተናግሯል።

232 ምስጢር የሚሆነው፡ እነዚያ አይሁዶችም፡ ልክ እንደ ቤተክርስትያኒቱ፡ በእነዚህ ዘመናት፡ እንደገጠማት ሰደት በሁሉም ቦታ ተሰደዱ ተባረሩ ሸሹ ተጣሉ፡ ቢሆንም ግን ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "በለስ ጫፏ ሲለሰልስ ቀንበጧም ሲወጣ ስታዩ፡ ያቺ ሀገር ዳግም ሀገር ለመሆን መመለስ ስትጀምር፡ ያኔ ዘመኑ ቀርቧል፡ በደጅ ነው። እውነት እላችኋለሁ፡ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።" ይህ ጫና... ይህ ህዝብ አያልፍም። ሂትለር ሊገድላቸው ሞከረ፡ ሙሶሎኒ ሊገድላቸው ሞከረ፡ ስታሊን ሊገድላቸው ሞከረ፡ ሌላውን ሁሉ፡ ነገር ግን ፈጽመው አያድፉም፡ ወይም ከምድር አይጠፉም፡ ቆሞ የጸና ሀገር እና ህዝብ ይሆናሉ እንጂ። አሜን!

233 ሙሴና ኤልያስ ይመጣሉ። ኦህ! እንደገባችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

234 እሺ፡ “በኃይል እንደምትበራ ጸሐይ፡” ፊቱ፡ ተለወጠ፡ ተቀየረ። ሌላ ነገርም፡ መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ በራዕይ 21፡23 ላይ። በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም፡ 21፡23 ላይ፡ እርሱ ከተማውን የሚያበራ፡ በዚያ የሚያንጸባርቅ፡ የሚበራ በግ ነው፡ በከተማይቱ ውስጥ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፡ ፀሐይም አትወጣም፡ ምክንያቱም በከተማዋ መካከል ያለው በጉ ብርሃንዋ ይሆናል። የዳኑትም አሕዛብ በበጉ ብርሃን ይመላለሳሉ! አሜን! እርሱ የበጉ ብርሃን ነው። ኦህ፡ በዚህ ደስተኛ አይደላችሁም ወይ?

235 ይህም ብቻ አይደለም፡ በሚመጣው ደግሞ (ዮሐንስ በጌታ ቀን ዘንድ አይቶታልና)፡ እርሱ የጽድቅ ጸሐይ ነው። ወደ ሚልክያስ እንሂድ። የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ነቢይ፡ ሚልክያስ። ሚልክያስ፡ ምዕራፍ 4።

236 እዚያ ቁጭ ብላ ስላለች ውድ ባለቤቴ የምነግራችሁ ትንሽ ታሪክ ይዣለሁ። ከመጋባታችን በፊት አስቸጋሪ ጊዜ እንድታሳልፍ አድርጌአለሁ፡ ከተጋባን በኋላ ለማካካስ ሞክሬ ነበር። እንደገና ማግባት ይኑርብኝ አይኑርብኝ ገና አላወቅኩም ነበር፡ በዚህም ምክንያት በጣም ተሰባበረች። እሷን አግብቶ ለመፍታት የማይገባት መልካም ሴት ስለነበረች፡ የሚንከባከባት መልካም ሰው ቢያገባት ይሻላል ብዬ አሰብኩ። እና እኔ እንኳን ብቁ እንዳልሆንኩ አሰብኩ፡ ሲቀጥልም፡ እንደ ደግነትዋ፡ አልሆንኩላትም። ስለዚህ በቃ አዘነች እና ምን ማድረግ እንዳለባት አታውቅም። ይህ የሆነው ከዓመታት በፊት፡ ማለትም ከሃያ ዓመታት በፊት ነው። በጣም አዘነች፡ ቀን ከሌት ማልቀስ ጀመረች። ከእሷ ለመለያየት እየሞከርኩ ነበር፡ ስለማልወዳት አይደለም፡ ጊዜዋን ማበላሸት ስላልፈለግኩ ነበር፡ ምክንያቱ፡ ሌላ ሰው ማግኘት አለባት፡ አንድ መልካም ሰው፡ ምክንያቱ እሷን እንዲህ አድርጎ መተው የማይገባት መልካም ሰው ናት፡ እና እኔ… ከሷ ጋር መሆኔ እና ወዘተ። እና—እንደምታፈቅረኝ አሰባለሁ፡ እኔም እንደማፈቅራት አውቃለሁ። እንግዲህ እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “እሺ፡ እስኪ ልሞክር… ከሌላ ሴት ልጅ ጋር ልገናኝ ልውጣ፡ እና በእኔ ላይ መጥፎ ስሜት እንዲሰማት ላድርግ ብዬ አሰብኩ።” እንደው እንደ ገደልኳት ነው፡ በኋላ ግን መጥፎ ስሜት ተሰምቶኛል፡ ተሰባብራ ነበርና። እንዲህ አልኳት፡ ነገርኳት፡ “አንቺ በጣም መልካም ሴት ነሽ፡ ጊዜሽን እንዲሁ ማቃጠል—አልፈልግም።”

237 እርሰዋም፡ “ነገር ግን እኔ—እኔ ግን **እወድሃለሁ፡** ቢል፡ መውደድ የምችለው ያ ብቻ ነው።” “እኔ—ሁሌም ስወድህ ኖሬአለሁ፡” አለችኝ።

እኔም፡ “እኔም—እንዲህ መሆኑ አመሰግናለሁ። ግን፡” አልኳት፡ “ታውቂያለሽ፡” እኔ “ጃንደረባ ነኝ፡” አልኳት። “እንደ—ጃንደረባ እኖራለሁ። አየሽ፡ እኔ—ለወደፊትም በጭራሽ ሳላገባ እኖራለሁ፡” አልኳት።

238 ምስኪኗ፡ በነገሩ ላይ፡ እጅግ አዝና ነበር። እና ጥላ ወዳለበት—ወጣች። ወደ ውጭ ወጥታ፡ በጉልበቷ ተንበረከከችና፡ እንዲህ አለች፡ “ጌታ ሆይ፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እኔ አላውቅም። እኔ አንተን አለመታዘዝ—አልፈልግም፡ ቢልን ግን እወደዋለሁ፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝም አላውቅም። ጌታ ሆይ፡ እባክህ ትንሽ መጽናኛ ብቻ ስጠኝ? አቤቱ ትንሽ ብቻ እርዳኝ? ጌታ ሆይ፡ በህይወቴ ከዚህ በፊት ይህን አልጠየቅሁህም፡ ዳግመኛም እንዳልጠይቅህ ተስፋ አደርጋለሁ፡” እንዲህ አለች፡ “እንድትረዳኝ ከፈቀድክ፡ ይህን መጽሀፍ

ስከፍተው፡ አንተም ቃል ሰጠኝ። ሰዎች ያንን አደረግክላቸው ሲመሰክሩ ሰምቻለሁና።” በከፈተችው ጊዜ፡ ሚልክያስ 4 ነው፡

> **እነሆ፡ ከሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን** በፊት—**ነብይ ኤልያስን** ስጥቻችኋለሁ... ወይም **ልኬላችኋለሁ፡**

239 “ምንም ይሁን ልንጋባ መሆናችንን ረክቼ ከዚያ ተነሳሁ፡” አለች። አያችሁ?

> **እነሆ፡ እንደ ምድጃ እሳት የሚነድድ ቀን፡ ይመጣል፡ ትዕቢተኞችና፡ አዎን**፡... ኃጢአትን **የሚሠሩ** ሁሉ፡ **ገለባ** ይሆናሉ፡ **የሚመጣውም ቀን ያቃጥላቸዋል፡** ሥርንና **ቅርንጫፍንም አይተውላቸውም፡ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።**

> **ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ... የጽድቅ ጸሐይ** (S-u-n) **ጸሐይ ትወጣላችኋለች ፈውሰም በክንፎችዋ** ውስጥ ይሆናል፡...

240 “በኃይል እንደሚበራ ጸሐይ።” ኦህ! የእግዚአብሔር ልጅ ዛሬ ማታ በኃይል በመካከላችን ይብራ። እዚህ እንደ ዳኛ በሰባት ድርብ ሰብዕናው በሰባት የወርቅ መቅረዞች መካከል ቆሟል። ስለ እኛ እንደተሰቃየ፡ እና እንደሞተ እና መለኮታዊውን ፍርድ በራሱ ላይ እንደ ወሰደ፡ የእግዚአብሔርንም ጽኑ፡ የወይን መጥመቂያም ረገጠ። ለኃጢአተኛው እርሱ አስቃቂ ማዕበል ነው፡ ለእናንተ ግን በህይወት ባህር ላይ እንደፈታች ነፍስ ነው። ለቤተክርስቲያን፡ በእረፍት የጸና፡ መልካም መድኃኒት፡ በክርስቶስ ፍጹም እርካታ ረክታችሁ በማረፍ ፈፋው ሲፍለቀለቅ እንደመሰማት ነው። እንዴት ያለ ጊዜ ነው! በሞቀ ጨረሩ በእኛ ላይ የሚያበራ፡ “የነበረው፡ ያለዉም፡ የሚመጣውም እኔ ነኝ፡ አትፍራ። እኔ ሁሉን ቻይ ነኝ፡ ከእኔ በቀር ሌላ የለም። አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ፡ ለተጠማም የሕይወትን ውኃ ምንጭ በነጻ እሰጣለሁ።” አቤት፡ እንዴት ያለ ቃል ኪዳን እና እንዴት ያለ ፍቅር ነው! እንዲሁም በከተማዋ መካከል ሌላ ብርሃን የማያስፈልገው በግ ነው፡ በክንፎቹ ውስጥ ፈውስ ያለው የጽድቅ ፀሐይ እርሱ ነው።

> የሸለቆው አበባ፡ ብሩህ የንጋት ኮከብ እሱ ነው፡
> ለነፍሴ ከአስር ሺህዎች ይልቅ የሚሻለው፡
> በኀዘን መጽናኛዬ፡ በችግር ጊዜ ማረፊያዬ፡
> እረፍ ብሎኛል ሸክሜን ሁሉ ለርሱ ጥዬ።
> ሃሌሉያ!
> የሸለቆው አበባ፡ ብሩህ የንጋት ኮከብ እሱ ነው፡
> ለነፍሴ ከአስር ሺህዎች ይልቅ የሚሻለው፡

241 አዎን፡ ወዳጄ! አቤት፡ ታላቁ የንጋት ኮከብ ሊያበራ ሲወጣ፡ ቀጣይ ቀንን እጅ ሊነሣ፡ እንዲህ፡ “ቀኑ ሊበራ ተዘጋጅቷል፡ ልጁም ቀርቧል፡” በማለት ይናገራል፡ እራሱም ከሌሎቹ ከዋክብት ሁሉ ጀርባ (ኦህ፡ ማይ።) በክንፎቹ ፈውስ ይዞ እራሱን ያሰወጣል።

242 አሁን ወደ መልእክታችን እንመለስ። እና ለነገ ምሽት ለመዘጋጀት፡ አሁን እንዘጋለን፡ ምክንያቱም ጊዜው ለዘጠኝ ሩብ ጉዳይ ሆኗል፡ ወደዚህ መመለስ እንድንችል፡ ማንንም ብዙ ማቆየት አንፈልግም።

243 እሺ፡ ፈውስን በክንፎቹ የያዘ የጽድቅ ጸሐይ ነው። ስለ ፊቱ ነው። ዳኛም ነው፡ ሌላም ሳይሆን ደግሞ ወደ ጌታ ቀን መጓዙ ለማሳየት ነው። ታምናላችሁ? ወደ ጌታ ቀን ሄደ እና ጌታን እንደ ዳኛ አየው፡ እንደ ካህን ሳይሆን፡ እንደ ንጉሥ ሳይሆን፡ እንደ ዳኛ አየው። ዳኛ ነው። ይህን አታምኑም? መጽሐፍ ቅዱስ ዳኛ ነው ይላል። እነሆም የሰራውን ሥራ እያሳየ፡ ሙሉ የዳኛ ልብስ ለብሶ ነበር፡ ለሐጢአተኛውም፡ ለክርስትያኑም፡ እንዲሁ ነበር። እነሆም አሁን ከብዙ ውኃዎች ድምጽ ቆሟል፡ ፊቱም በኃይል እንደምታበራ ጸሐይ የደመቀ ነበር።

244 አሁን ውጤቱ፡ 16 ኛው ቁጥር ላይ ነው። "እና... " አይደለም፡ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡ ቁጥር 17 ነው፡

**ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኼ፡ ከእግሩ በታች ወደቅሁ።**

245 አቤት! እንዲህ ያለውን ራዕይ ተመልክቶ፡ ነብዩ መቋቋም አልቻለም። በቃ—ኃይሉን አሟጦ፡ እንደ ሞተ ሰው ከእግሩ በታች ወደቀ። አሁን ተከታተሉ፡

**ቀኝ እጁንም ጫነብኝ፡ እንዲህም አለኝ፡ አትፍራ፡ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፡**

246 ኦህ፡ ማይ! ነብይ አይደለም፡ አምላክ እንጂ! "ፊተኛውና መጨረሻው እኔ ነኝ። የመገለጡ መጀመሪያ እኔ ነኝ፡ የመገለጡ መጨረሻም እኔው ነኝ። የነበረው እኔ ነኝ፡ ያለውም እኔ ነኝ፡ የሚመጣውም እኔ ነኝ።" እስኪ እንየው፡-

**እኔ**... **እኔ ነኝ**...

**ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፡ አትፍራ፡ ፊተኛውና መጨረሻው እኔ ነኝ፡**

**ሕያውም እኔ ነኝ፡ ሞቼም ነበርሁ፡ እነሆም፡ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ፡ ሕያው ነኝ፡** (እዚህ ላይ ነው። እንዲህ በማለት ጮኸ፡) **አሜን፡ የሞትና የሲኦልም... መክፈቻ አለኝ።**

247 አሁን፡ አትፍራ። ለምን እንፈራለን? ቤተክርስቲያን ለምን የእርሱን ቃል ለመጠበቅ... ማሰብ ለምን አቃታት? እስኪ ለአንድ ደቂቃ ብቻ እዚህ እናቁም፡ ምክንያቱም እየዘጋን ነውና። ይህች ቤተክርስቲያን ለምን ትፈራለች? ቃል ገብቶ በፊታችን ያልገለጠው ምን አለ? ቅጣት ወይም ከሞት በኋላ ያለው ህይወት ለምን ትፈራላችሁ "አትፍራ! የነበረውም፡ ያለውም፡ የሚመጣውም እኔ ነኝ። መጀመሪያው እና የመጨረሻው እኔ ነኝ። የገሃነም እና የሞት መክፈቻዎች አሉኝ።" ለምን? "ሁለቱንም ሲኦልን እና ሞትን አሸንፌአለሁና ለእናንተ (ይህም መቃብር እና የነፍሳት ማቆያ፡ ሞት ራሱ፡ የነፍሳት ማቆያ።) ድል አድርጌአለሁ። ሁሉንም ድል ነስቻለሁ። ሲኦልን፡ ሞትን፡ መቃብርን ድል ነስቼዋለሁ።" በምድር ላይ በነበረ ጊዜ፡ እርሱ አንዱና ብቸኛ-...

248 ብዙ ሰዎች ለማሸነፍ ተነስተው ነበር። ይሄን ታውቃላችሁ? ናፖሊዮን ዓለምን ለማሸነፍ ተነሳ፡ በሰላሳ-ሶስት ዓመቱ አሳካው። ከአስራ ሰባት እስከ ሃያ-አምስት አመት እድሜው፡ ናፖሊዮን ራሱን ይገዛ ነበር፡ በመጠጣትም ሆነ በማንኛውም ነገር አያምንም ነበር። ወደ ፈረንሳይ ሄደ። ፈረንሳዊ አልነበረም፡ የተገኘው ከአንድ ደሴት ነው፡ ፈረንሳይን ስለጠላት ጉዳዩን ሊያሳካ ሄደባት፡ ፈረንሳይን አይወዳትም ነበር። ወጥቶም ፈረንሣይን ያዘ፡ ፈረንሳዮችን ማረካቸው ዓለምን ሁሉ አሸነፈ። በኋላ ግን ተሸነፈ። በሠላሳ-ሦስት ዓመቱ

ተቀምጦ አለቀሰ፡ ምክንያቱም ሌላ የሚሸነፍለት የለምና የአልኮል ሱሰኛ ሆኖ ሞተ። ተሸነፈ፡ እራሱን እንኳን ማሸነፍ አልቻለም። አያችሁ? እና ከዚያ የራሱን ዋተርሉ በዋተርሉ ተጠመደ፡ መጨረሻውም በዋተርሉ ሆነ። እኔ እዚያ ነበርኩ እና በምድሪቱ ውስጥ በነበርንበት ጊዜ፡ የጥንት ጥንታዊ ምልክቶችን እና እዚያ ያሉ ነገሮችን አይቻለሁ። አሁን፡ ያንን ድል አድራጊ ብንወስድ፡ በወጣትነት ዕድሜው ድል ለማድረግ የተሳሳተ መንገድ መረጠ፡ ተዋርዶ፡ ሞተ።

249 ነገር ግን አንድ ቀን ደግሞ አንድ ሌላ ወጣት ተነሣ ወደ ዓለምም መጣ። በሠላሳ-ሦስት አመቱ ድል የሚደረገውን ሁሉ ድል አድርጎ ሞተ። በምድር በነበረበት ጊዜ ምኞትን፡ ትዕቢትን፡ በሽታን አሸንፏል፡ ሰይጣኖችን አሸንፏል። በመሞቱ፡ ሞትን ድል አደረገ። በተነሣ ጊዜ፡ ገሃነምን ድል አደረገ። ወጥቶ የሰው ልጆች የሚያስቸግር የነበረውን ሁሉ ድል አደረገ፡ በእግዚአብሔር ወይን መጥመቂያ ውስጥ ገባ ሞትን፡ ሲኦልን፡ መቃብርን፡ ሕመምን፡ ሥርዐትን፡ ሌላውን ሁሉ ረገጠ፡ ሁሉንም አሸንፎ በሦስተኛው ቀን ተነስቶ ከላይ ያሉትን ከባቢ አየር ሁሉ፡ ድል አደረገ፡ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ጭጋግ ቈርጦ፡ ሰማይንና ምድርንም አንድ ላይ አገናኘ። ክብር! ኦህ፡ ማይ! አቤት!

250 መጋረጃውን ለሁለት የሰነጠቀ ኃያሉ አሸናፊ፡ እነሆ ቆሞአል። የሞት እና የገሃነም መክፈቻዎች ከጎኔ አንጠልጥያለሁና፡ "አትፍራ።" ቀኝ እጁን (ስልጣኑን) በእርሱ ላይ ጭኖ፡ በቀኝ እጁ ሰልጣንም እስነሣው፡ አለም፡- "የነበረውና፡ ያለውም፡ የሚመጣውም እኔ ነኝ፡ አትፍራ። መጀመሪያው እና መጨረሻው እኔ ነኝ። ሕያውም እኔ ነኝ፡ ሞቼም ነበርኩ፡ ለዘለአለምም ህያው ነኝ። አሜን!" አቤት!

> እነሆ! ኃያሉ ድል ነሺ፡
> እነሆ! በግልጽ ይታያል፡
> ኃያሉ ድል ነሺ፡ በእግሮቹ ቆሟል፡
> መጋረጃውን ለሁለት ሰንጥቋል።

251 አሜን! በኤደን ገነት እንደነበረው ሕብረት አንድ ይሆኑ ዘንድ፡ ከሰው ልጆች እንቅፋት ሁሉ ቈረጠ። አሁን፡ ሰው... ዝም እላለሁ ብዬ ነበር፡ ነገር ግን ልናገረው። ሰው ሁሉን ቻይ ነው። እናንተ ባታምኑትም፡ እንዲሁ ነው። ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የተገዛ ሰው ሁሉን ቻይ ነው። በማርቆስ 11፡ 22 ላይ፡ እንዲህ አይልምን፡- "በልባችሁ ሳትጠራጠሩ፡ ይሁን የምትሉት ነገር፡ ይፈጸማል። የተናገርከው ማግኘት ትችላለህ" አላለምን።?

252 ሁለት ሁሉን ቻይዎች ሲገናኙ ምን ይፈጠራል? እግዚአብሔር እና ሰው፡ ሁለቱ ሁሉን ቻይዎች ሕብረት ሲያደርጉ፡ የሆነ ነገር ይንቀጠቀጣል። አንዳንዶች-... እርሱ ቃል እንደገባለት አውቃችሁ፡ በእግዚአብሔር ሁሉን ቻይ የመፍጠር ኃይል የምትናገሩት ሁሉ፡ በቃሉም እንደተናገረው አምናችሁ የምትሉ ነገር፡ አድማስን ተሻግሮ የሚፈጸሙ ነገሮች ይዞ ይመለሳል፡ ያልነበሩ ነገሮች፡ እንደነበሩ፡ ያደርጋቸዋል፡ ምክንያቱም ሁለት ሁሉን ቻይዎች ተገናኝተዋል። እነሆ ቆመ! አቤት፡ አይደንቅም ወይ!

253 ተጨማሪ ጥሩ ነገሮች ካገኘን እስኪ እንይ። 18ኛው ቁጥር፣ አሁን 19ኛው ቁጥር። ዮሐንስ፡ ፊቱን ባየ ጊዜ ምን ሆነ? ውጤቱ? በእግሩ ስር ወደቀ፡ ከዚህ

በላይ መቋቋም አልቻለም፡ የሰው ህይወቱ ተሚጠጠ፡ በቃ አልቻለም። ሁሌም ድል ነሺ ነውና፡ ድል ነሺ ነው።

254 አሁን ትእዛዝ ሰጠ፡ እና ይህን 19ኛው ቁጥር፡ ወደ ምዕራፍ መጨረሰ እንጀምራለን።

> **እንግዲህ ያየኸውን፡ አሁንም ያለውን፡ ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ፡**

255 20ኛውን ቁጥር እንግባ፡

> **በቀኝ እጄ**፡... ያየሃቸው **የሰባቱ ከዋክብትና የሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ምሥጢር ይህ ነው። ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርሰቲያናት** ሰባት **መላእክት ናቸው፡ ሰባቱም መቅረዞች ሰባቱ አብያተ ክርሰቲያናት ናቸው።**

256 አቤት! ወዳጆች ሆይ፡ አሰደናቂ ነው። እዩት ከአምላክነቱ ሉአላዊነት ጋር... በሉአላዊነቱ ቆሟል። ዳኛ፣ ካህን፣ ንጉሥ፣ ንሰር፣ በግ፣ አንበሳ፣ አልፋ፣ ኦሜጋ፣ አባት፣ ልጅ፣ መንፈሰ ቅዱሰ፣ የነበረ፣ ያለው፣ የሚመጣው እርሱ ነው። የእግዚአብሔርን ጽኑ የወይን መጥመቂያ ረገጠው፡ ከፍ ከፍ ባለ ጊዜም፡ እግዚአብሔር (መሰቀል ላይ እንዲህ ሆኖ፡)፡ ("ተፈጸመ፡" እሰኪል ድረሰ)፡ ሁሉ ደሰ አሰኘው። የተወው መንፈሰ፡ በፋሲካ ጠዋት ተመልሶ እሰኪወሰደው ድረሰ **ሰለ** ጽድቃችንም እሰኪያነሣው ድረሰ እግዚአብሔርን ደሰ አሰኘ።

257 በዚያም ዮሐንሰ አሻቅቦ አየና በናሰ እግሮቹ እና በምድር ሁሉ ላይ፡ የሚመላለሱትን የእሳት ነበልባል አይኖቹንም አየው። ዳንኤልም ከዚያ ከሰባት መቶ ዓመያት በፊት፡ ያው አካልን፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፡ በተመሳሳይ መልኩ አይቶታል፡ በዘመናት የሸመገለውና፡ የሰውንም ልጅ የሚመሰለውን ከእርሱም ጋር በአንድነት አየው፡ በነጩ ዙፋን ፍርድ ፊት፡ ፍርድም ሁሉ ለእርሱ ተሰጠው።

258 ወዳጆች ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች ሰናይ፡ ምን ዓይነት ሰዎች ልንሆን ይገባናል? እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ ጸሎቴ ነው። አያችሁ? ትወዱታላችሁ? ታምኑታላችሁን? ነፍሳችሁሰ በርሱ ዘንድ ጸንታለችን?

259 ለእፍታ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

260 **ነፍሴን በእረፍት ሰፍራ አኖርኳት**፡ እያልን በዝግታ ዝማሬ እየዘመርን፡ ረጋ እያልን በትህትና፡ "ነፍሴን የሚያጠፏት እነዚያን የማዕበል ጩኸቶች ከእንግዲህ አልሰማቸው፡ ሰለ ነፍሴ ግን ጣፋጭ ሰላም እሰብካታለሁ።" አሁን በመረጋጋት፡ በትህትና፡ ሁላችንም።

ነፍሴን በእረፍቱ ሰፍራ አኖርኳት፡
ላልሄድ ወደ ጫካው ወደ ጥርጣሬው ባሕር ላልወሰዳት፡
በጥልቁ ማዕበል፡ ጫካውም በቁጣው ሲጠረግ፡
በኢየሱሰ ግን አገኘን የዘላለም ደህንነት።

ነፍሴን በእረፍቱ ሰፍራ አኖርኳት፡
ላልሄድ ወደ ጫካው ወደ ጥርጣሬው ባሕር ላልወሰዳት፡
በጥልቁ ማዕበል፡ ጫካውም በቁጣው ሲጠረግ፡
በኢየሱሰ ግን አገኘን የዘላለም ደህንነት።

በላዬ ይብራ (የክብር ጨረር፣ ጌታ ሆይ፣) ጌታ ሆይ፣
በላዬ ይብራ፡
የብርሃን ቤት ብርሃን በላዬ ይብራ፡
አቤቱ፡ በላዬ ይብራ፡ ጌታ ሆይ፡ በላዬ ይብራ፡

እጆቻችንን ወደ እርሱ እናንሳ።

የብርሃን ቤት ብርሃን በላዬ ይብራ።

ኢየሱስን መምሰል (አዎን፡ ጌታ ሆይ።) ኢየሱስን
መምሰል።
በምድር ምኞቴ እርሱን መምሰል ነው፡
በህይወት ጉዞ ከምድር ወደ ክብር የምጓዘው፡
ጸሎቴ እርሱን ልምሰል ብቻ ነው።

... አቤቱ አንተ ድንቅ አዳኝ፡
በምድር ምኞቴ እርሱን መምሰል ነው፡
በህይወት ጉዞ ከምድር ወደ ክብር የምጓዘው፡

261 የእርሱን መገኘት በማንፀባረቅ፡ ህይወቱ በእናንተ እንዲኖር ትፈልጋላችሁ? ፈልጋችሁ፡ እስከ አሁንድ ድረስ ያላገኛችሁ እንደሆነ፡ ለጸሎት ትቆማላችሁን? በጸሎት መታሰብ የሚፈልግ ሰው። ጌታ ይባርካችሁ።

ከቤተልሔም ግርግም...

አሁን እንደቆማችሁ፡ ቆዩ።

... እንግዳ ተወለደ፡ (ለአለም እንግዳ ትሆናላችሁ።)
በምድር ምኞቴ እርሱን መምሰል ነው፡
በህይወት ጉዞ ከምድር ወደ ክብር የምጓዘው፡
ጸሎቴ እርሱን ልምሰል ብቻ ነው።

ኢየሱስን መምሰል፡ ኢየሱስን መምሰል፡ (ፍላጎቴ ይህ
ነው።)
በምድር ምኞቴ እርሱን መምሰል ነው፡
በህይወት ጉዞ ከምድር ወደ ክብር የምጓዘው፡
እኔ እንደ እርሱ ለመሆን ብቻ እጠይቃለሁ።

... በመረጋጋት፡ በትሕትና እና በእርጋታ።

262 አሁን፡ የሰማይ አባት ሆይ፡ ብዙዎች በእግራቸው የቆሙ አንተን መቀበል የሚፈልጉ ናቸው። መንከራተት ሰልችቷቸው፡ በሕይወት ማዕበል፡ የት እንደሚያደርሳቸው ሳያውቁ ተንሸራተዋል፡ ምናልባትም ቀኑ ሳያልቅ በፊት ልብ መምታቱን ሊያቆም ይችላል፡ ከዚያም ታላቁ ማዕበል፡ ከሚንሳፈፍ ነፍሳቸው፡ ፊት፡ ይፈስባቸዋል። ራሳቸውን መስለው ኖሩ፡ ዓለምን መስለው ኖሩ፡ አሁን ግን ጌታ ሆይ፡ አንተን መምሰል ወደዱ። አባት ሆይ፡ የአንተ ናቸው፡ አንተ ልባቸውን እና የልባቸውን አሳብ ታውቃለህና፡ በመንግሥትህ ውስጥ ተቀበላቸው። አንተም በመጽሐፍ ጽፈህ፡ በከንፈሮችህ እንዲህ ተናግረሃልና፦ “ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።” ደግሞም፡ ጌታ ሆይ፡ “ቀኑ ቀርቧልና የሚያነቡት የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል የሚሰሙ፡ ብጹአን ናቸው ብለሃልና።” ጊዜው እንደቀረበ ተገንዝበዋል። ከእንግዲህ

አይንሳፈፉም፡ ጌታ ሆይ። የሕይወትን ገመድ ወርውርላቸው፡ ጌታ ሆይ፡ ወደ ራስህ ሳባቸው። ከዛሬ ምሽት ጀምረው የኢየሱስ ክርስቶስን ብርሃን እያንጸባረቁ ይኃዙ። እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለአንተ አደራ እሰጣቸዋለሁ። በጥምቀት እዚህ ቤተ ክርስቲያን ጌታን በትሕትና መከተል ይሁንላቸው፡ በቀሪ ዘመናቸው ኢየሱስን እንዲመስሉ በሕይወታቸው መንፈስ ቅዱስን ይልበሱ። በስሙ እንጠይቃለን።

ኢየሱስን መምሰል፡ እንደ እርሱ...

263 አንዳንዶቻችሁ ክርስትያን የሆናችሁ ከእነዚያ ሰዎች አጠገብ ቆማችሁ፡ ወይም የተቀመጣችሁ፡ ጠጋ በሉና እጆቻቸውን ጨብጣችሁ ሰላም በሏቸው። “ሰለ ነፍስህ እግዚአብሔር ይክበር፡” እያላችሁ እጆቻችሁን ጫኑባቸውና። መሠዊያዎቻችን ሁሉ እዚህ በልጆች እና ነገሮች ተሞልተዋል፡ እዚህ ልንጠራቸው አንችልም።

... በህይወት ጉዞ ከምድር ወደ ክብር የምኃዘው፡
ጸሎቴ እርሱን ልምሰል ብቻ ነው።

በላዬ ይብራ፡ አቤቱ፡ በላዬ ይብራ፡
አቤቱ፡ የብርሃን ቤት ብርሃን፡ በላዬ ይብራ፡
አቤቱ፡ በላዬ ይብራ፡ ጌታ ሆይ፡ በላዬ ይብራ፡
የብርሃን ቤት ብርሃን፡ በላዬ ይብራ፡

264 ደስተኞች ሆናችሁ ወይ? ደስ አላላችሁምን? ክርስትያን በመሆናችሁ ደስተኞች አልሆናችሁም ወይ? መዝሙር ለመዘመር እየተዘጋጀን፡ አሁን በአጠገባችሁ ከሚገኝ ሰው ጋር ተጨባበጡ፡ “በብርሃን ውስጥ እንሄዳለን፡ ይህ የሚያምር ብርሃን፡” የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን በሥጋ ሲገለጥ።

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃን እንሄዳለን፡
የምሕረት ጠል ወደሚበራበት እንቀርባለን፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

ሁላችሁም፡ ዘምሩ!

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃን እንሄዳለን፡
የምሕረት ጠል ወደሚበራበት እንቀርባለን፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

የብርሃን ቅዱሳን ድምጻችሁ፡ ይሰማል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል፡
የሰማይ ነጋሪት ድምጻቸው ይሰማል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

አሁን እጆቻችሁን አንሱ።

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃን እንሄዳለን፡
የምሕረት ጠል ወደሚበራበት እንቀርባለን፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

በሚያምረው ብርሃን፡ ጉዞአችንን በብርሃን እንቀጥላለን፡
የምሕረት ጠል ወደሚበራበት እንቀርባለን፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

በሚያምረው ብርሃን፡ (በወንጌል ብርሃን) በብርሃን እንሄዳለን፡
የምሕረት ጠል ወደሚበራበት እንቀርባለን፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

265 ወደ መጀመሪያው፡ በጴንጤቆስጤ ዕለት መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያን ላይ ወረደ። መልእክቱ ወደ ሰምርኔስ ተጓዘ፡ በዚያም ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው፡ ኢራኔዎስ ቆመ፡ በልሳኖችም ሲናገር፡ በእግዚአብሔር ኃይል፡ ሙታንን እያስነሣ፡ ድውያንን እየፈወሰ፡ በብርሃን ተመላለሰ። ከእርሱ በኋላ ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው፡ ኮሎምባ መጣ። ብዙ ሌሎች ታላላቅ ቅዱሳን መልእክቱን ይዘው፡ በብርሃን ተጉዘዋል፡ በወንጌል ብርሃን ተራምደዋል፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን ያበራው ያው ብርሃን ይዘው ተጉዘዋል፡ በሙቀቷ መካከል እንደምትቆም እንደ ጸሀይ፡ እርሱም በህዝቡ መካከል እና ብርሃኑን በሚያንጸባርቁ ሰባት የወርቅ መቅረዞች መካከል የቆመው ክርስቶስ ነው።

266 እነሆ 1961 ደርሰናል፡

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃን እንሄዳለን፡
የምሕረት ጠል ወደሚበራበት እንቀርባለን፡
አቤቱ፡ በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

እንቁም።

እንቀጥል እንሂድ በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃን እንሄዳለን፡
የምሕረት ጠል ወደሚበራበት እንቀርባለን፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

ትወዱታላችሁ ወይ?

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ፡
ምክንያቱ (ምክንያቱ'ማ) ቀድሞ ስለወደደኝ፡
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

267 እንደገና ወደ ዓለም ነገሮች አልመለሰም። እኔ ለአለም ሞቻለሁ አለምም ለእኔ ሞታለች። በመንፈስ ቅዱስ እየተመራሁ፡ በክርስቶስ ብቻ እመላለሳለሁ። በረከቱን ስለሚያበራልኝና፡ ስለወደደኝ እወደዋለሁ፡ ወደ መንግሥቱ የቀኝ እጅ ህብረት ሰጠኝ። አሁን የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ነን፡ እናም በመጨረሻው ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም፡ ነገር ግን እርሱ እንዳለ እናየዋለንና፡ የእርሱን ክብር የሚመስል አካል እንዲኖረን እናውቃለን።

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃን እንሄዳለን፡
የምሕረት ጠል ወደሚበራበት እንቀርባለን፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

268 ትወዱታላችሁ ወይ? ታውቃላችሁ፡ መልእክቱ ከተሰበከ እና ከተነገረ በኋላ፡ ሰዎቹ ወደ መዝሙር ገብተው በመንፈስ ወደ አምልኮና መዝሙር ሲዘምሩ መስማት እወዳለሁ። ከጥሩ የጥንት መዝሙር የበለጠ የሚያምር ነገር የለም። አዎን። የቆዩ-የጴንጤቆስጤ ቆንጆ ዝማሬዎችን እውዳለሁ፡ ምን እየዘመሩ እንዳሉ የማያውቁ ፊታቸው ሰማያዊ እስኪሆኑ ድረስ ከልክ በላይ የሚሰረቀረቁ፡ የሰለጠኑ ድምጾች አይመስጡኝም። ምናልባት ዜማው በቅርጫት ለመጣል እንኳን የማይመች ግን የጴንጤቆስጤ በረከት፡ ያለው ሰው አሁን ሲዘምር ይሰበኛል። አቤት፡ እነዚያ የመስቀል መዝሙሮች እንዴት—የተከበሩ ናቸው! ኦህ፡ ማይ!

የመዝጊያ መዝሙራችን ይህ ነው፡

የኢየሱስ ስም ካንተ ጋር ውሰድ፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
ደስታ እና ምቾት ይሰጣል፡
በሄድክበት እርሱን ውሰድ።

ነገ ማታ በሰባት ሰአት፡ በሰባት ሰአት ላይ፡ አገልግሎቶቹ ይጀምራሉ።

ለኢየሱስ ስም እንሰግዳለን፡
በእግሩ ስር እንወድቃለን፡
የነገሥታት ንጉሥ በሰማይ እናከብራለን፡
ጉዟችን ሲጠናቀቅ።

አሁን ሁላችንም እንዘምር።

የኢየሱስ ስም ካንተ ጋር ውሰድ፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
ደስታ እና ምቾት ይሰጣል፡
ኦህ፡ በሄድክበት እርሱን ውሰድ።

ድንቅ ስም፡ ኦ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ ኦ ውብ ስም! (ውብ ስም!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

269 አሁን፡ ዛሬ ማታ ጨርሰነዋል። አሁን… “ጠዋት አገልግሎት ቢኖርስ፡” በማለት ጠይቀውኛል? አይ፡ ነገ አይኖርም፡ ነገ በደንብ እረፍት እርጉ። ምናልባት ነገ ምሽት፡ መልእክቱ ማስተላለፍ አልችል ይሆናል፡ በሚቀጥለው ቀን አደርገዋለሁ። የዚህን መልእክት ሙላት… ማዳረስ በተሳነኝ ጊዜ ሁሉ፡ በሚቀጥለው ቀን አደርገዋለሁ። በዚህ ሁሉ ግን ተማምነናል። በቤተ ክርስትያን ዘመናት እንደገባችሁ አምናላችሁ። አይደል?

እሺ አሁን በጸጥታ እየዘመርን አንገታችንን ዝቅ እናደርጋለን፡

ለኢየሱስ ስም እንስግዳለን፡ (ምላስ ሁሉ ይመሰክርለታል)
በእግሩ ስር እንወድቃለን፡
የነገሥታት ንጉሥ በሰማይ እናከብራለን፡
ጉዟችን ሲጠናቀቅ

ድንቅ ስም፡ ኦ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ ኦ ውብ ስም! (ውብ ስም!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

**የፍጥሞ ራዕይ** AMH60-1204E

(The Patmos Vision)

**የኢየሱስ ክርሰቶሰ መገለጥ ተከታታይ ትምህርት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሁድ ማታ፡ ታሕሣሰ 4፡ 1960፡ በዩ.ኤስ.ኤ. ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ ከሚገኘው ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

# የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈለጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org